አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ

የቋንቋዎች ጥናት ፋክልቲ

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር



CLEARED FROM ILS LIBRARY


# በተግባራዊ ስነ-ልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ILS LIBRARY
ADDIS ABABA UNIVERSITY



በ

ዮሐንስ አያሌው


መጋቢት፣ 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ

የቋንቋዎች ጥናት ፋክልቲ

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

# የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ የማስተማር ሁኔታ የአተገባበር ግምገማ (በሰሜን ወሎ ዞን በሚገኙ ሁለት የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች)

በ

ዮሐንስ አያሌው

መጋቢት፣ 2003 ዓ.ም

የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ ፊርማ

ፈታኝ ፊርማ

# ምስጋና

በመጀመሪያ በየጊዜው የሚገጥሙኝን እንቅፋቶች ሁሉ ከፊቴ ገለል እያደረገ የህይወት መንገዴን ቀና ላደረገልኝ ኤልሻዳይ እግዚአብሔር ምስጋና ይሁን፡፡

በመቀጠል ይህንን የትምህርት እድል ለሰጠኝና ሙሉ ወጪዬን ሸፍኖ ላስተማረኝ የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ በተለይም ለቢሮ ኃላፊው ለአቶ ጥላዬ ጌቴ የላቀ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

አማካሪዎቼ አቶ ታደሰ ሲባሞ እና አቶ አክሊሉ ይልማ የጥናት ሥራዬ መልክ እንዲይዝ ላበረከታችሁልኝ የተቀላጠፈ ሙያዊ እገዛ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

ልዩ ስጦታዬ ባለቤቴ ራዲያ መሐመድ ለዚህች ቀን እንድበቃ በጥንካሬ ከጎኔ ስለቆምሽ ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡ የእኔ በመሆንሽ እድለኛ ነኝ፡፡

ወንድሜ አብርሃም ወ/ሥላሴ፡- ሰው በሚያስፈልገኝ ሰዓት ሁሌም ከጎኔ የማገኝህ አንተን ለማመስገን ምን ቃል ይኖረኛል ብለህ!
ተዘራወርቅ የሱፍ፡- ለእኔ ያለሽ አሳቢነት ዘወትር በልቤ ውስጥ አለ፡፡

ጓደኛዬ እሸቴ መብራት አብረን ባሳለፍነው የትምህርት ጊዜ ለነበረህ ቀናነትና ተባባሪነት ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

# ማውጫ

**አርዕስት** **ገጽ**


ምስጋና ......................................................... I

ማውጫ ......................................................... II

የሰንጠረዥ ማውጫ ......................................................... V

አጠቃሎ ......................................................... VI

**ምዕራፍ አንድ፡- መግቢያ**

1.1 የጥናቱ ዳራ ......................................................... 1

1.2 ሰበበ ጥናት ......................................................... 2

1.3 የጥናቱ ዓላማ ......................................................... 2

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ ......................................................... 3

1.5 የጥናቱ ወሰን ......................................................... 3

1.6 ሙዳየ ቃላት ......................................................... 4

**ምዕራፍ ሁለት፡- ክለሳ ድርሳናት**

2.1 የሰዋስው ምንነት ......................................................... 5

2.2 የሰዋስው ትምህርት ታሪካዊ ዳራ ......................................................... 6

2.3 በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የሰዋስው ፋይዳ ......................................................... 7

2.4 የሰዋስው ዘርፎች ......................................................... 8

2.5 ስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው ......................................................... 9

2.6 በትምህርትነት የሚቀርቡ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ......................................................... 11

2.6.1 የቋንቋ ድምፆች ......................................................... 12

2.6.2 ምዕላዶች ......................................................... 12

2.6.3 ቃላት ......................................................... 12

2.6.4 ሐረጋት ......................................................... 12

2.6.5 አረፍተ ነገሮች ......................................................... 13

2.7 የሰዋስው ማስተማሪያ ይዘቶችና ዘዴዎች ሲመረጡ ከግንዛቤ መግባት ያለባቸው ጉዳዮች ......................................................... 13

2.8 የሰዋስው ትምህርት ስነ-አቀራረቦች እና ዘዴዎች ......................................................... 14

2.8.1 ውጤት ተኮር አቀራረብ ....................................................15
2.8.1.1 ሰዋስው ወትርጉም ዘዴ ....................................................16
2.8.1.2 ቀጥተኛ ዘዴ ....................................................16
2.8.1.3 ንባባዊ ዘዴ ....................................................17
2.8.2 ተግባቦታዊ (ክሂል ተኮር) አቀራረብ ....................................................17
2.8.2.1 አእምሮታዊ ዘዴ ....................................................20
2.8.2.2 ዝምታዊ ዘዴ ....................................................20
2.8.2.3 ማህበራዊ ዘዴ ....................................................20
2.9 ሰዋስውን የማስተማር መርሆች ....................................................21
2.9.1 ይዘትን የሚመለከቱ ሰዋስውን የማስተማር መርሆች ....................................................22
2.9.2 የማስተማር ስልትን የሚመለከቱ ሰዋስውን የማስተማር መርሆች ....................................................23
2.10 በቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ....................................................24
2.10.1 ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ ....................................................24
2.10.2 ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ ....................................................25
2.10.3 ሰዋስውን እንደ ክሂል ማቅረብ ....................................................26
2.11 የቋንቋ መምህር ሊኖሩት የሚገቡ ሰዋስዋዊ እውቀቶች እና አስፈላጊነታቸው ....................................................27
2.11.1 ሰዋስውና ተግባቦት የማይነጣጠሉመሆናቸውን ማወቅ ....................................................27
2.11.2 የታላሚው ቋንቋ ሰዋስው እውቀት ....................................................27
2.11.3 የሰዋስውና የተግባቦት እውቀት ....................................................28
2.11.4 ሰዋስውን በውጤት ተኮር ዘዴ የማቅረብ እውቀት ....................................................28
2.11.5 ንፅፅራዊ የሰዋስው እውቀት ....................................................28
2.12 የሰዋስው ትምህርት ዕቅድ ....................................................29
2.13 ሰዋስዋዊ ስህተትን ማረም ....................................................30
2.14 የሰዋስው ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ ....................................................31
2.15 ለናሙና የቀረበ ዕለታዊ የሰዋስው ትምህርት ....................................................34
2.16 ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ቀደምት ስራዎች ቅኝት ....................................................37
**ምዕራፍ ሦስት፡- የአጠናን ዘዴ** ....................................................39
3.1 የትምህርት ቤቶች፣ የመማሪያ ክፍሎችና የመምህራን ናሙና አወሳሰድ ....................................................39
3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪዎች እና ዘዴዎች ....................................................39

3.2.1 ምልከታ ....................................................................................39
3.2.2 ቃለ መጠይቅ ................................................................................40
3.2.3 የሰነድ ፍተሻ .................................................................................40
3.3 የመረጃ አደረጃጀትና ትንተና .............................................................40
**ምዕራፍ አራት፡- የመረጃ ትንተና እና የጥናቱ ውጤት** ..........................................41
4.1 በምልከታ በመምህራን የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ላይ
የተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና .........................................................41
4.1.1 መምህር አንድ ...........................................................................42
4.1.2 መምህር ሁለት ..........................................................................52
4.1.3 መምህር ሦስት ..........................................................................61
4.1.4 መምህር አራት ..........................................................................68
4.2 በቃለ መጠይቅ ከመምህራን የተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና ..................................74
4.3 በሰነድ ፍተሻ የተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና ................................................80
4.3.1 በ11ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ውስጥ የሰዋስዋዊ ይዘቶች
አቀራረብ ግምገማ ..........................................................................80
4.3.2 በ11ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የተካተቱ ሰዋስዋዊ ይዘቶች
አቀራረብ ግመገማ..........................................................................86
4.3.3 በ11ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመምህሩ መመሪያ መፅሀፍ ውስጥ
የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ግምገማ...............................................92
**ምዕራፍ አምስት፡- ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳብ**..............................................94
5.1 ማጠቃለያ....................................................................................94
5.1.1 በምልከታ ከተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና የተገኙ ውጤቶች .................................94
5.1.2 በቃለ መጠይቅ ከተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና የተገኙ ውጤቶች ............................95
5.1.3 በሰነድ ፍተሻ ከተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና የተገኙ ውጤቶች ..............................96
5.2 የመፍትሄ ሀሳብ................................................................................97
ዋቢ. ፅሁፎች ......................................................................................98
አባሪዎች
አባሪ 1፡- የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ምልከታ መከታተያ ቅፅ ..............................100
አባሪ 2፡- ከመምህራን ጋር የተካሄደ ቃለ መጠይቅ ..............................................103

# የሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ 1፡ በስነ-ልሳን አተገባበር ላይ የኮርደር እይታ ....................11
ሰንጠረዥ 2፡ የሰዋሰው ትምህርትን በተግባቦታዊ አቀራረብ የማስተማር ሂደት ....................34
ሰንጠረዥ 3፡ በ11ኛ ክፍል የአማርኛ መርሃ ትምህርት ውስጥ የቀረበ የሰዋሰው ትምህርት ....................84
ሰንጠረዥ 4፡ በ11ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የቋንቋ ትምህርት ዘርፎች ስርጭት ....................87

# አጠቃሎ /Abstract/

ይህ ጥናት ይዞት የተነሳው ዋነኛ አላማ የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ የማስተማር ሁኔታ በሰሜን ወሎ ዞን በሚገኙ ሁለት የከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ ትምህርት ቤቶች 11ኛ ክፍል ውስጥ ምን እንደሚመስል በጥልቀት በመገምገም ችግሮች የሚስተዋሉ ከሆነ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን መጠቆም የሚል ነው፡፡

ለጥናቱ የተመረጡት ትምህርት ቤቶች የወልድያ የከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ እና የቆቦ አጠቃላይና የከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲሆኑ የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ በሁለቱ ትምህርትቤቶች በተተኳሪው የክፍል ደረጃ አማርኛ ቋንቋን ከሚያስተምሩ አራት መምህራን፣ እነዚህ መምህራን ከሚያስተምሩባቸው አራት የመማሪያ ክፍሎችና ለ11ኛ ክፍል ከተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ማስተማሪያ መሣሪያዎች መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ መረጃዎቹ የተሰበሰቡት በምልከታ፣ ከመምህራኑ ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና ለክፍል ደረጃው የተዘጋጁትን የሰዋስው ማስተማሪያ ሰነዶች ማለትም መርሃ ትምህርቱን፣ የተማሪው መጽሐፍን እና የመምህሩ መመሪያ በመፈተሽ ነው፡፡

በእነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች የተገኙበትን ምንጭ መሠረት በማድረግ በየፈርጃቸው ተመድበው ተተንትነዋል፡፡ የትንተናው ውጤት እንደሚያሳየውም መምህራኑ የሰዋስው ትምህርትን በተግባቦታዊ አቀራረብ አያስተምሩም፤ ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ ስለማስተማርም የግንዛቤ እጥረት አለባቸው፡፡ በተጨማሪም ለ11ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን ለማስተማር የተዘጋጁት የማስተማሪያ መሣሪያዎች ሰዋስውን ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅቶና በተግባቦታዊ አቀራረብ ለማስተማር በሚያስችል መልኩ አልተዘጋጁም፡፡

ስለዚህም መምህራኑ ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ እንዴት ማስተማር እንደሚቻል ግንዛቤ የሚያገኙበት ሁኔታ ቢመቻችና ለክፍል ደረጃው የተዘጋጁት የማስተማሪያ መሣሪያዎች ሰዋስውን ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅተውና ተግባቦታዊ በሆነ አቀራረብ ቢዘጋጁ በጥናቱ የታዩት ችግሮች ሊቀረፉ እንደሚችሉ የዚህ ጥናት አቅራቢ ያምናል፡፡

# ምዕራፍ አንድ፡- መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ትኩረት ከሚደረግባቸው አበይት ርዕሰ ጉዳዮች መካከል አንዱ የሰዋስው ትምህርት ነው፡፡ ሰዋስውን የማስተማር ተግባር ረጅም ዘመን ያስቆጠረ ሲሆን በአሁኑ ጊዜም ቦታ የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ ቀደምትነቱን ስናይ ጥንታዊ በሚባሉት የግሪክና የላቲን ቋንቋዎች ትምህርት ውስጥ በሰፊው ተግባር ላይ ይውል እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ /Brown 2000:15, Richards and Rodgers 1995:1/፡፡ በአሁኑ ዘመን በሀገራችን የተሰጠውን ትኩረት በተመለከተም በክፍል ውስጥ እየተሰጠ ያለውን የቋንቋ ትምህርት እና በየክፍል ደረጃው ቋንቋን ለማስተማር ታስቦ የተዘጋጁትን የማስተማሪያ መሳሪዎች በመመልከት መረዳት ይቻላል፡፡ ለተለያዩ የክፍል ደረጃዎች የተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መሳሪዎች ማለትም መርሃ ትምህርቱ፣ የተማሪው መጽሀፍ እና የመምህሩ መመሪያ ሰዋስውን እንደ አንድ ዋነኛ ይዘት አድርገው አካተው ይዘዋል፡፡ በዚህም መሰረት በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች በትምህርትነት በመሰጠት ላይ ይገኛል፡፡

ሰዋስዋዊ ይዘቶች በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተካተው መቅረባቸው ለተሟላ የቋንቋ ችሎታ መዳበር ፋይዳ ያለው ጉዳይ ሲሆን ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ጥያቄ "ሰዋስውን በምን መንገድ ማስተማር ይገባል?" የሚል ይሆናል፡፡ በዚህ ላይ የተለያዩ ምሁራን ሰዋስውን በውጤታማነት ለማስተማር ያስችላሉ ያሏቸውን ስነ-አቀራረቦች እና የማስተማሪ ዘዴዎች ሰንዝረዋል፡፡ አብዛኞቹን የሚያስማማው ሀሳብ ደግሞ ሰዋስውን በሰዋስውነቱ በደረቁ ሳይሆን ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር አዋህዶ እና ተግባቦታዊ በሆነ መንገድ ማስተማር ይገባል የሚለው ነው /መሰሉ 1994፡59፣ Bygate, M. et.al 1994፡2፣ Celce-Murcia 1991፡283፣ Krashen 1987፡113 እና Harmer 1987፡3/፡፡ የምሁራኑን አስተያየት ይዘን በሀገራችን በቋንቋ ትምህርት ክፍሎች ውስጥ አተገባበሩ ምን ይመስላል? የሚለውን ለማወቅ ብንፈልግ ራሱን የቻለ ሰፊ እና ጥልቅ ምርምር ይጠይቃል፡፡ የዚህ ጥናት ማዕከላዊ ትኩረትም ይኸው ነው፡፡

የጥናቱ ዋነኛ ጥኩረት አማርኛ ቋንቋን በማተማር ሂደት የሰዋስው ትምህርት አተገባበር ምሁራኑ በሚመክሩት ማለትም በተግባቦታዊ አቀራረብ የመሰጠት ሁኔታው ምን እንደሚመስል ሳይንሳዊ በሆነ ጥናት መፈተሽ ነው፡፡ ለዚህ ተግባር ይረዳ ዘንድም በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ወሎ ዞን ስር የሚገኙ ሁለት የከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ ትምህርት ቤቶች ተመርጠዋል፡፡ እነዚህም የወልድያ የከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ ትምህርት ቤት እና የቆቦ አጠቃላይና የከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲሆኑ ተተኳሪው የክፍል ደረጃም 11ኛ ክፍል ነው፡፡ ጥናቱ በዚህ የክፍል ደረጃ ሰዋስውን ለማስተማር ታስበው

በተዘጋጁ የማስተማሪያ መሳሪዎች፣ በሰዋስው ትምህርቱ አቀራረብ እና መምህራኑ ሰዋስውን ስለማስተማር ባላቸው ግንዛቤ ላይ ተመርኩዞ የሰዋስው ትምህርት በተለይ በተግባቦታዊ አቀራብ የመስጠት ሁኔታው ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ ሞክሯል፡፡

## 1.2 ሰበበ ጥናት

አጥኚው በዚህ ርዕስ ላይ እንዲያተኩር ያደረጉት ምክንያቶች በዋነኛነት ሁለት ናቸው፡፡ የመጀመሪያው አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሚያስተምርበት ወቅት የሰዋስው ትምህርት አተገባበርን በተመለከተ ክፍተት መኖሩን መታዘቡ ነው፡፡ ይኸውም መምህራኑ የቋንቋ ትምህርት ዋነኛ ዓላማን ታሳቢ በማድረግ የተማሪዎቹን የተግባቦት ችሎታ ለማዳበር የሚያስችሉ ተግባራትን ከማከናወን ይልቅ ሰዋስዋዊ ይዘቶችን በቀጥታ በማቅረብ ገለፃና ማብራሪያ እየሰጡ ሲያስተምሩ ማስተዋሉ ነው፡፡ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ አጥኚው የድህረ ምረቃ ትምህርቱን በሚከታተልበት ወቅት በዘመናችን ተቀባይነትን እየገኘ የመጣው ሰዋስውን የማስተማሪያ አቀራረብ "ተግባቦታዊ በሆነ መንገድ ማስተማር" የሚለው መሆኑን መረዳቱ ነው፡፡ ይህ ግንዛቤም የአጥኚውን ቀልብ ስቦ በርዕሰ ጉዳዩ ላይ እንደሚያተኩር ሰበብ ሆኖታል፡፡ በእነዚህ ሁኔታዎች በመነሳሳት አጥኚው፡-

1. በሰሜን ወሎ ዞን በሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 11ኛ ክፍል ውስጥ ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ የማተማር ሁኔታ ምን ይመስላል?
2. ትምህርቱ በተግባቦታዊ አቀራረብ የማይሰጥ ከሆነ ምክንያቶቹ ምንድን ናቸው?

የሚሉትን መሪ ጥያቄዎች በመያዝ ጥናቱን አካሂዷል፡፡

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ በወልድያ የከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ እና በቆቦ አጠቃላይና የከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 11ኛ ክፍል ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ የማተማር ሁኔታ ምን እንደሚመስል በጥልቀት በማጥናት ችግሮች የሚስተዋሉ ከሆነ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን መጠቆም ነው፡፡ በዚህ ዋና ዓላማ ስር ሌሎች ንዑሳን ዓላማዎች አሉ፡፡ እነዚህም፡-

- መምህሩ በዕለታዊ ወይም በሳምንታዊ የትምህርት ዕቅዱ የሰዋስው ትምህርቱን ዓላማ በተገቢ ሁኔታ መግለጹ፣
- መምህሩ የሰዋስው ትምህርትን በተግባቦታዊ አቀራረብ ለማስተማር የሚያስችሉ ቅደም ተከተሎችን ጠብቆ ማስተማሩን መገምገም፣
- መምህራን በሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ላይ ያላቸውን እውቀት መገምገም እና

- ለ11ኛ ክፍል የተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መሣሪያዎች ሰዋስውን ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅቶና በተግባቦታዊ አቀራረብ ለማስተማር በሚያስችል መልኩ መዘጋጀታቸውን መፈተሽ ናቸው፡፡

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ከዚህ ጥናት የሚገኘው ውጤት ከሰዋስው ትምህርት ጋር በተያያዘ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል፡፡

- መምህራን የሰዋስው ትምህርትን በክፍል ውስጥ እንዴት ተግባቦታዊ በሆነ አቀራረብ መተግበር እንደሚችሉ አቅጣጫ ይጠቁማል፣
- ለክፍል ደረጃው የሚያገለግሉት የሰዋስው ማስተማሪያ መሳሪዎች ማለትም መርሃ ትምህርቱ፣ የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ፣ የመምህሩ መመሪያ እና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው መሳሪያዎች በሚዘጋጁበት ወይም በሚሻሻሉበት ወቅት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅተው እና ተግባቦታዊ በሆነ አቀራረብ የሚቀርቡበትን ብልሃት ይጠቁማል፣
- በዚህ ርዕስ ዙሪያ ጥናት ማድረግ ለሚፈልጉ አጥኚዎች ማጣቀሻ ወይም መነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፣

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በ2003 ዓ.ም በሰሜን ወሎ ዞን ስር በሚገኙ ሁለት የከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 11ኛ ክፍል ውስጥ የሚሰጠው የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ትምህርት ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅቶ እና ተግባቦታዊ በሆነ አቀራረብ የመተግበር ሁኔታን ይመለከታል፡፡ በዚህ ስር ጥናቱ የዳሰሳቸው ጉዳዮች፡-

- በክፍል ውስጥ የመምህራኑ የሰዋስው ትምህርት አተገባበር፣
- መምህራኑ ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ በማስተማር ላይ ያላቸው ግንዛቤ እና
- የመምህሩ ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ፣ መርሃ ትምህርቱ፣ የተማሪው መጽሀፍ እና የመምህሩ መመሪያ ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ ለማስተማር ታስቦ የመዘጋጀታቸው ሁኔታ ናቸው፡፡

## 1.6 ሙዳዩ ቃላት

| | |
|---|---|
| ማህበራዊ የቋንቋ አጠቃቀም | Language use in a social context |
| ማቅረቢያ | Presentation |
| ማብራራት | Demonstration |
| ማውጣጣት | Elicitation |
| ሰዋስው (የቋንቋ ስርዓት) | Grammar |
| ስነ ትምህርታዊ ሰዋስው | Pedagogical Grammar |
| ቅርፅ | Form |
| ተግባቦታዊ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ | Communicative Grammar Teaching Approach |
| ትውረት | Theory |
| አቀራረብ | Approach |
| አፍልቆታዊ | Generative |
| አፍፅሞ ማፍለቅ | Accurate Production |
| ገለፃ | Explanation |
| የማስተማር ዘዴ | Teaching Method |
| ውጤት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ | Deductive/overt/Approach |
| ጥንታዊ ሰዋስው | Traditional Grammar |
| ፍልቀ ራስ | Immediate Creativity |
| ፍቺ | Meaning |

# ምዕራፍ ሁለት:- ክለሳ ድርሳናት

## 2.1. የሰዋስው ምንነት

"ሰዋስው" የሚለው ፅንሰ ሃሳብ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ረጅም እድሜ እንደማስቆጠሩ በምንነቱ ላይ የበርካታ ምሁራን አስተያየቶች ተሰንዝረውበታል። ከእነዚህም መካከል፣ Ur (1994:4) "ሰዋስው ማለት በቋንቋ አማካኝነት የተስፋፋ ፍችን ለመመስረት ቃላት እርስ በርሳቸው የሚቀናጁበት መንገድ ነው" ሲሉ Harmer (1989:1) ደግሞ Longman መዝገበ ቃላትን ጠቅሰው "ሰዋሰው ማለት ቃላት ቅርፃቸውን የሚቀያይሩበት እና በአረፍተ ነገር ውስጥ የሚቀናጁበት ህግ ወይም ስርዓት ነው" ይላሉ። በሁለቱም ምሁራን ገለፃ ውስጥ ትኩረት ተሰጥቷቸው የምናገኛቸው ነጥቦች "የቃላት የእርስ በርስ ቅንጅት" እና "የመቀናጃ መንገድ ወይም ህግ" የሚሉት ናቸው። Harmer ከላይ ያቀረቡትን ብያኔ ሲያብራሩ:-

> *የሰዋስው ህግ ማለት ቃላት ለተለያዩ ሰዋሰዋዊ ሁኔታዎች (ለምሳሌ:- ከአሁን ጊዜ ወደ ኃላፊ ጊዜ፣ከነጠላ ቁጥር ወደ ብዙ ቁጥር ወዘተ ሲቀየሩ) ቅርፃቸውን የሚቀያይሩበትና በዓረፍተ ነገር ውስጥ የሚገቡበት መንገድ ነው። የሰዋስው ህግን ማጥናት ማለት ደግሞ ቃላት በስርዓት ተቀናጅተው ዓረፍተ ነገር እንዴት እንደሚመሰርቱ ማጥናትና መመርመር ማለት ነው*

ይላሉ። Celce-Murcia (1991:16) በበኩላቸው "ቋንቋ በስርዓት የሚመራ ነው። ይህንን ስርዓት የሚያሳየው እሳቤም ሰዋስው ይባላል" ይላሉ።

ከእነዚህ ምሁራን ገለፃ መረዳት እንደሚቻለው ሰዋስው በቋንቋ አማካኝነት መልዕክትን በአግባቡ ለማስተላለፍ የቋንቋ ክፍሎች/Constituents/ የሚቀናጁበት ስርዓት ወይም ህግ ነው። እዚህ ላይ በግልጽ ልንረዳቸው የሚገቡ ሁለት መሰረታዊ የሆኑ ጽንስ ሀሳቦች አሉ። እነሱም የቋንቋ ክፍሎች (Language Constituents) እና ሰዋስው ወይም የቋንቋ ስርአት (Grammar) የሚሉት ናቸው።

የቋንቋ ክፍሎች የምንላቸው የአንድን ቋንቋ የተለያዩ አካላትን ነው። እንደሚታወቀው በቋንቋ አማካኝነት መልዕክት ማስተላለፍና መቀበል ማለትም መግባባት የሚቻለው የተለያዩ የቋንቋ አሀዶችን እንደየአስፈላጊነታቸው እያቀናጁ በመጠቀም ነው። ድምፆች ተቀናጅተው ምዕላዶችንና ቃላትን፣ ቃላት ተቀናጅተው ሀረጋትን፣ ሀረጋት ተቀናጅተው ዓረፍተ ነገሮችን ወዘተ ይመሰርታሉ። የቋንቋ ክፍሎች የምንላቸውም እነዚህን ተግባቦትን ለመፍጠር የሚያስችሉ የተለያዩ የቋንቋ አሀዶችን ነው።

ሰዋስው የምንለው ደግሞ እነዚህ የተለያዩ የቋንቋ አሀዶች ወይም ክፍሎች የሚመሰረቱበትን እና የሚቀናጁበትን ህግ ወይም ስርዓት የሚመለከት ነው። እነዚህ ሁለት ጽንስ ሀሳቦች እርስ

በርሳቸው የጠበቀ ቁርኝት ያላቸው ሲሆኑ በሰዋስው ትምህርት ውስጥም በዋነኛነት የሚነሱ ጉዳዮች ናቸው። የሰዋስው ትምህርት በቋንቋ አማካኝነት መልዕክትን በማስተላለፍ ሂደት ምን ዓይነት የቋንቋ አሀዶች ተግባር ላይ እንደሚውሉ እና እነዚህ መዋቅሮች ቅርፃቸውን የሚቀያይሩበትን ስርዓት ይዳስሳል።

የሰዋስው ምንነት የቋንቋ ክፍሎች እና ስርዓት የሚሉትን ፅንሰ ሀሳቦች ብቻ የሚመለከት እና በእነዚህም የሚገደብ አይደለም። በተጨማሪም የሰው ልጅ ቋንቋን እንዴት ነው ሊያውቅ እና ሊጠቀምበት የሚችለው? ከሚለው አዕምሮአዊ እሳቤ ጋር ይያያዛል። ከዚህ ሀሳብ ጋር በተያያዘ ጌታሁን (2002፡iv) የሚከተለውን ይላሉ።

> *...ሰዋስው ከቋንቋ ጥናቶች ውስጥ ስርዓትን የሚመለከተው ክፍል ነው። በአሁኑ ወቅት ሰዋስው የሚለው ቃል ሁለት አሻሚ ፍችዎችን ይዞ ይገኛል። አንደኛው ፍች የሰው ልጅ የሚጠቀምበትን ቋንቋ እውቀት የሚጠቁመው እና በሰው ልጅ አእምሮ ውስጥ ያለውን ችሎታ ነው። የሰው ልጅ ቋንቋን ሊያውቅ እና ሊጠቀምበት የሚችለው ይህ ችሎታ ስለአለው ነው። ከዚህ አንፃር ሲታይ ሰዋስው አዕምሮአዊ እሳቤ ነው ለማለት ይቻላል። ሁለተኛው ደግሞ የቋንቋ ተመራማሪዎች ስለቋንቋ ስርአትና መዋቅር የሚያደርጉትን ገለፃ የሚጠቁመው ነው። ይህ ፍቺ የአንድን ቋንቋ የስርዓት ጥናት የሚመለከት ስለሆነ ከመጀመሪያው ፍቺ ጠባብ ነው።*

ከዚህ ገለፃ ሰዋስው የቋንቋ ስርዓትና የቋንቋ ክፍሎች እንዲሁም የሰው ልጅ ቋንቋን እንዴት እንደሚያውቅ እና እንደሚጠቀም የሚያጠና የቋንቋ ጥናት ዘርፍ መሆኑን መረዳት ይቻላል። ነገር ግን ይህ ጥናት ትኩረቱን ያደረገው በአንድ በተወሰነ ቋንቋ /አማርኛ/ ሰዋስው ትምህርት አተገባበር ላይ ስለሆነ "የቋንቋ ስርዓት እና ክፍሎች ጥናት" የሚለውን ብያኔ ተከትሎ ይሄዳል። በዚህም መሰረት የተለየ ነገር ካልተጠቆመ በስተቀር በዚህ ጥናት ውስጥ "ሰዋስው" ሲባል የቋንቋ ስርዓትን እና ክፍሎችን የሚመለከት መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል።

## 2.2. የሰዋስው ትምህርት ታሪካዊ ዳራ

ሰዋስውን የማስተማር ተግባር ከቋንቋ ትምህርት ጋር ተያይዞ አሁን እስካለንበት ዘመን ቢዘልቅም የሚሰጠው ትኩረት በየዘመናቱ ሲለያይ ቆይቷል። ለዚህም ምክንያቱ በየዘመናቱ በቋንቋ ስነ-ትምህርት ላይ የሚቀርቡት ስነ-አቀራረቦች ፣ትውረቶች፣የማስተማር ዘዴዎች እንዲሁም ቋንቋን የማስተማር ዓላማዎች መለያየት ነው/Richards and Rodgers 1995:4/። ለምሳሌ ለምዕተ ዓመታት ያክል በባህላዊ ዘዴ ይቀርቡ በነበሩት በጥንታዊዎቹ የግሪክና የላቲን ቋንቋዎች ትምህርት ውስጥ የትምህርቱ ማዕከላዊ ጉዳይ ሰዋስው ነበር። በእነዚህ ቋንቋዎች ትምህርት ውስጥ ቋንቋን መማር ማለት የዚያን ቋንቋ ሰዋስው ተምሮ ማወቅ እና በቋንቋው የመፃፍ እና የማንበብ ችሎታን ማዳበር ማለት ነው። ይህ የሰዋስው እውቀትም

የልሂቅነት/elliteness/ ዋነኛ መለኪያ ተደርጎ ይወሰድ ነበር /Bygate,M.et.al 1994:2/:: በአንፃሩ እ.ኤ.አ በ1960ዎቹ አካባቢ "የቋንቋ ትምህርት ዋነኛ ዓላማ የተግባቦት ችሎታን ማደበር መሆን አለበት" የሚል አስተሳሰብ በስነ-ልሳን ባለሙያዎች ዘንድ መራመድ በመጀመሩ ለሰዋስው ትምህርት የሚሰጠው ትኩረት ነቀፌታ እየገጠመው መጣ ። ነገር ግን በዚሁ ዘመን መጨረሻ አካባቢ በ Noam Chomsky የቀረበውና "ቋንቋ በህግ የሚገዛ እና አፍልቆታዊ ነው" የሚለው ሀሳብ ምንም እንኳን በቋንቋ ትምህርቱ ላይ በቀጥታ ተፅዕኖ ባያሳድርም "ቋንቋ አፅምሮታዊ ባህሪ አለው" የሚለው አቀራረብ ተቀባይነት እንዲያገኝ በማድረጉ በዚያው የሰዋስውን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የመካተት አስፈላጊነት እንዲታሰብበት አድርጓል። በሌላ በኩል እ.ኤ.አ በ1960ዎቹ ሁለተኛ አጋሽ አካባቢ የሰዋስው ትምህርት ተነፍጎት የነበረውን ትኩረት እያገኘ እና በአፍ መፍቻም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ቦታ እየተሰጠው መጣ /Bygate,M.et.al 1994:5 ፣ Richards and Rodgers 1995:64/:: እንዲህ እንዲህ እያለ የተጓዘው የሰዋስው ትምህርት በአሁኑ ዘመን በመላው ዓለምም ሆነ በሀገራችን የቋንቋ ትምህርት ውስጥ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶት ይገኛል።

## 2.3. በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የሰዋስው ፋይዳ

አቀንቃኞችንና ተቀናቃኞችን እያፈራ እዘመናችን የደረሰው የሰዋስው ትምህርት አሁንም ቢሆን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተካቶ መቀጠሉ አስፈላጊ መሆኑን ምሁራን ይገልፃሉ። የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያክል Ur/1991:4/ "የቋንቋ እውቀታችንን ለማዳበር ሰዋስዋዊ ህጋጋትን ማወቅ ጠቀሜታ እንዳለው ጥርጥር የለውም። ምክንያቱም ቃላት እንዴት አንድ ላይ እንደሚቀናጁ ሳናውቅ ልንጠቀምባቸው አንችልምና" ይላሉ። መሰሉ/1994፡58/ ደግሞ የተለያዩ ምሁራንን በመጥቀስ የሰዋስው ትምህርትን አስፈላጊነት ከተግባቦት ጋር በማያያዝ እንደሚከተለው ያስረዳሉ።

> ቋንቋ በህግ የሚገዛ ነው። ህጉ ደግሞ ሰዋስው ነው። ስለዚህ ቋንቋን ከሰዋስው ለይቶ ማየት አይቻልም። ምክንያቱም ድምፆችና ምዕላዶች ስርዓት ይዘው ካልተዋቀሩ በስተቀር ትርጉም አዘል ቃላትን አይመሰርቱም። ቃላትም በስርዓት ካልተዋቀሩ በተወሰነ አውድ ውስጥ የሚኖራቸውን ፍቺ ያጣሉ። ስለዚህም ትክክለኛውን የአወቃቀር ስርዐት ተጠቅሞ ያለ እንቅፋት በቋንቋው ለመግባባት ህጉን ማወቅ ያስፈልጋል።

እነዚህ ምሁራን አፅንኦት የሰጡት ሰዋስውን ማወቅ ለውጤታማ ተግባቦት ያለውን ፋይዳ ነው። ነገር ግን ሰዋስውን የመማር ፋይዳ በዚህ ብቻ የሚገደብ ሳይሆን ሌሎች ጠቀሜታዎችም አሉት። ተጨማሪ ጠቀሜታዎቹን በተመለከተ ባዬ /2000፡ xxv/ ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር በማነፃፀር አቅርበውታል።

...የቋንቋን ትምህርት የሚመለከት አንድ ነገር ያለ ጥርጥር መናገር ይቻላል ። ይኸውም የአንድን ቋንቋ አጠቃቀም ብቻ ካወቀ ተማሪ ይልቅ፣ አጠቃቀሙን፣ ማለትም ክህሎቱን ከነስርዓቱ የተገነዘበ ተማሪ የተሻለ ክህሎትና ስነ-ልሳናዊ እውቀት ያለው መሆኑ ነው። ይህ እውቀትም ከቋንቋ አልፎ፣ ከቋንቋ ጋር ተያያዥነት ካላቸው እንደ ሳይኮሎጅ፣ ሶሲዮሎጅና ፍልስፍና ካሉ የትምህርት ዘርፎች ጋር ተማሪው በቀላሉ እንዲተዋወቅ ይረዳዋል። ቋንቋ አእምሮአዊ እንደሆነ ሁሉ ማህበራዊ ብሎም ባህላዊ ነውና።

ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች እና ማጠየቂያዎች በመነሳት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ያለውን ፋይዳ መረዳት ይቻላል። ሰዋስው የቋንቋ ስርዓት ወይም ህግ ነው ፤ ቋንቋ ደግሞ በህግ የሚገዛ ነው። ስለዚህም የቋንቋው ስርዓት በሚፈቅደው መልኩ እና በቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት ባለው መልኩ ለመግባባት የሚያስችል ችሎታን ተማሪው እንዲያዳብር ከተፈለገ በቋንቋ ትምህርቱ ውስጥ ሰዋስውን ማካተት አስፈላጊ ነው።

## 2.4. የሰዋስው ዘርፎች

ሰዋስው ከቋንቋ ጥናት ዓይነቶች ውስጥ አንዱ ሆኖ የቋንቋ ስርዓትን የሚመለከተው ክፍል እንደሆነ ቀደም ሲል ተገልጿል። ይህ የቋንቋ ጥናት አንድ ክፍል በበኩሉ ሌሎች የጥናት ዘርፎችን በስሩ አቅፎ እንደያዘ መረጃዎች ይጠቁማሉ/Chelker 1994፣ Prabhu 1987/:: የጥናት ዘርፎቹ አከፋፈል ወጥነት ያለው ሳይሆን በተለያዩ ምሁራን ዘንድ በተለያዩ መንገዶች የመከፋፈል ሁኔታ እንደሚታይበት አበበ (2000፡8) Crystal /1987/ን ጠቅሰው ያስረዳሉ። እንዲህም ሆኖ በአብዛኞቹ ምሁራን የሚጠቀሱት የሰዋው ጥናት ዘርፎች የሚከተሉት ናቸው።

- ጥንታዊ ሰዋስው
- ንድፈ ሀሳባዊ ሰዋስው
- ገላጭ ሰዋስው
- ትዕዛዛዊ ሰዋስው
- ማጣቀሻ ሰዋስው
- አመንጪ ሰዋስው
- አለማቀፋዊ ሰዋስው
- ተግባራዊ ሰዋስው
- ስነ ትምህርታዊ ሰዋስው ናቸው።

እነዚህ የጥናት ዘርፎች ትኩረት የሚያደርጉባቸው የየራሳቸው የሆኑ የጥናት አቅጣጫዎች እና ዓላማዎች አሏቸው ። ነገር ግን የዚህ ጥናት ትኩረት እያንዳንዱን የጥናት ዘርፍ ምን እንደሚመስል ማሳየት ሳይሆን ከዘርፎቹ አንዱ ከሆነው ከስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው ጋር የሚያያዝ በመሆኑ እሱን በዝርዝር ለማየት እንሞክራለን።

## 2.5. ስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው

ስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው ለሚለው እሳቤ መፈጠር ምክንያት የሆነው ጉዳይ 'በስነ-ልሳን ጥናት የሚደረስባቸው ግኝቶች በቋንቋ ትምህርት ውስጥ በቀጥታ ሊቀርቡ አይገባም' የሚለው የቋንቋ ምሁራን አስተያየት እንደሆነ Stern/1991:175/ ያስረዳሉ። እንደ ምሁራኑ አባባል በአንድ ቋንቋ ላይ በተደረገ ሳይንሳዊ ጥናት የተገኙ ግኝቶችን እንዳለ በትምህርትነት በክፍል ውስጥ ለማቅረብ መሞከር ተገቢ አይደለም። ከዚያ ይልቅ እንደ ቋንቋ ትምህርቱ ዓላማና ሁኔታ አጣጥሞና አመቻችቶ ማቅረብ ያስፈልጋል። ከዚህ አኳያ በተለያዩ የሰዋስው ጥናት ዘርፎች የተገኙ ግኝቶችን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ለማካተት ሲፈለግ ስነ-ልቦናዊ /Psychology/ እና ማህበረ-ስነ-ልሳናዊ /socio-linguistics/ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ሰዋስዋዊ ይዘቶችን ማጣጣም እና ማመቻቸት ያስፈልጋል። ይህ የሚደረግበት የሰዋስው ጥናት ዘርፍም ስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው ይባላል።

እዚህ ላይ በተለያዩ የሰዋስው ጥናት ዘርፎች የሚገኙ ግኝቶችን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ለማካተት ማጣጣም እና ማመቻቸት ለምን አስፈለገ? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ለዚህ ምክንያቱ ከላይ በ 2.4 ስር እንዳየነው እያንዳንዱ የሰዋስው ጥናት ዘርፍ የራሱ የሆኑ የጥናት አቅጣጫዎች እና ዓላማዎች ያሉት መሆኑ ነው። ለምሳሌ ያክል የተወሰኑትን ብንጠቅስ ንድፈ ሀሳባዊ ሰዋስው ስለ ቋንቋ አፈጣጠር፣ ባህርይ፣ ስርዓት ወዘተ ትውረታዊ እሳቤዎችን ይዘረዝራል። ገላጭ ሰዋስው ደግሞ የአንድን ቋንቋ ሰዋስዋዊ መዋቅር እየነጣጠለ ገለፃ ያደርጋል። ትዕዛዛዊ ሰዋስው በበኩሉ ትክክለኛ የሆኑ እና ያልሆኑ የቋንቋ አጠቃቀሞችን ለይቶ ለማስቀመጥ ይጥራል። አለማቀፋዊ ሰዋስውም እንዲሁ ቋንቋዎች ሁሉ የሚጋሩትን ወጥ የሆነ ስርዓት እና ባህሪ ለማሳየት ይሞክራል። ስለዚህም ከእነዚህ የተለያየ አቅጣጫ ካላቸው የጥናት ዘርፎች የተገኙ ሰዋስዋዊ መረጃዎችን እንደወረዱ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ማካተቱ ለተማሪዎቹም ሆነ ለመምህራኑ አስቸጋሪ ስለሚሆን ከቋንቋ ትምህርቱ ዓላማና ሁኔታ ጋር አጣጥሞና አመቻችቶ ማቅረብ አስፈላጊ ይሆናል።

በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የሚካተቱት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ከተለያዩ የሰዋስው ጥናት ዘርፎች እንደመገኘታቸው የማጣጣም እና የማመቻቸት ስራውም ከእነዚህ የጥናት ዘርፎች ጋር መነካካቱ የማይቀር ነው። ከዚህ ሁኔታም ስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው ዘርፈ ብዙ የሆነ የሰዋስው ጥናት ዘርፍ መሆኑን መረዳት ይቻላል ። ይህን አስመልክቶ አበበ /2000:16/ Little /1994/ን ጠቅሰው ሲያስረዱ "ስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው የተለያዩ የሰዋስው ዘርፎችን እሳቤዎች አካቶ የያዘ፣ የድቅልነት ባህሪ ያለው እና በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የቋንቋ መዋቅርን ከቋንቋ አገልግሎት ጋር በቅንጅት ለማቅረብ የሚሞክር ነው" ይላሉ። ከድረ ገጽ የተገኘ መረጃ ደግሞ

ስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው የሚለው ጽንሰ ሃሳብ የአሻሚነት ባህሪ ያለው መሆኑን በመጠቆም ጽንሰ ሀሳቡ በተለምዶ ሶስት ጉዳዮችን እንደሚያመለክት ይገልፃል። እነዚህም፡-

1. ስነ-ትምህርታዊ ሂደት፡- የታላሚው ቋንቋ ሰዋስዋዊ ይዘቶች በቋንቋ ትምህርቱ ስነ-ዘዴ ውስጥ በግልጽ ተካተው የመቅረባቸውን ሁኔታ ይመለከታል።
2. ስነ-ትምህርታዊ ይዘት፡- ስለታላሚው ቋንቋ ስርዓት ማጣቀሻ የሚሆኑ የተለያዩ ሰዋስዋዊ መረጃዎችን ይመለታል።
3. የስነ-ትምህርታዊ ሂደት እና ይዘት ቅንጅት ናቸው /http.www.pedagogical grammar/።

ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች መረዳት እንደሚቻለው ስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው ከተለያዩ የቋንቋ ጥናቶች የተገኙ ሰዋስዋዊ መረጃዎችን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ አካቶ ለማቅረብ ጥረት ያደርጋል። በዚህ ሂደትም የትምህርቱ ሂደት በምን መልኩ መከናወን እንዳለበት ፣ በትምህርቱ ውስጥ ምን ምን ሰዋስዋዊ ይዘቶች መካተት እንዳለባቸው እና እነዚህ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ከትምህርቱ ሂደት ጋር እንዴት ተቀናጅተው መቅረብ እንዳለባቸው አቅጣጫ ይጠቁማል።

በስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው አማካኝነት እነዚህ ተግባራት በሚከናወኑበት ሂደት ልንከተላቸው የሚገቡ ቁም ነገሮች አሉ። ከእነዚህም አንዱ "በአንድ የስነ-ልሳን ንድፈ ሀሳብ ላይ ብቻ አለመወሰን" የሚል ነው /Stern 1991:175/። ቀደም ሲል እንዳየነው ስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው ዘርፈ ብዙ በመሆኑ ከተለያዩ የቋንቋ ጥናት ዘርፎች ጋር ይገናኛል። ነገር ግን ግንኙነቱ በዚህ ብቻ አይገታም። ለቋንቋ ትምህርት አስተዋፆኦ ሊያበረክቱ ከሚችሉ ሌሎች የጥናት መስኮች ጋርም ይገናኛል። ለምሳሌ ስለ መማር ጽንሰ ሀሳብ መረጃ ለማግኘት ከስነ-ልቦና ጋር፣ ስለ ተማሪዎች ማህበረስነ-ልሳናዊ ዳራ ወይም ልዩነት ለማወቅ ከማህበራዊ ስነ-ልሳን ጋር፣እንዲሁም ስለ ትምህርት ሂደት ለመረዳት ከስነ-ትምህርት ጋር መገናኘት አለበት። ስለዚህም ስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው እራሱን በአንድ በተወሰነ የስነ-ልሳን ንድፈ ሀሳብ የሚያጥር ሳይሆን ከሌሎች ለቋንቋ ትምህርት ጠቀሜታ ካላቸው ዘርፎች ጋር ግንኙነት ያለው መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። በዚህም መሰረት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ተመርጠው ለትምህርትነት የሚቀርቡት እነዚህን ጉዳዮች ግምት ውስጥ ባስገባ አሰራር መሆን አለበት።

ሌላው በስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው የክንውን ሂደት ልንፈፅመው የሚገባ ተግባር መረጃዎችን እና ጽንሰ ሀሳቦችን መግለጽ እና ማነፃፀር ነው። መረጃዎችን ቅደም ተከተል ማስያዝም ሌላው ተግባር ነው። መረጃዎች ከቋንቋ ክሂሎች አኳያ (ማለትም ማዳመጥ፣መናገር፣ማንበብና መፃፍ) እና ከተማሪዎች ውጤታማነት ደረጃ(ማለትም ለጀማሪ፣ለመካከለኛ እና ለከፍተኛ) አኳያ ቅደም ተከተል ተሰጥቷቸው ሊደራጁ ይችላሉ። የምዘና ስርዓትን ማስቀመጥም በሂደቱ ውስጥ

የሚናወን ተግባር ነው። በእነዚህ ተግባራት ክንውን ወቅት ሁሌም ልብ ልንላቸው የሚገቡ ሁለት ጉዳዮች አሉ። እነዚህም የቋንቋ ትምህርቱ ዓላማና የቋንቋ ትምህርቱ የሚሰጥበት አውድ ናቸው።

ከዚህ በላይ በዝርዝር ያየነውን የስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው አተገባበር ሂደት Stern(1991:176)፥ Corder/1973፡156/ ን ጠቅሰው በሚከተለው መልኩ አጠቃለው አስቀምጠውታል።

| ተግባር /Application/ | ንድፈ ሀሳብ /Theory/ | ሂደት /Process/ | መረጃ /Data/ |
|---|---|---|---|
| 1ኛ/ ደረጃ | ስነ-ልሳን እና ማህበራዊ ስነ-ልሳን | ገለፃ → | Language Utterances ↓ |
| 2ኛ/ ደረጃ | ስነ-ልሳን እና ማህበራዊ ስነ-ልሳን | ማወዳደር እና መምረጥ → | Description of Languages ↓ |
| 3ኛ/ ደረጃ | ስነ-ልሳን ፣ ማህበራዊ ስነ-ልሳን እና ስነ-ልቦናዊ ስነ-ልሳን | ማደራጀት እና → | የመርሃ ትምህርት ይዘት ↓ የማስተማሪያ መሣሪያዎች |

ሰንጠረዥ 1. በስነ-ልሳን አተገባበር ላይ የኮርደር እይታ( በ stern 1991:176 እንደተጠቀሰው)።

## 2.6. በትምህርትነት የሚቀርቡ ሰዋስዋዊ ይዘቶች

ከተለያዩ የስነ-ልሳን ጥናት ዘርፎች የተገኙ ሰዋስዋዊ መረጃዎች ወይም ይዘቶች በስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው አማካኝነት ከስነ-ትምህርት ጋር ግንኙነት ካላቸው ሌሎች የጥናት ዘርፎች ከሚገኙ መረጃዎች ጋር በመቀናጀትና በመጣጣም ለትምህርት አገልግሎት ሊውሉ እንደሚችሉ ቀደም ሲል ገልፀናል።ከዚህ ቀጥሎ የሚነሳው ጥያቄ በትምህርትነት የሚቀርቡት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ምንድን ናቸው? የሚል ይሆናል። በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተካተው ሊቀርቡ የሚችሉ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ከአነስተኛዎቹ የቋንቋ ቅንጣት ድምፆች አንስቶ ውስብስብ እስከሆነው የቋንቋ መዋቅር-ዓረፍተ ነገር የሚደርሱ ናቸው/አልፋ ዩኒቨርስቲ 2006፡122/። እነዚህም የሚከተሉት ናቸው።

### 2.6.1. የቋንቋ ድምፆች

ማንኛውም ቋንቋ መሰረቱ የንግግር ድምጽ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ያለድምጽ የሚከወን ቋንቋ ባለመኖሩ የመዋቅሩ ጥናት መነሻ ድምጽ ይሆናል፡፡ የቋንቋ ድምጾች ከአፈጣጠራቸው ሁኔታ እና ከሚፈጠሩበት የአንደበት ክፍል አኳያ ተናጥላዊ ባሕሪይ የሚያሳዩ ሲሆን ከሌሎቹ ድምጾች ጋር ሲቀናጁ ደግሞ ድምፀ ልሳናዊ ሂደት፣ መጥበቅና መላላት፣ ንበት የመሳሰሉ ቅንጅታዊ ባሕርያትን ያሳያሉ፡፡ ስለዚህ በቋንቋ ውስጥ የንግግር ድምፆችን ተናጠላዊ እና ቅንጅታዊ ባህሪ መመርመር የሰዋስው ትምህርት አንዱ ትኩረት ነው፡፡

### 2.6.2. ምዕላዶች

በሰዋስው ትምህርት መካተት ካለባቸው ነጥቦች አንዱ ምዕላድ ነው፡፡ ምዕላድ ፍቺ ያለው እና ወደ ሌሎች ፍቺ ወዳላቸው አነስተኛ የቋንቋ አካላት ሊሸነሸን የማይችል የቋንቋ አሀድ ነው፡፡ ምዕላዶችና ቃላት አንድነትም ልዩነትም አላቸው/ባዬ 2000:74/፡፡ አንድነታቸውን ስናይ በመጀመሪያ ቃላት እንደ ምዕላድ ትርጉም አዘል ስለሆኑ ይመሳሰላሉ፡፡ ሁለተኛም እራሳቸውን ችለው መቆም የሚችሉ ምዕላዶች ስላሉና ቃላትም ራሳቸውን ችለው ስለሚቆሙ ይመሳሰላሉ ልዩነታቸውን በተመለከተ ደግሞ አንደኛ ቃላት በውስጣቸው ከአንድ በላይ ጥገኛ ምዕላዶችን ሊይዙ ይችላሉ፡፡ ፍቺ አዘል ወደ ሆኑ አነስተኛ ክፍሎችም ሊሸነሸኑ ይችላሉ ምዕላዶች ግን ይህንን ስለማያደርጉ ይለያያሉ፡፡ ሁለተኛም ቃላት ከቃላት ክፍሎች ውስጥ በአንዱ ሊመደቡ ሲችሉ ምዕላዶች ግን (በተለይ ጥገኛዎቹ) ላይመደቡ ይችላሉ፡፡ የሰዋስው ትምህርቱም የምዕላዶችን ባህሪ እና አገልጋሎት ይመረምራል፡፡

### 2.6.3 ቃላት

ቃል ትርጉም አልባ የሆኑ ድምጾች ስርዓታዊ ቅንጅት ወይም የምዕላዶች ቅንጅት ወይም የቃላት ቅንጅት ውጤት ሊሆን ይችላል፡፡ የአንድ ቋንቋ ቃላት በተለያዩ ክፍሎች ሊመደቡ ይችላሉ፡፡ የተለያዩ ቅጥያዎችን በመውሰድም ሊረቡ ወይም ሊመሰረቱ ይችላሉ፡፡ ስለዚህም የቃላትን አፈጣጠር እና አከፋፈል መመርመር የሰዋስው ትምህርት ትኩረት ነው፡፡

### 2.6.4. ሐረጋት

ሀረግ በቃል ላይ የተመሰረተ የመዋቅር አይነት ሲሆን ከአንድ ቃል ወይም ከአንድ በላይ ከሆኑ ቃላት ቅንጅት ሊፈጠር ይችላል /ባዬ 2000:237/፡፡ በሀረግ ውስጥ አይቀሬው አካል መሪው

ነው። የሰዋስው ትምህርትም የሀረጋትን አመሰራረትና የሚኖራቸውን ሰዋስዋዊ አገልግሎት ይመረምራል።

### 2.6.5. ዓረፍተ ነገሮች፡-

ዓረፍተ ነገር ከሀረግ የሚሰፋ የመዋቅር ዓይነት ነው በውስጡም ሌሎች ሀረጉችን ይይዛል። ዓረፍተ ነገሮች በተራክቦ /Interaction/ ሂደት ለተለያዩ አገልግሎቶች ሊውሉ ይችላሉ። የሰዋስው ትምህርትም ዓረፍተ ነገሮችን ከመዋቅራቸው እና ከአገልግሎታቸው አኳያ ይመረምራል።

## 2.7. የሰዋስው ማስተማሪያ ይዘቶችና ዘዴዎች ሲመረጡ ከግንዛቤ መግባት ያለባቸው ጉዳዮች

እንደማንኛውም የትምህርት ይዘት ሁሉ የሰዋስው ማስተማሪያ ይዘቶችና ዘዴዎች ሲመረጡ የተለያዩ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። ይህንን አስመልክቶ መስሉ /1994፡ 60/ የተለያዩ ምሁራንን በመጥቀስ በቋንቋ ትምህርት ብሎም በሰዋስው ትምህርት ይዘቶችና ዘዴዎች መረጣ ወቅት የሚከተሉትን ነጥቦች ልብ ማለት እንደሚገባ ይመክራሉ።

1. **የተማሪዎቹ ዕድሜ፡-** ሕፃናትና ትልልቅ ተማሪዎች በሰዋስው ትምህርት አቀባበላቸው ይለያያሉ። ሕፃናት የረቀቀ ሃሳብን የመቀበል ችሎታቸው አነስተኛ ነው። ተጠቃሚ የሚሆኑት በቅርጽ ላይ ከሚደረግ ትኩረት ነው። ስለዚህም ትምህርቱ ቀላልና ያልረቀቀ ሆኖ መቅረብ ይኖርበታል። በአንፃሩ አዋቂዎች የአስተሳሰብ ችሎታቸው የዳበረ ነው። የረቀቀ ሃሳብን ለመገንዘብ ይችላሉ። በዚህ ችሎታ ተጠቅመው ሰዋስውን ለተግባቦታዊ አገልግሎት እንዲያውሉት ረቀቅ ብሎ መቅረብ ይኖርበታል።
2. **የችሎታ ደረጃ፡-** የተማሪዎች የችሎታ ደረጃ ትምህርት ላይ እንደቆዩበት ጊዜ መጠን ይለያያል። የጀማሪዎች የችሎታ ደረጃ አነስተኛ ነው። ስለዚህም ብዙ የሰዋስው ትምህርት እንዲማሩ መገደድ የለባቸውም። ምክንያቱም በቋንቋው እንደልብ የመጠቀም ችሎታቸውን ይገድበዋል። በዚህ ደረጃ ትምህርቱ መቅረብ ያለበት በጥቂት በጥቂቱ ከትምህርቱ ጋር እንዲተዋወቁ ያህል እንጂ በስፋት እንዲለማመዱበት መሆን የለበትም። የችሎታ ደረጃቸው ለዳበረ ተማሪዎችም ቢሆን የትምህርቱ ረቂቅነት እንደየቋንቋ ችሎታቸው መጠን መለያየት ይኖርበታል። ተማሪዎቹ ችሎታቸው ያልዳበረ ኢ-አፍ-ፊት ተማሪዎች ከሆኑ ለሰዋስዋዊ ትንታኔ የሚሰጥ ትኩረት የቋንቋቸውን አፍስሶት ሊያግደው ይችላል። ስለዚህም ትምህርቱ የተማሪዎቹን ችሎታ የመጠነ መሆን ይኖርበታል።
3. **የትምህርት ዳራ፡-** የመደበኛ ትምህርት ዳራቸው ዝቅተኛ የሆነ ተማሪዎች ውስብስብ ሃሳቦችን ለመቀበል የሚኖራቸው የአእምሮ ዝግጅት አነስተኛ ነው። ስለዚህም ሰዋስዋዊ ስያሜዎችንና ትንታኔዎችን በቀላሉ ለመያዝ ይቸገራሉ። ከፍ ያለ የትምህርት ደረጃ ላይ

ያሉ ተማሪዎች አእምሮ ደግም ሰዋስው ተኮር የሆነን ትምህርት ለመቀበል ዝግጁ ነው። ስለዚህም ትምህርቱ ሰፋ እና ረቀቅ ብሎ መቅረብ ይችላል። ይህም ፍሰት ደረጃ ላይ ባለው ቋንቋቸው ላይ የሚፈጽሟቸውን ሰዋስዋዊ ስህተቶች እንዲያርሙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።

4. **እንዲዳብር የሚፈለገው የቋንቋ ክሂል፡-** በሁሉም የቋንቋ ክሂሎች ሲጠቀሙ መልዕክቱን ሳይዛባ ለማስተላለፍ ሰዋስዋዊ ትክክለኛነት ያስፈልጋል። ነገር ግን ይህ አስፈላጊነት በተለያዩ ክሂሎች ዘንድ እኩል አይደለም። ለምሳሌ በጽሁፍ ክሂል ወጥነት እና ሰዋስዋዊ ትክክለኛነት በጣም አስፈላጊዎች ናቸው። ከዚህ አንፃር የሰዋስው ትምህርቱ ከሌሎቹ ይልቅ የጽሁፍ ችሎታን ለማዳበር የጐላ ጠቀሜታ ይኖረዋል። ስለዚህም በትምህርቱ ሂደት በጣም የሚፈለገው የተማሪዎቹን የጽሁፍ ክሂል ማዳበር ከሆነ ለሰዋስው ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል ማለት ነው።

## 2.8. የሰዋስው ትምህርት ስነ-አቀራረቦች እና ዘዴዎች

የሰዋስው ትምህርት ስነ-አቀራረቦች እና ዘዴዎች ከቋንቋ ትምህርት ስነ-አቀራረቦችና ዘዴዎች የሚመነጩ ናቸው። እነሱን በዝርዝር ከማየታችን በፊት የእነሱ ምንጭ የሆኑትን የቋንቋ ትምህርት ስነ-አቀራረቦችን እና ዘዴዎችን ማየት ያስፈልጋል።

የቋንቋ ትምህርት ስነ-አቀራረቦች የሚባሉት የቋንቋ ተፈጥሮን እና ቋንቋ መማርን አስመልክቶ በምሁራን የተሰነዘሩ አተያዮች ወይም ትንታኔዎች ሲሆኑ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች የሚባሉት ደግሞ በተወሰኑ ስነ-አቀራረቦች ላይ ተመስርተው የሚቀነባበሩ የቋንቋ ማስተማሪያ አውዶች መሆናቸውን መሰሉ /1994:7/ የተለያዩ ምሁራንን በመጥቀስ ይገልፃሉ። እነዚህ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች የማስተማሪያ መሳሪያዎችን እና የትምህርት ይዘቶችን መምረጥን ወይም ማዘጋጀትን እና የትምህርት ይዘቶች ወደ ተማሪው የሚተላለፉባቸውን መንገዶች መግለጽን ያካትታሉ። በእነዚህ ዘዴዎች አማካይነት የቋንቋ ትምህርት ለተማሪዎች ሲቀርብ በክፍል ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት አሉ። እነዚህም የቋንቋ ማስተማሪያ ስልቶች ይባላሉ። የቋንቋ ማስተማሪያ ስልቶች ዝርዝር አላማዎችን ከግብ ለማድረስ በስነ-አቀራረቡና በማስተማሪያ ዘዴው መሰረት በክፍል ውስጥ የሚተገበሩ የትምህርት ክንውኖች ናቸው።

አሁን ደግሞ የዚህ ጥናት ትኩረት የሆኑትን የሰዋስው ትምህርት ስነ-አቀራረቦችን እና ዘዴዎችን በዝርዝር እንመልከት። የሰዋስው ትምህርት በምን መልኩ ለተማሪዎች ይቅረብ? በሚለው ላይ ምሁራን የተለያዩ አስተያየቶችን ይሰነዝራሉ። ለምሳሌ ያክል Harmer /1987:3/ ሰዋስውን የማስተማሪያ ሁለት መንገዶች እንዳሉ ይገልፃሉ። እነዚህም ሰዋስውን በስውር የማተማር ስልትና ሰዋስውን በግልጽ የማስተማር ስልት ናቸው። ሰዋስውን በስውር

በማስተማር ስልት ለተማሪዎቹ የሰዋስዋዊ ህግጋትና እውነታዎች አይነገሯቸውም፡፡ ነገር ግን በትምህርቱ ሂደት በተለያዩ የቋንቋው ክፍሎች ላይ (ለምሳሌ መረጃ በመለዋወጥ፣ በንባብ ጊዜ) ልምምድ ሲያደርጉ ሰዋስውን ይገለገሉበታል፡፡ ሰዋስውን በግልጽ በማስተማር ስልት ግን መምህሩ በቋንቋ ተስተምህሮ ጊዜ የሰዋስው ህጎችን በማቅረብ ለተማሪዎቹ ገለፃ ያደርግላቸዋል፡፡ Celce-Murcia/1991፡283/ ደግሞ ሰዋስውን ለማስተማር ሁለት ዓይነት አቀራረብ መጠቀም እንደሚቻል ያስረዳሉ፡፡ እነዚህም ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር (Deductive) እና ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ (Inductive) ናቸው፡፡ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ማለት ለተማሪዎቹ የተወሰነ ሰዋስዋዊ ህግ ይነገራቸውና ያን ህግ በተለያዩ የቋንቋ አጠቃቀሞች ውስጥ እያስገቡ እንዲለማመዱበትና ከራሳቸው ጋር እንዲያዋህዱት የሚደረግበት አቀራረብ ነው፡፡ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ማለት ደግሞ ተማሪዎቹ በቋንቋው የተለያዩ ቅርፆች እየተለማመዱ ቀስ በቀስ በሂደት በራሳቸው ሰዋስዋዊ ህጉን እንዲለዩ የሚደረግበት አቀራረብ ነው፡፡ ሌሎች ምሁራንም የየራሳቸውን ሀሳብ ሰንዝረዋል፡፡

ከላይ ከቀረቡት ገለፃዎች ሁለት ዓይነት የሰዋስው ትምህርት ስነ-አቀራረቦች እንዳሉ እንረዳለን፡፡ እነዚህም ውጤት ተኮር (ትኩረቱን ሰዋስውን በቀጥታ ማስተማር ላይ ያደረገ) እና ተግባቦታዊ ወይም ክሂል ተኮር (ሌሎች የቋንቋ ክሂሎችን በማስተማር በሂደት ወደ ሰዋስዋዊ ህግጋት ለመድረስ የሚሞክር) ሲሆኑ በየአቀራረቦቹ ውስጥም የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችና ስልቶች ይገኛሉ፡፡ እነዚህን አቀራረቦች ተጠቅሞ ሰዋስውን በውጤታማነት ለማስተማር ይቻል ዘንድ የእያንዳንዱን አቀራረብ ዝርዝር ባህሪ፣ የማስተማሪያ ዘዴ እና የማስተማሪያ ስልት እንዲሁም ጠንካራና ደካማ ጎኖች ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

### 2.8.1. ውጤት ተኮር አቀራረብ

ውጤት ተኮር አቀራረብ ሰዋስውን በቀጥታ ለተማሪዎች አቅርቦ በማስተማር ላይ የሚያተኩር ስነ-አቀራረብ ነው፡፡ በዚህ አቀራረብ መምህሩ ለማስተማሪያነት በቀረበው ሰዋስዋዊ ይዘት ላይ ማብራሪያ እየሰጠ ያስተምራል፡፡ አፈፃፀሙም የሚከተሉትን ደረጃዎች ይከተላል፡፡

1. መምህሩ በጥቁር ሰሌዳው ላይ ምሳሌ ይሰጣል፣
2. ምሳሌውን እየተነተነ ህጉን ያብራራል፣
3. ተማሪዎቹ በተማሩት መሰረት ህጉን በቃልና በጽሑፍ እንዲተነትኑ ያደርጋል፡፡

ይህ አቀራረብ በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ሂደት በተማሪዎቹ አፍ መፍቻና በታላሚው ቋንቋዎች መካከል ላሉ ልዩነቶች ትኩረት ይሰጣል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ አቀራረቡ በተስፋፋበት ዘመን 'በሁለቱ ቋንቋዎች መካከል ያሉ ልዩነቶች ለመዳውን ያጓትታሉ' ተብሎ ይታመን ስለነበረ ነው፡፡ ተማሪዎቹ ትምህርቱን መረዳት አለመረዳታቸው የሚታወቀውም የቀረበላቸውን መልመጃ

መተንተን በመቻላቸውና ባለመቻላቸው ነው። ቅርፁን ለተግባቦታዊ አገልግሎት ማዋል አለማዋላቸው ግን ከግንዛቤ አይገባም። ውጤት ተኮር አቀራረብ ሰዋስውን ለማስተማር ፈጣን ነው። አቀራረቡም ለመምህሩ ይቀላል። ነገር ግን ሰዋስዋዊ ቅርፆቹ ለሚሸከሙት ፍች እና አጠቃቀማቸው የሚሰጠው ትኩረት አነስተኛ በመሆኑ የተግባቦት ችሎታን ለማዳበር ምቹ ሁኔታን አይፈጥርም። ስለዚህም አብዛኛውን ጊዜ ለማስተማሪያነት ያለው ተመራጭነት አነስተኛ ነው። በዚህ አቀራረብ ስር ከሚመደቡ ሁለተኛ ቋንቋን የማስተማሪያ ዘዴዎች ውስጥ የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል።

#### 2.8.1.1 ሰዋስው ወትርጉም ዘዴ/Grammar Translation Method/

ሰዋስው ወትርጉም ዘዴ የመጀመሪያው ሁለተኛ ቋንቋን ማስተማሪያ ዘዴ ነው። ሀረጐችንና ዓረፍተ ነገሮችን በቃል ለቃል ፍች ከታላሚው ቋንቋ ወደ ተማሪዎች አፍ መፍቻ ቋንቋ በመተርጐምና ሰዋስዋዊ ትንታኔን በመስጠት ይከናወናል። የትምህርቱ ግብ ተማሪዎቹን በታላሚው ቋንቋ የተፃፉ ስነ ፅሑፎችን ማንበብ ማስቻል ነው።

ይህ ዘዴ በሚከተሉት ሁለት መሠረተ ሀሣቦች ላይ የተመሠረተ ነው።

1. ሁለተኛ ቋንቋን በቀላሉ መማር የሚቻለው በትርጉም አማካይነት ነው።
2. ሰዋስው የቋንቋ መሠረት ነው።

የመማር ማስተማሩ ሂደት ደረጃ በደረጃ ቃላትን፣ ሀረጐችንና ዓረፍተ ነገሮችን ፍች በመስጠት ይከናወናል። መምህሩ የእያንዳንዱን አዲስ ቃል ፍች ወደ ተማሪዎቹ አፍ መፍቻ ቋንቋ በመተርጎም ያቀርባል። ሰዋስዋዊ ህግጋትንም እየተነተነ ያስረዳል።

በዚህ ማስተማሪያ ስልት ላይ የሚከተሉት ዋና ዋና ባህርያት ይንፀባረቃሉ።

1. ትምህርቱ የሚጀምረው ከቃል ነው።
2. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ ጎልቶ ይታያል።
3. በሰዋስዋዊ ትንታኔና በቃላት ፍች ላይ ያተኮረ ነው።

#### 2.8.1.2 ቀጥተኛ ዘዴ/Direct Method/

ቀጥተኛ ዘዴ "የቋንቋ መሠረቱ ንግግር ነው" በሚል ፍልስፍና ላይ የተመሠረተና ለንግግር ትኩረት የሚሰጥ የሁለተኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ ነው። ቋንቋን ከድምፅ አንስቶ ደረጃ በደረጃ የሚያድግ ሰዋስዋዊ መዋቅር አድርጎ ይመለከተዋል። ዋነኛ አላማዎቹም ተማሪዎቹን በታላሚው ቋንቋ ንግግር ማስቻል፣ ቋንቋን ለእለታዊ መግባቢያ መጠቀም ማስቻል፣ ከተግባሩ ተነስተው ሰዋስውን እንዲያውቁ ማድረግ፣ ቃላትን በትክክል ማፍለቅ ማስቻል የሚሉት ናቸው።

አላማዎቹን ከግብ ለማድረስ ተማሪዎቹን ለጥያቄና መልስ የሚያነሳሱና የዘወትር ቃላትን የያዙ ይዘቶች ይመረጣሉ። ተማሪዎቹ ሲጠይቁም ሆነ ሲመልሱ ሙሉ አረፍተ ነገር መናገር ይጠበቅባቸዋል። ዘዴው ለንግግር ትኩረት ስለሚሰጥ ተማሪዎቹ እርስ በእርስም ሆነ ከመምህሩ ጋር ሀሣብ ለመለዋወጥ እድል ያገኛሉ። በትምህርቱ ሂደት የአፍ መፍቻ ቋንቋን መጠቀምም የተከለከለ በመሆኑ በታላሚው ቋንቋ የመገልገል እድልን ያሰፋል።

### 2.8.1.3 ንባባዊ ዘዴ/Reading Metod/

ንባባዊ ዘዴ ግቡን አንብቦ በመረዳት ላይ ብቻ ያደረገ የሁለተኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ ነው። ስለዚህም በትምህርቱ ሂደት ማንበብ እንጂ መናገር አስፈላጊነቱ እምብዛም ነው የሚል መሠረተ ሀሣብ ስላለው ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋቸው የሚናገሩበት አጋጣሚ አነስተኛ ነው።

በዚህ ዘዴ ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች በጣም አስፈላጊው ንባብ ነው። ንባብ ለንግግር ለፅሁፈትና ለንግግርም መሠረት ነው። በዚህ መሠረት እንደየተማሪዎቹ የብስለት ደረጃ ሰፋና ጠለቅ ያለ የትምህርት ይዘት ተመርጦ እንዲያነቡ ይደረጋል።

## 2.8.2. ተግባቦታዊ (ክሂል ተኮር) አቀራረብ

ተግባቦታዊ ቋንቋን የማስተር አቀራረብ ቀደም ሲል በቋንቋ ስነ-ትምህርት ላይ ሲስነዘሩ የነበሩ አመለካከቶችን በመተካት እ.ኤ.አ በ1970ዎቹ መጀመሪያ አካባቢ የተከሰተ ሲሆን በዘመናችን በሰፊው ተቀባይነትን ያገኘ ሀሳብ ነው /Brown 2000:245፤ Celce-Murcia 1991:8፤ Richards and Rodgers 1995፤65 እና Stern 1991:111/። የዚህ አቀራረብ ዋነኛ አመለካከት 'የቋንቋ ትምህርት ቀዳሚ አላማ የተግባቦት ችሎታን ማዳበር መሆን አለበት' የሚል ነው። ለዚህም መነሻው 'የቋንቋ ዋነኛ አገልግሎት ማግባባት ስለሆነ የቋንቋ ትምህርቱም ትኩረቱን ተግባቦትን በመፍጠር ላይ ማድረግ አለበት' የሚለው ሀሳብ ነው። ይህ ሀሳብም አቀራረቡ ተቀባይነትን እንዲያገኝ ያስቻለ አሳማኝ ነጥብ ነው።

እንደሚታወቀው በአንደኛም ሆነ በሁለተኛ ደረጃ ባሉ የክፍል ደረጃዎች የሚገኙ ተማሪዎች አንድን ቋንቋ እንዲማሩ የሚደረገው በዚያ ቋንቋ በፅሁፍም ሆነ በንግግር በተገቢው ሁኔታ ሃሳባቸውን መግለፅ እንዲችሉ ለማድረግ ነው። ይህን ማምጣት የሚቻለውም ከአሁን ቀደም እንደነበሩት የቋንቋ ትምህርት አቀራረቦች ተማሪዎቹ የቋንቋውን ሰዋስው እንዲያጠኑ እና እንዲተነትኑ በማድረግ ብቻ ሳይሆን የተግባቦት ችሎታቸውን ሊያሳድጉ የሚችሉ ተግባራትን በማከናወን ነው። ስለዚህም ለሰዋስው ብቻ ሳይሆን በቋንቋ አማካኝነት ለሚተላለፈው ፍች እና ለማህበራዊ አጠቃቀም ትኩረት በመስጠት ትምህርቱን ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ ማቅረብ ያስፈልጋል።

ከአሁን ቀደም በነበሩት የቋንቋ ትምህርት አቀራረቦች እና ዘዴዎች ላይ ከሚቀርቡት ትችቶች አንዱ ተማሪው ስለ ታላሚው ቋንቋ ሰዋስው እንዲያውቅ እንጂ በቋንቋው እንዲገለገልበት የሚያስችሉ አይደሉም የሚል ነው። በእነዚህ አቀራረቦች እና ዘዴዎች የቋንቋ ትምህርቱ ያተኩር የነበረው ተማሪዎች የዚያን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ህግጋት እንዲያጠኑ እና እንዲተነትኑ በማድረግ ላይ ነበር። ይህ ተግባር ደግሞ ከክፍል ውጭ ያለውን እውናዊ የቋንቋ አገልግሎት ከግምት ውስጥ ስለማያስገባ ተማሪዎቹ ከዚህ አኳያ ችግር ይገጥማቸዋል። በተለይ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የቋንቋውን ህግጋት ቢያጠኑ እና መዋቅሮቹን ቢተነትኑም በእውናዊ ዓለም፣ የህግጋት እና የመዋቅር እውቀታቸውን ተጠቅመው ከቋንቋው ተናጋሪ ህብረተሰብ ጋር የመግባባት ሁኔታቸው ደካማ ይሆናል። ለዚህም ምክንያቱ የገሀዱ ዓለም ተግባቦት ከቋንቋ ስርዓት (ሰዋስው) ባለፈ የራሱ የሆኑ ባህርያት ስላሉት እና እነዚህም በቋንቋ ትምህርቱ ውስጥ ባለመካተታቸው ነው።

የገሀዱ ዓለም ተግባቦት ትኩረቱን በአብዛኛው ከሰዋስዋዊ ትክክለኛነት ይልቅ በፍች ላይ ማለትም መልዕክትን በአግባቡ በማስተላለፍ ላይ ያደርጋል። እንዲሁም እንደየ አውዱ ማለትም በሰዎች መካከል በርካታ ልዩነቶች የሚለያይ የቋንቋ አጠቃቀም ገጽታን ያሳያል። ማለትም በሰዎች መካከል በርካታ ልዩነቶች ስላሉ (ምሳሌ፡- ፆታ፣ ዕድሜ፣ የቅርበት መጠን፣ የስልጣን ደረጃ፣ የምጣኔ ሀብት ደረጃ፣ ወዘተ) በመካከላቸው የሚደረገው ተግባቦትም እነዚህን ልዩነቶች ተከትሎ የተለያዩ የቋንቋ አጠቃቀም ገጽታዎችን ያሳያል። በተጨማሪም ሰዋስዋዊ ትክክለኛነት ሁልጊዜም የአጠቃቀም ትክክለኛነትን ላያሳይ ይችላል። በሰዋስው ስህተት ሆነው በአጠቃቀም ትክክል የሆኑ የቋንቋ ገጽታዎች ይኖራሉ።

የቋንቋ ክሂሎች እርስ በርሳቸው ተቀናጅተው መገኘታቸውም ሌላው የገሀዱ ዓለም ተግባቦት ባህሪ ነው። አንድ ሰው ተናጋሪ ወይም አድማጭ ብቻ አይሆንም። ይናገራል፤ ሌላው ሲናገር ያዳምጣል፤ መልዕክቱን ለመረዳት ይሞክራል፤ ስህተት የመሰለውን ይቃወማል፤ ያልገባውን ይጠይቃል፤ ትክክል ነው ብሎ ያመነበት ሀሳብ ተቀባይነት እንዲያገኝ ጥረት ያደርጋል።

የተግባቦታዊ አቀራረብ አቀንቃኞች እንደሚሉት ከእነሱ በፊት የነበሩት የቋንቋ ትምህርት አቀራረቦችና ዘዴዎች እነዚህን የሀገዱ ዓለም የተግባቦት ገጽታዎች ግምት ውስጥ ያስገቡ አልነበሩም። ትኩረት ሰጥተዋል ቢባል እንኳ ግልጽ በሆነ ሁኔታ የተቀመጠ ሳይሆን ማዳመጥ እና መናገርን እንደ ቋንቋ ክሂልነታቸው በጥቅል የሚያነሱ ነበሩ /Stem 1991:259/። ነገር ግን ተማሪው በተፈጥሮአዊ አውድ ውስጥ ከቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ ጋር በብቃት መግባባት የሚያስችለውን እውቀትና ችሎታ ለማዳበር ከተፈለገ እነዚህ የቋንቋ አጠቃቀም ገጽታዎች በትምህርቱ ውስጥ ተካተው መቅረብ አለባቸው። የሰዋስው ትምህርት ዓላማም በዚሁ ማዕቀፍ

ስር የሚጠቃለል በመሆኑ የተማሪውን የተግባቦት ችሎታ ከማዳበር አኳያ ተቃኝቶ መቅረብ አለበት።

በዚህ አቀራረብ መሠረት ለማስተማሪያነት የሚቀርቡት የቋንቋ ይዘቶች እውነተኛ እና የገሀዱን ዓለም የሚያንፀባርቁ መሆን አለባቸው። የቋንቋ ክሂሎችም ተነጣጥለው ሳይሆን እርስ በርሳቸው ተቀናጅተው መቅረብ አለባቸው። ተማሪዎቹም በአብዛኛው በቡድን እና በጥንድ እንዲሰሩ መደረግ አለበት። ፍችን ወይም መልዕክትን እንዲያስተላልፉ፣ ሲያስፈልግም በፍች ላይ እንዲወያዩ ማድረግም ያስፈልጋል /Celce-Murcia 1991:8/።

ተግባቦታዊ አቀራረብን ከሰዋስው ትምህርት አኳያ ስናየው የቋንቋ መዋቅር እንዴት መልዕክትን እንደሚሸከም እና ለመግለጽ እንደሚያገለግል ከሚያሳዩ መልመጃዎች ውስጥ ተማሪዎቹ ህግጋቱን በራሳቸው ጥረት ለይተው እንዲያወጡ በማድረግ ለማስተማር ይሞክራል። አላማውም ሰዋስውን ለተግባቦታዊ አገልግሎት ማዋል ነው። የተመሰረተውም ተገቢነት ያላቸው እና ጥሩ ጥሩ አውዳዊ ምሳሌዎች በጥቅም ላይ ከዋሉ ሰዋስዋዊ ህግጋት በትምህርቱ ሂደት ግልጽ ይሆናሉ በሚል እምነት ላይ ነው። አፈጻጸሙም የሚከተለውን ይመስላል።

1. መምህሩ በአንድ አውድ ውስጥ ያዘጋጀውን የሰዋስው ትምህርት ለተማሪዎቹ አቅርቦ ቅርፀ የሚሸከመውን ፍች ግልፅ ያደርጋል።
2. በአውዱ መሰረት የተለያዩ ምሳሌዎችን በመስጠት ለተማሪዎቹ ፍችውን ያለማምዳል።
3. ከብዙ ልምምድ በኋላ የሰዋስዋዊ ነጥቡን ምሳሌ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ያሳያል።
4. ተማሪዎቹ አውዱንና ምሳሌዎቹን በደብተራቸው ላይ ይገለብጣሉ።
5. ተማሪዎቹ በፃፉት ምሳሌ መሰረት እንዲተነትኑ ሌሎች መልመጃዎች ይሰጧቸውና ይተነትናሉ።
6. መምህሩ ተማሪዎቹ ተንትነው መጨረሳቸውንና ፍችውን መረዳታቸውን ካረጋገጠ በኋላ መጠነኛ ማብራሪያ ይሰጣል።

ይህ ተግባቦታዊ አቀራረብ ከአንድ በላይ የሆኑ የቋንቋ ክሂሎችን በቅንጅት ለማስተማር ያስችላል። የተማሪዎችን ተሳትፎ ያበረታታል። ተማሪዎችን በጥንድና በቡድን ለማሳተፍም ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ተማሪዎቹ በራሳቸው ችግር የመፍታት ችሎታ እንዲኖራቸው ያደርጋል። በልምምዱ ሂደትና ህግጋቱን ከተነተኑ በኋላ በመልሶቻቸው ላይ በቡድንና በጥንድ እንዲወያዩ ያደርጋል። በዚህም ይህ የሰዋስው ትምህርት ሂደት በቋንቋው እንዲለማመዱ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። በአቀራረቡ ላይ የሚነሣው ነቀፋ ለቋንቋ ሰዋስው አነስተኛ ትኩረት ይሰጣል የሚል ነው። በዚህ አቀራረብ ስር ከሚመደቡ ሁለተኛ ቋንቋን የማስተማሪያ ዘዴዎች ውስጥ የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል።

#### 2.8.2.1 አእምሮታዊ ዘዴ/Cognitive Method/

አእምሮታዊ ዘዴ በአእምሮታዊና በሰዋስዋዊ ትውረቶች ላይ የተገነባ ዘዴ ነው፡፡ ቋንቋ መማር ማለት ቋንቋው የተዋቀረበትን ስርዓት አውቆ አዳዲስ ዓረፍተ ነገሮችን ማፍለቅ መቻል ነው የሚል መሠረተ ሀሳብ አለው፡፡

አላማው በታላሚው ቋንቋ ሀሣብን መግለፅ ማስቻል የሚል ሲሆን ለአራቱም የቋንቋ ክሂሎች ሚዛናዊ ትኩረት ይሰጣል፡፡ የአፍ መፍቻ ቋንቋን እንደ አስፈላጊነቱ መጠቀምንም አይከለክልም፡፡ በትምህርቱ ሂደት ስህተት ሊከሰት እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ የትምህርቱ አንድ ክፍል ተደርጎም ይታያል፡፡

ይህ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መገልገልን ያስገደብ መልቀቁና ልምምድ ለቋንቋ ለመዳ የሚያበረክተውን አስዋፅኦ መዘንጋቱ እንደ ድክመት ተቆጥሮበታል፡፡

#### 2.8.2.2. ዝምታዊ ዘዴ

ዝምታዊ ዘዴ ተማሪዎቹን ችግር ፈቺ በማድረግ ላይ ያተኮረ የሁለተኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ ነው፡፡ እንደዚህ ዘዴ እምነት ቋንቋ የትርጉም አልባ ድምፆች ስብስብ ነው፡፡ የአፍ መፍቻና የሁለተኛ ቋንቋ ለመዳዎችም የተለያዩ ናቸው፡፡

በዚህ ዘዴ በትምህርቱ የሚፈለገው ውጤት የሚገኘው ተማሪውን ፈጣሪና ተመራማሪ በማድረግ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ፍች በቁሳዊ መረጃዎች በመታገዝ ግልፅ ይደረጋል፡፡ በአብዛኛው በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚከናወኑት እንቅስቃሴዎች የተማሪዎቹ ናቸው፡፡ መምህሩ ተማሪዎቹ ብዙ እንዲናገሩ ይገፋፋል፡፡

የዝምታዊ ዘዴ የአጭር ጊዜ አላማ ሰዋስውን ማሳወቅ ነው፡፡ ስለዚህም የቋንቋው ሰዋስው ተጠየቃዊ በሆነ መንገድ ከቀላል ወደ ከባድ ይቀርባል፡፡ የትምህርቱ መነሻ የተማሪዎቹ የቀደመ እውቀት ነው፡፡ ትምህርቱ ሲሰጥ ደግሞ አራቱ የቋንቋ ክሂሎች እንዲደጋገፉ ይደረጋል፡፡

#### 2.8.2.3. ማህበራዊ ዘዴ

ማህበራዊ ዘዴ በማማከር መማር ስነልቦናዊ ትውረት ላይ የተገነባ የሁለተኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ ነው፡፡ በዚህም መሠረት መማር በግለሰብና በማህበረሰብ መሀከል በሚደረግ ግንኙነት ይከናወናል፡፡ ቋንቋም ማህበራዊ ክስተት ነው፡፡ አዲስ ቋንቋን መማር ደግሞ አዲስ ማህበራዊ ግንኙነትን መፍጠር ነው፡፡

የማህበራዊ ዘዴ አላማ ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋቸውን ልክ እንደ አፍ ፈቱ እንዲያውቁ ማድረግ ነው፡፡ ስለዚህም በትምህርቱ ሂደት ተማሪዎቹ የማህበረሰቡ አባል ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ እርስ በእርስ በተማሪዎቹ እና በተማሪና በመምህር መሀከል የሚኖር መልካም ግንኙነት ለአላማው ግብ መምታት ወሳኝ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

ይህ ዘዴ የተለያዩ የመማሪያ ክፍል ውስጥ ክንውኖች አሉት፡፡ እነዚህም ትርጉም፣ የቡድን ሥራ፣ ድምፅ ቀረፃ፣ ማዳመጥ፣ ውይይትና ስርዓተ ዝግበት ናቸው፡፡ መምህሩ ከአስተማሪነቱ በተጨማሪ የማማከር ተግባርን ይፈፅማል፡፡ ለዚህም የተማሪዎቹን ስሜት ማጥናት ይጠበቅበታል፡፡ በዚህ ዘዴ አሰራር መሠረት የስነልቡናው መካሪ ተመካሪ ግንኙነት የአስተማሪ ተማሪ ግንኙነት ሆኖ ይከናወናል፡፡ ይህም የተማሪዎቹን ጭንቀትና ጫና ለመቀነስ ያገለግላል፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ በዝርዝር እንዳየነው ተግባቦታዊ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ የቋንቋ ቀዳሚ ተግባር በሆነው ተግባቦት ላይ የሚያተኩር ሲሆን የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ ለማስተማር ይሞክራል፡፡ የተማሪዎችን የተግባቦት ችሎታ ለማዳበር ለሚያስችሉ የትምህርት እንቅስቃሴዎችም ቅድሚያ ይሰጣል፡፡ ይህ ባህሪውም ተመራጭ የቋንቋ ማስተማሪያ አቀራረብ ያደርገዋል፡፡ ለተግባቦት የበዛ ትኩረት መስጠቱም የሰዋስው ትምህርትን ዘንግቷል አያስብለውም፡፡ ምክንያቱም ከእያንዳንዱ ከሂል በስተጀርባ ሰዋስው ስላለ ተማሪዎቹ በእነዚህ ክሂሎች ላይ ሲለማመዱ በሰዋስው ላይም ስለሚለማመዱ የሰዋስው እውቀታቸውም አብሮ ስለሚዳብር ነው፡፡ ስለዚህም በክፍል ውስጥ የሚቀርበው የሰዋስው ትምህርት በዘመናችን ተቀባይነትን ባገኘው የቋንቋ ትምህርት አቀራረብ ላይ ተመስርቶ መሰጠት ይገባዋል፡፡ ይህ ሲባል ግን ውጤት ተኮር አቀራረብ ሰዋስውን ለማስተማር አገልግሎት ላይ ሊውል አይገባውም ማለት አይደለም፡፡ አቀራረቡ በተለይ የተግባቦት ችሎታቸው የዳበረ ተማሪዎችን ለማስተማር ያገለግላል፡፡ ስለዚህም በዋነኛነት ተግባቦታዊ አቀራረብን በማስቀደም ውጤት ተኮር አቀራረብንም እንደ አስፈላጊነቱ በመጠቀም ሰዋስውን ማስተማር ይገባል፡፡

## 2.9 ሰዋስውን የማስተማር መርሆች

በሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ላይ ከተስማማን ቀጥሎ የሚነሳው ጥያቄ "ትምህርቱ ምን ዓይነት መርሆችን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አለበት?" የሚለው ነው፡፡ በዚህ ጥያቄ ላይም ምሁራን አስተያየቶቻቸውን ሰንዝረዋል፡፡ Celce-Murcia/1991፡280/ ሰዋስውን ለማስተማር "ሦስት መሠረታዊ ነገሮችን (ቅርጽን ወይም መዋቅርን፣ ፍቺን እና ማህበራዊ አጠቃቀምን) ማየት ተገቢ ነው ይላሉ፡፡ ማረው(1998) ደግሞ 'የሰዋስው ትምህርት ትኩረት በምን ላይ መሆን አለበት?' ለሚለው ጥያቄ የተለያዩ ምሁራን የተለያየ ሃሣብ እንደሚያቀርቡ ያስረዳሉ፡፡

*ለተወሰኑ ምሁራን የሰዋሰው ትምህርት ክፍለ ጊዜ ተቀዳሚ ተግባር ሰዋስዋዊ ህግጋትንና ተዛማጅ ፅንሰ ሃሳቦችን ማብራራት ነው። ለሌሎች ደግሞ መደበኛ ሰዋስዋዊ መዋቅሮችን ፥ ለምሣሌ፡- የመሆን ግስ፣ ተውላጠ ስሞችንና የመሳሰሉትን ማለማመድ ማለት ነው። ከዚህ በተለየ ሁኔታ ደግሞ ሰዋስውን ማስተማር ማለት ተማሪዎች በሚማሩበት ቋንቋ በሚገባ መግባባት እንዲችሉ በእውነተኛ ሁኔታ የሚጠቀሙባቸውን አጋጣሚዎች ማመቻቸት ማለት ነው /ማረው 1998፡49/።*

ከሁለቱ ምሁራን ገለፃ የሰዋስው ትምህርት ሰዋስዋዊ ህግጋትን፣ እነዚህ ህግጋት በተግባቦት ሂደት እንዴት ተግባር ላይ እንደሚውሉ እና መደበኛ ሰዋስዋዊ መዋቅሮችን የሚያለማምድ ወይም የሚያስተምር መሆን እንዳለበት መረዳት ይቻላል። እነዚህም ጉዳዮች የትምህርቱን ይዘት የሚመለከቱ ናቸው። በተጨማሪም Celce-Murcia/1991፡283/ በማስተማር ሂደቱ ልንከተላቸው የሚገቡ አራት የሚሆኑ ስልቶችን ጠቁመዋል። እነዚህንም ወደፊት በንዑስ ክፍል 2.9.2 እናያቸዋለን።

እስካሁን የቀረቡትን ሃሣቦች በመመርኮዝ ሰዋሰውን በማስተማር ሂደት ልንከተላቸው የሚገቡ መርሆችን ይዘትን የሚመለከቱና የማስተማር ስልትን የሚመለከቱ በማለት በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች መመደብ ይቻላል።

### 2.9.1 ይዘትን የሚመለከቱ ሰዋስውን የማስተማር መርሆች

ቀደም ሲል እንዳየነው ሰዋስውን ለማስተማር ቅርጽን(መዋቅርን) ፣ ፍችን እና ማህበራዊ አጠቃቀምን ማየት ተገቢ ነው ።

*1. ቅርጽ ወይም መዋቅር /Form/*

ቅርጽ ወይም መዋቅር ስንል *ሥነ ድምጽን* ፣ *ሥነ ምዕላድን* ፣ *ሥነ* አገባብን ወዘተ የሚመለከት ነው። እነዚህን ሰዋስዋዊ ቅርፆች ለማስተማር በቅድሚያ የማስተማሪያ ይዘትና ስልት መምረጥ ያስፈልጋል። ምርጫውም ለየትኛው ክፍል ፣ ለየትኛው ተማሪ (አፍ-ፈት ለሆነ ወይስ ላልሆነ) የሚለውን ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት።

*2. ፍች /Meaning/*

ፍች ሲባል ቃላት በተናጠልና በዓረፍተ ነገር ውስጥ ሆነው የሚይዙትን መልዕክትና ሰዋስዋዊ መዋቅሮች የሚይዙትን መልዕክት ይመለከታል ። በሰዋስው ትምህርት ውስጥ ፍችን ለማስተማር የተለያዩ መልመጃዎችን ማቀድ ያስፈልጋል ። ለምሣሌ ቃላዊ ዝምድናን ፣ ጽንሰ ሃሣብን ፣ ቅርጽና ፍቺ ማዛመድን ፣ አንድን ሰዋስዋዊ ፍች ከሌላው መለየትን፣ የፍቺ ዝምድናን መለየትን ወ.ዘ.ተ. ማለማመድ ይቻላል።

*3. ማህበራዊ የቋንቋ አጠቃቀም /Language use in a social context /*

ማህበራዊ የቋንቋ አጠቃቀም ማህበራዊ አውድን፣ ሥነ ልሣናዊ የዲስኩር አውድን እና ይዘትን ይመለከታል Celci-Murcia (1991፡280)። ማህበራዊ የቋንቋ አጠቃቀምን ስናስተምር ተማሪዎች ከተለያዩ መዋቅሮች ውስጥ ትክክለኛውን ቅርጽ ከአውድ እንዲለዩ ማድረግ ይቻላል። ለምሣሌ የአንድን ነገር ምክንያት ወይም አስራር፣ መመሪያና የመሳሰሉትን በማስለጽ ተገቢነት ያላቸው የሠላምታ ልውውጦችን፣ ንግግሮችን ወዘተ በጭውውትና በተለያዩ መልመጃዎች እያለማመዱ የማህበራዊ ዓውድ ጠቀሜታን ማስተማር ይቻላል።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ሶስት ነጥቦች በቋንቋ አማካኝነት የመግባባት ስርዓትን የሚያሣዩ ሲሆኑ የማይነጣጠሉና የተያያዙ ናቸው። ቅርጽ/መዋቅር/ እንዴት ተዋቀረ? የሚለውን፣ ፍችው ምን ማለት ነው? የሚለውን እና ተግባራዊነቱ መቼ? ለምን አገልግሎት? የሚሉትን ጥያቄዎች በማንሣት የቋንቋ አወቃቀርን፣ ይዘትንና አተገባበርን በጥምር የምንመለከትበት ስልት ነው። በታላሚው ቋንቋ ተጠቅመን ተግባባን ማለት የምንችለውም የሶስቱ መሠረታዊ ነገሮች አጠቃላይ ቅንጅት ሲኖር ነው። ስለዚህም ሰዋሰውን በማስተማር ጊዜ ሶስቱን ጉዳዮች አስተሳስሮ ማቅረብ ያስፈልጋል።

## 2.9.2 የማስተማር ስልትን የሚመለከቱ ሰዋስውን የማስተማር መርሆች

እንደ Celci-Murcia(1991፡284)። አገላለጽ ሰዋሰውን በምናስተምርበት ወቅት የሚከተሉትን አራት ነጥቦች ልብ ማለት ያስፈልጋል ።

1. *ተማሪዎች አንድን መዋቅር ለአንድ ጊዜ ብቻ በመማር ሁለ ነገሩን አይገነዘቡትም።* የአንድን መዋቅር ትክክለኛ/ተገቢ/ ቅርጽ፣ ፍች እና ማህበራዊ አጠቃቀም በተሟላ መልክ ለመጠቀም የሚችሉት በሂደት በሚመጣ እውቀት ነው። ስለዚህም አንድን መዋቅር አንድ ጊዜ ብቻ አስተምሮ በሌላ ጊዜ አለማንሣት ተገቢ አይደለም ።
2. *ተማሪዎች የአንድን መዋቅር ህግ ሲማሩ ያ ህግ የማይሰራባቸውን አጋጣሚዎች/exceptions/ ማወቅ አለባቸው።* ካልሆነ ግን ስህተት ላይ ሊወድቁ ይችላሉ። ለምሣሌ "ነጠላ ስሞችን ለማብዛት '-ኦች' ን መጨመር ያስፈልጋል" የሚለውን ህግ የያዘ ተማሪ ሁሉም ስሞች ላይ '-ኦች' ን ለመጨመር ይሞክራል ።
3. *የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች አፍ ወደ ፈቱበት የቋንቋ እውቀትና ልምድ ያዘነብላሉ።* ስለዚህም መምህሩ ሁሉንም የመዋቅር ጉዳዮች በቡድን በተመሳሳይ ሁኔታ ለማስተማር ከመሞከር ይልቅ ተማሪዎቹ ከሚያውቁት ወይም ከደረሱበት የመዋቅር እውቀት መነሣት አለበት። ይህ ሁኔታ ከክፍል ክፍል የሚሰጠውን የመዋቅር ትምህርት እንዲለያይ ሊያደርገው ይችላል። የልዩነቱ መንስኤዎችም

ሀ. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሁኔታ እና

ለ. የታላሚው ቋንቋ እውቀት ናቸው።

4. ቋንቋ ውስብስብ በመሆኑ ለተለያዩ የሰዋስው ይዘቶች የተለያዩ የማስተማር ሂደቶችን መከተል ያስፈልጋል።

## 2.10 በቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ

ሐዋዝ (2000፡ 14) Grant /1989/ን ጠቅሰው እንደገለፁት ሰዋስዋዊ ይዘቶች በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ በሦስት መንገዶች ሊቀርቡ ይችላሉ። እነዚህም ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ እና ሰዋስውን እንደ ክሂል ማቅረብ ናቸው። እነዚህ ሰዋስውን የማቅረቢያ መንገዶች የየራሳቸው የሆኑ የትኩረት አቅጣጫዎችና ደካማና ጠንካራ ጎኖች ስላሏቸው በዝርዝር ማየት ያስፈልጋል።

### 2.10.1 ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር (ውጤት ተኮር) አቀራረብ

በዚህ አቀራረብ አማካኝነት ሰዋስዋዊ ይዘቶች በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሚካተቱት የታላሚውን ቋንቋ ቅርፅ፣ መዋቅር እና ሌሎች ህግጋትን ለተማሪዎቹ በቀጥታ ለማስተማር ታስቦ ሲሆን አቀራረቡ የተመሰረበት ዋነኛ ሀሳብም "ተማሪዎቹ የቋንቋውን ስርዓት ከተማሩ፣ ለሚፈልጉት ጉዳይ ተገቢ ነው ብለው ባመኑበት መንገድ በቋንቋው መጠቀም ይችላሉ" የሚል ነው/Grant 1989:12/። ተማሪዎቹ በዚህ መንገድ የቀረቡ ሰዋስዋዊ ይዘቶችን ሲማሩ ሁለት ቁልፍ ደረጃዎችን ማለፍ ይጠበቅባቸዋል። የመጀመሪያው አዲሱን የቋንቋ ግብዓት መረዳት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ይህን ግንዛቤ ተጠቅሞ የቋንቋው ሕግ በሚፈቅደው መሠረት የተለያዩ መዋቅሮችን ማዋቀር፣ መበታተን፣ መለዋወጥ እና እንደገና ማዋቀር መቻል ናቸው/Batstone 1994:51/። ሰዋስዋዊ ይዘቶችን ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በሆነ መንገድ የሚያቀርቡ የመማሪያ መፃህፍት ባህላዊ /Traditional/ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት እንደሚባሉ/Grant 1989:12-13/ ይገልፃሉ። እነዚህ ባህላዊ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍትም ጠቅለል ባለ መልኩ የሚከተሉትን ባህርያት ያሳያሉ።

- ከቋንቋ ተግባቦታዊ ተግባር ይልቅ ለቋንቋ መዋቅሮች እና ለሰዋስው ትኩረት ይሰጣሉ።
- ከማዳመጥና ከመናገር ክሂሎች ይልቅ ለንባብና ለመፃፍ ክሂሎች ትኩረት ይሰጣሉ።
- ለቋንቋ ትክክለኛነት (accuracy) ትኩረት ይሰጣሉ።
- በመርሃ ትምህርቱ እና በፈተና ላይ የማተኮር ዝንባሌ ይታይባቸዋል።
- ለአጠቃቀም ቀላል ስለሚመስሉ እና በከፍተኛ ሁኔታ ፈተና ተኮር በመሆናቸው በአንዳንድ መምህራን ዘንድ ተወዳጅ ናቸው።

የዚህ አቀራረብ ጠንካራ ጎኖች ተደርገው የሚወሰዱት ተማሪዎቹ የቋንቋ መዋቅሮችን እና ሰዋስዋዊ ህግጋትን በቀጥታና በፍጥነት እንዲረዱ ማስቻሉ እና መምህራኑ ያለብዙ ውጣውረድ

ሊተገብሩት የሚችሉ መሆኑ ናቸው። ከዚህ ውጭ ግን በተለይ ሌሎች የቋንቋ ክሂሎችን ከማዳበር አኳያ ድክመቶች ይታዩበታል። በዚህ ላይ /Grant 1989:13/ የሚከተለውን ይላሉ።

> ተማሪዎቹ በዚህ ዘዴ በቀረቡ መፃህፍት አማካኝነት ለዓመታት ያክል በቋንቋው መዋቅሮችና ህግጋት ላይ ልምምድ ያደርጋሉ። የቋንቋውን መዋቅሮችና ህግጋትም ሊያውቋቸው ይችላሉ። ነገር ግን ከትምህርቱ በኋላ በቋንቋው መጠቀም አይችሉም፤ ማለትም አይግባቡበትም። የአቀራረቡ ዋነኛው ችግርም ይሄው ነው።

ከዚህ በላይ ከቀረቡት ሃሳቦች መረዳት እንደሚቻለው ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ ትኩረቱን የሚያደርገው የቋንቋ መዋቅሮችን እና ህግጋትን ለተማሪዎቹ በቀጥታ በማቅረብ የተማሪዎቹን ሰዋስዋዊ እውቀት በማዳበር ላይ ነው። ይህን ሲያደርግም ሌሎች የቋንቋ ክሂሎችን በታቀደ ሁኔታ ግምት ውስጥ ስለማያስገባ የተማሪዎቹን የተግባቦት ችሎታ ከማዳበር አኳያ ክፍተት ይታይበታል። ተማሪዎቹ ምንም እንኳን ሰዋስዋዊ እውቀት ቢኖራቸው በቋንቋው መግባባት ካልቻሉ፣ የቋንቋ ትምህርቱ ጉዳይ እንደተተወ ይቆጠራል።

### 2.10.2 ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ (ክሂል ተኮር) አቀራረብ

የዚህ አቀራረብ አቀንቃኞች እንደሚሉት የቋንቋ መዋቅሮች እና የሰዋስዋዊ ሕግጋት እውቀት አስፈላጊ ቢሆንም፣ መዋቅሮቹን እና ሕግጋቱን ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ነጥሎ ማስተማሩ ግን ተገቢ አይደለም። ምክንያቱም የመዋቅር እና የሰዋስዋዊ ሕግጋት እውቀት ብቻውን በቋንቋው ለመጠቀም አያስችልም/Freeman 1986:123/። ስለዚህም ሰዋስዋዊ ይዘቶች ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅተው መቅረብ አለባቸው።

የሰዋስዋዊ ይዘቶቹን አቀራረብ ስናይ በጥንቃቄ የተመረጡ መልመጃዎች ቀርበው ተማሪዎቹ መልመጃዎቹን ከሰሩ በኋላ በእነዚህ ምሳሌዎች መሠረት ሰዋስዋዊ ህጉን በራሳቸው እንዲደርሱበት ይደረጋል። በዚህ አቀራረብ ሰዋስዋዊ ይዘቶቹ በአውድ ውስጥ ተካተው ስለሚቀርቡና ተማሪዎቹም ዕውናዊነት ያለው የሃሳብ ልውውጥ ስለሚያደርጉ የቋንቋው ቅርጾች ያላቸውን አጠቃቀም ለመረዳት ያስችላል።

በዚህ መንገድ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን የሚያካትቱ የመማሪያ መፃህፍት ተግባቦታዊ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት እንደሚባሉ ምሁራን ይጠቀማሉ/Grant 1989:13/። ተግቦታዊ የመማሪያ መፃህፍት ተማሪው በታላሚው ቋንቋ እንዲገለገልበት የሚያስችሉ እድሎችን በክፍል ውስጥ ለመፍጠር ይሞክራሉ። መፃህፍቱ ጠቅለል ባለ መልኩ የሚከተሉት ባህሪያት ይታዩባቸዋል።

- ከቋንቋ ቅርፅ ይልቅ ለቋንቋ ተግባቦታዊ ተግባር ትኩረት ይሰጣሉ።
- የተማሪዎቹን ፍላጎት ለማንፀባረቅ ይሞክራሉ።

- ቋንቋውን በመጠቀም በክሂሎቹ ላይ ያተኩራሉ። በዚህም ምክንያት ተግባር ተኮር ናቸው።
- አብዛኛውን ጊዜ ለአራቱ የቋንቋ ክሂሎች የተመጣጠነ ትኩረት ይሰጣሉ። ነገር ግን ከባህላዊ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት በበለጠ ለማዳመጥና ለመናገር ትኩረት ይሰጣሉ።
- በአላማ ገለፃቸው በጣም ዝርዝር የመሆን አዝማሚያ ይታይባቸዋል።
- ይዘቶቹ እና የማስተማሪያ ዘዴዎቹ እውነተኛውን የዕለት ተዕለት ቋንቋ እና የቋንቋ አጠቃቀም ያንፀባርቃሉ።
- የጥንድ እና የቡድን ስራን ያበረታታሉ። በዚህም የመምህራንን የክፍል አስተዳደር ብቃት ይፈታተናሉ።
- ትኩረታቸው ለቋንቋ ትክክለኛነት ሳይሆን ለቋንቋ አፍስሶት (Fluency) ነው።

ከዚህ በላይ በዝርዝር ለማየት እንደተሞከረው ከርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ የተግባቦት ችሎታን በማዳበር ላይ ትኩረቱን በማድረግ ሰዋስውን ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅቶ ለማስተማር የሚሞክር አቀራረብ ነው። አቀራረቡ እውናዊ የሆኑ የቋንቋ አጠቃቀሞችን እና ተግባራትን ወደ ክፍል አምጥቶ ስለሚያሠራ ተማሪዎቹ ለትምህርቱ ፍላጎትና ተነሳሽነት ይኖራቸዋል። በተጨማሪም ለትምህርት በቀረበው ሰዋስዋዊ ይዘት ላይ ተማሪዎቹ በተለያዩ ዘዴዎች እንዲለማመዱበት ስለሚያደርግ ትምህርቱን ለማስረፅ ይረዳል። በአቀራረቡ ላይ የሚቀርበው ትችት ለቋንቋ አጠቃቀም የበዛ ትኩረት ይሰጣል የሚል ነው።

### 2.10.3 ሰዋስውን እንደ ክሂል ማቅረብ

ሐዋዝ (2000:17) Grant /1989/ን ጠቅሶ እንደዘገቡት ይህ አቀራረብ የተመሰረተው ከላይ በቀረቡት ሁለት አቀራረቦች ውስጥ የሚታዩ ክፍተቶችን ለመድፈን በማሰብ ሲሆን ዋነኛ አላማውም ተማሪዎቹን ጥንቃቄና ቁጥጥር ከተሞላበት ውጤት ተኮር አቀራረብ ወደ ውጤታማ የቋንቋ አጠቃቀም (ክሂል ተኮር) ማሸጋገር ነው። ቀደም ሲል እንዳየነው ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ በቋንቋው ቅርፅ ላይ ሲያተኩር ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ ደግሞ በቋንቋው አጠቃቀም ላይ ያተኩራል።

ተማሪዎች በተማሯቸው ሰዋስዋዊ ይዘቶች ላይ ልምምድ ሲያደርጉ በቂ ቁጥጥር ካልተደረገ ለትምህርት የቀረበውን ይዘት እየተውት ሊሄዱ ይችላሉ። እንዲህ ከሆነ ደግሞ በውጤት ተኮር የቀረበው ሰዋስዋዊ ይዘት እንዴት ለተግባቦት አገልግሎት እንደሚውል የማወቃቸው ዕድል አናሳ ይሆናል። ሰዋስውን እንደ ክሂል ማቅረብ የሚለው ሀሳብ የመጣውም ይህንን ክፍተት ለመድፈን ነው።

ሰዋስው እንደ ክሂል ሲቀርብ ተማሪዎቹ ሰዋስውን እንዲከታተሉ ይጠበቅባቸዋል። ተግባራትን በሚሰሩበት ጊዜ ደግሞ በቋንቋው አጠቃቀም ላይ ትኩረት ያደርጋሉ። ለዚህም እንዲረዳ በተማሩት ሰዋስው መሠረት የማዳመጥ እና የማንበብ ተግባራትን በስፋት በመስጠት በውጤት ተኮር እና በሂደት ተኮር አቀራረቦች መካከል ያለውን ክፍተት ሚዛናዊ ማድረግ ይቻላል።

በአጠቃላይ የሰዋስው ትምህርትን በቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ በተለያዩ መንገዶች ማቅረብ ይቻላል። እያንዳንዱ የአቀራረብ መንገድም የየራሱ የትኩረት አቅጣጫ እና ጠንካራና ደካማ ጎኖች አሉት። ስለዚህም "የትኛውን አቀራረብ እንጠቀም" የሚለውን ለመወሰን እያንዳንዱን አቀራረብ በጥልቀት ማወቅ ያስፈልጋል።

## 2.11 የቋንቋ መምህር ሊኖሩት የሚገቡ ሰዋስዋዊ እውቀቶችና አስፈላጊነታቸው

የሰዋስው ትምህርት ውጤታማ እንዲሆን ማለትም ተማሪው የታላሚው ቋንቋ መዋቅርን በአግባቡ ተገንዝቦ እንዲገለገልበት ከሚረዱ ጉዳዮች ውስጥ የመምህሩ የሰዋስው ትምህርት እውቀት ዋነኛ ተጠቃሽ ነው። ምንም እንኳ በቋንቋ ትምህርት ክፍል ውስጥ ብዙ መናገር የሚጠበቅባቸው ተማሪዎቹ ቢሆኑም መምህሩ ለተማሪዎቹ መመሪያ ሲሰጥ እና ገለፃ ሲያደርግ በቋንቋ አጠቃቀሙ ጥሩ ሞዴል መሆን አለበት /Prabhu 1987 ፥ Odlin 1994 /።

አንድ የቋንቋ መምህር ሰዋስውን በውጤታማነት ማስተማር እንዲችል የስነ ልሣን ንድፈ ሃሣቦችን፣ የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስው እና የሰዋስው ትምህርት ማቅረቢያ ዘዴዎችንና ስልቶችን በሚገባ ማወቅ እንዳለበት ምሁራን ይጠቁማሉ /Harmer 1987፣ Leech 1994፣ Mitchell 1994/። በሞዴልነት የሚታይ የቋንቋ መምህር ሊኖሩት ይገባል ተብለው በምሁራን የሚታመንባቸው ዝርዝር ሰዋስዋዊ እውቀቶች የሚከተሉት ሲሆኑ የሰዋስዋዊ እውቀቶቹ አስፈላጊነትም በየርዕሳቸው ተያይዞ ቀርቧል።

### 2.11.1 ሰዋስውና ተግባቦት የማይነጣጠሉ መሆናቸውን ማወቅ

ሰዋስው ከተግባቦታዊ ስርዓት ጋር የተያያዘ መሆኑን ማወቅ ለመምህራን እጅግ አስፈላጊ ነው። በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተግባቦታዊ ብቃት ማለትም የአፍላቂና የተቀባይ ክሂሎች ችሎታ ዋነኛ የትምህርቱ አላማ ተደርጎ የሚታይ ቢሆንም የሰዋስው ችሎታ ሳይዳብር የክህሎት ችሎታ ሊዳብር አይችልም። ስለዚህም በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተግባቦት እና ስርዓት ተያያዥነት ያላቸው መሆኑን መምህሩ ሊያውቅ ይገባል።

### 2.11.2 የታላሚው ቋንቋ ሰዋስው እውቀት

መምህሩ በታላሚው ቋንቋ በሳል የሰዋስው እውቀት እንዲኖረው የሚፈለግበት ምክንያት ለተማሪዎች የሚቀርቡትን የማፍለቅ ክሂሎች(መናገርና መፃፍ) ከመቀበል ክሂሎች(ማዳመጥና

ማንበብ) ጋር ለማመጣጠን የሚያስችለው በመሆኑ ነው። አንብቦ መረዳትና አዳምጦ መረዳት ከመናገር እና ከመፃፍ ይልቅ ረቂቅ የሆኑና ለክትትልም አስቸጋሪ የሆኑ ክሂሎች ናቸው። ተማሪዎቹ በማዳመጥ ወይም በንባብ ልምምድ ጊዜ የሚገጥሟቸውን ችግሮች ለመለየትና ለችግሮቹም መፍትሄ ለመስጠት መምህሩ የቋንቋውን ሰዋስው በሚገባ ሊያውቀው ይገባል።

### 2.11.3 የሰዋስውና የተግባቦት እውቀት

የቋንቋ መምህር በሳል ሰዋስዋዊ እና ተግባቦታዊ እውቀት እንዲኖረው የሚያስፈልግበት ምክንያት የተማሪዎችን የንግግር እና የጽሁፍ አፍልቆት ለመገምገም፣ በተለይም ተማሪዎቹ የጽህፈት ክሂላቸውን እንዲያበለጽጉ ተገቢ እገዛ ለመስጠት ስለሚያስችል ነው። የመምህሩ ሰዋስዋዊ እውቀት ተማሪዎቹ በቋንቋ ትምህርት ሂደት ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምክንያት የሚሆኑትን ጉዳዮች ለመለየት፣ ሊፈጽሟቸው የሚችሉትን ስህተቶች ቀድሞ በማወቅ እንዳይፈጠሩ ለመከላከል፣ ተገቢ የትምህርት አቀራረብ ስልቶችን ለመገልገልና ሰዋስዋዊ እውቀታቸውን ለማበልፀግ የሚያስችለው ነው።

### 2.11.4 ሰዋስውን በውጤት ተኮር ዘዴ የማቅረብ እውቀት

የሰዋስው ትምህርቱን በውጤት ተኮር ማለትም ሰዋስዋዊ ይዘቱን በቀጥታ በማብራራት ማስተማር አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በየትኛውም የትምህርት ደረጃ ለብዙ ጀማሪ ተማሪዎች ዋና ዋና ችግር በሆኑት ሰዋስዋዊ ስያሜዎች፣ ረቂቅ ሰዋስዋዊ ህግጋት ወዘተ ላይ በቂ ማብራሪያ መስጠት ያስፈልጋል ። ለዚህም የቋንቋ መምህሩ በሳል የሰዋስው እውቀት እንዲኖረው የሚያስፈልግ ሲሆን በአንፃሩ የተማሪው እውቀት በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኝና በሂደት እየዳበረ እንደሚሄድ ይታመናል። መምህሩ በሳል የሰዋስው እውቀት ከሌለው ለተማሪዎቹ የሚያቀርበውን ትምህርት በተፈለገ መጠን ለማብራራት እና በቀላል መንገድ ለማቅረብ ይቸገራል። ስለዚህም የቋንቋ መምህሩ በሳል የሆነ የሰዋስው እውቀት እና ሰዋስዋዊ ይዘቱን በቀጥተኛ መንገድ ለማቅረብ የሚያስችል እውቀት ባለቤት ሊሆን ይገባዋል።

### 2.11.5 ንጽጽራዊ የሰዋስው እውቀት

የመምህሩ በንጽጽራዊ ትንተና ላይ የተመሰረተ የሰዋስው እውቀት በታላሚውና በተማሪዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች መካከል የሚኖረውን መዋቅራዊ ልዩነትና ተመሳስሎ ለማወቅ ያስችለዋል ይህም እውቀት ተማሪዎቹ በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት ሊገጥሟቸው የሚችሉትን ችግሮች ለመለየትና ለንግግርና ለጽህፈት ልምምድ ምጋቤ ምላሽ ለመስጠት ጠቃሚ ነው ።

## 2.12. የሰዋሰው ትምህርት እቅድ

እንደማንኛውም የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ሁሉ ሰዋስዋዊ ይዘቶችን ወደ መማሪያ ክፍል ውስጥ አምጥቶ ለተማሪዎች ከማቅረብ አስቀድሞ በመምህሩ ሊከናወን የሚገባ ዋና ተግባር አለ፡፡ ይህም የሰዋስው ትምህርት እቅድ ማዘጋጀት ነው፡፡ መምህሩ የሰዋስው ትምህርቱን እቅድ ሲያዘጋጅ ከዚህ በላይ ከሰዋስው ትምህርት ጋር በተያያዘ ያነሳናቸውን ነጥቦች ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡ በተለይም የሰዋስው ትምህርቱን ሊያቀርብ ያሰበው በተግባቦታዊ መንገድ ከሆነ ተግባቦትን ሊፈጥሩ የሚችሉ ተግባራትንና ስልቶችን አስቀድሞ ማቀድ ይኖርበታል፡፡

የሰዋስው ትምህርትን ለማቀድ የሚያስፈልገውን ጊዜ አስመልክቶ Ur/1988/ እና Grant /1987/ በጥቂት ቀናት አንዳንዴም በጥቂት ሰዓታት ወይም ከሰዓታት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ሊታቀድ እንደሚችል ይገልፃሉ፡፡ እነዚሁ ምሁራን እንደሚመክሩት ሰዋስውን በውጤታማነት ለማስተማር እለታዊ የትምህርት እቅዱ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ነጥቦች አካቶ መዘጋጀት አለበት፡፡

- ግልጽ ዓላማ ፡- ተማሪዎቹ የእለቱን የሰዋስው ይዘት ከተማሩ በኋላ የሚያዳብሩት ሰዋስዋዊ እውቀት ወይም ችሎታ በግልጽ ቋንቋ መቀመጥ አለበት፡፡ እዚህ ላይ የሰዋስው ይዘቱ ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅቶ ለትምህርት ሊቀርብና ተማሪዎቹም በክሂሎቹ ላይ ልምምድ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ አላማው ሲገለጽ ተማሪዎቹ ሊያዳብሯቸው የሚችሉት ተግባቦታዊ ችሎታዎችም መጠቆም አለባቸው ፡፡
- መግቢያ፡- መምህሩ የእለቱን የትምህርት ይዘት፣ የትምህርቱን ዓላማ፣ ተማሪዎቹ በተለያዩ የትምህርቱ እርከኖች ማከናወን የሚገባቸውን ተግባራት የሚገልፅበት ክፍል ነው፡፡ በቀደመው የትምህርት ክፍለ ጊዜ ያስተማረው ትምህርት ዋና ዋና ነጥቦችን የሚከልስበት ደረጃም ነው ፡፡ በተጨማሪም ለእለቱ ትምህርት ወሣኝ የሆኑ አዳዲስ ቃላትን ሊያስተምርበት ይችላል ፡፡
- ማቅረቢያ፡- ይህ ደረጃ መምህሩ የእለቱን የሰዋስው ትምህርት ይዘት በአውድ ወይም በምሳሌ በማስደገፍ በገለፃ የሚያቀርብበት ነው፡፡
- መለማመጃ ፡- በዚህ ደረጃ መምህሩ ተማሪዎቹ በተማሯቸው አዳዲስ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ላይ እንዲለማመዱባቸው እና በይዘቶቹ እንዲገለገሉባቸው የሚያስችሉ ስልቶችን ይጠቁማል፡፡ ተማሪዎቹም የቀረበላቸውን አዲስ የቋንቋ መዋቅር በተግባቦታዊ ልምምድ አማካይነት እንዲያሰርፁና ከክፍል ውጭ ባለው አውድ እንዲገለገሉበት ይጠበቃል፡፡
- የጽሁፍ ማጠናከሪያ መልመጃ፡- በዚህ ደረጃ ተማሪዎቹ በተለያዩ መልኮች ልምምድ ያደረጉባቸውን አዳዲስ የሰዋስው ይዘቶች በጽሁፍ መልክ እንዲለማመዱባቸው ይደረጋል፡፡ የጽሁፍ ማጠናከሪያ መልመጃው ተማሪዎቹ የቀረበላቸውን አዲስ የቋንቋ መዋቅር

እንዲያስታውሱ ይረዳቸዋል ። በመሆኑም በትምህርቱ ዝግጅት ወቅት ለተማሪዎቹ የሚቀርቡት የጽሁፍ ማጠናከሪያ መልመጃዎች ሊገለፁ ይገባል ።

- ደጋፊ መሣሪያዎች፡- ደጋፊ የሆኑ ስዕላዊ መርጃ መሣሪያዎች፣ ምንባቦች ወይም ሌሎች ማቴሪያሎችን ሊያጠቃልል ይችላል። ይህም በሰዋስው ትምህርት እቅድ ውስጥ ሊገለጽ የሚገባው ሌላ ጉዳይ ነው ።

## 2.13. ሰዋስዋዊ ስህተትን ማረም

ስህተትና የቋንቋ ትምህርት የማይነጣጠሉ መሆናቸውን በየእለት ተእለቱ የክፍል ውስጥ ትምህርት ማስተዋል ይቻላል ። በእርግጥ ስህተቶች በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ብቻ ሣይሆን በማንኛውም የትምህርት ሂደት ውስጥ የሚከሰቱና ተፈጥሮአዊ ናቸው። እንደ ur/1996 : 85/ በስህተት ውስጥ ግድፈት (error) እና ህፀፅ የሚባሉ ፅንሰ ሃሣቦች አሉ። ግድፈት የአጋጣሚ እና ቀጣይነት የሌለው በተለምዶ ቀላል ወይም ሊያጋጥም የሚችል የሚባል አይነት ሲሆን ህፀፅ ደግሞ ቋሚና ቀጣይነት ያለው ከእውነታ ወይም በጊዜው ተቀባይነት ካገኘው ሃሳብ መፋለስ ነው። ሰለሞን (1987፡9) Norish(1983)ን ጠቅሰው እንደገለፁት ደግሞ ግድፈትም ህፀፅም ያልሆነ የቋንቋ አጠቃቀም ያጋጥማል። ይህ በማንኛውም ሰው ላይ የሚከሰትና ከትኩረት ማነስ፣ ከማስታወስ እጥረት፣ ከድካም እና ከመሳሰሉት የሚከሰት ሲሆን ዝንጋታ /lapse/ ተብሎ ይጠራል። እነዚህ የስህተት አይነቶች በማንኛውም የቋንቋ ትምህርት ክፍል ውስጥ ሊያጋጥሙ የሚችሉ በመሆናቸው ለውጤታማ የቋንቋ ትምህርት መምህሩ ባህሪያቸውንና አይነታቸውን በመለየትና በመገንዘብ አስቀድሞ ለክላከላቸው /ሊቆጣጠራቸው/ እና ሲፈጠሩም ሊያርማቸው ይገባል።

ስህተቶች ሳይፈጠሩ አስቀድሞ ለመከላከል ወይም ለመቆጣጠር የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ያስፈልጋል ።

1. አዳዲስ መዋቅሮችን ማቅረብና ማለማመድ፣
2. በቅድሚያ መታረም የሚገባቸውን ስህተቶች መለየት፣
3. ተደጋጋሚ ስህተቶችን በተደጋጋሚ ልምምድ ማስወገድ

ስህተቶች ከተፈጠሩ በኋላ ደግሞ በሚከተሉት ስልቶች አማካኝነት ማረም ይቻላል።

1. የመጀመሪያ ስህተቶችን መገንዘብ፣
2. የስህተት አይነቶችን መለየት፣
3. እንደ ስህተቱ ተደጋጋሚነት በቅደም ተከተል ማስቀመጥ እና
4. ከተረድኦታዊ /Cognitive/ እንቅፋትነት አንፃር ስህተቶችን መለየትና ማረም ናቸው።

## 2.14 የሰዋስው ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ

ተግባቦታዊ የሰዋስው ትምህርት በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚከተሉት ቅደም ተከተሎች ይከናወናል/ መሰሉ 1994፣ Celce-Murcia 1991/።

1.ማቅረቢያ:- ማቅረቢያ በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ሂደት የመጀመሪያ ክንውን ወይም መግቢያ ነው። አዲሱ ሰዋስዋዊ ቅርጽ የሚሸከመው ፍቺና አጠቃቀሙ ለተማሪዎቹ በአውድ አማካኝነት ግልጽ ይደረግበታል። አውዱ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ለተማሪዎቹ ከመቅረቡ በፊት ተገቢና ቅርፁ የሚሸከመውን ፍች ግልጽ አድርጐ የሚያሣይ መሆን ይኖርበታል። ከዚህ በተጨማሪ በማቅረቢያ ላይ ተማሪዎቹ ቀደም ሲል የተማሩትንና አዲስ የሚቀርበውን የትምህርት ይዘት እንዲያያይዙ ይደረጋል። ይህም ተማሪዎቹን ለትምህርቱ ተነሳሽ ያደርጋቸዋል።

ለዚህ ተግባር የሚውል አውድ በተለያዩ መንገዶች ሊቀርብ ይችላል። ከእነዚህም መካከል የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው ።

ሀ. *በምልልስ* :- ሰዋስዋዊ ቅርፆችን ለማስተዋወቅ የሚቀርብ አውድ በሁለት ሰዎች (ገፀ-ባህሪያት) መካከል የሚደረግ ንግግር ሊሆን ይችላል። ጥንቃቄ መደረግ ያለበት ግን የአዲሱን ቅርጽ ፍቺና አጠቃቀም በግልጽ በማሳየቱና ባለማሳየቱ ላይ ነው። የሚመረጠው ንግግርም በዚያ የክፍል ደረጃና ከቋንቋው ተናጋሪዎች ባህል አንፃር ተገቢነት ሊኖረው ይገባል።

ለ. *የተለያዩ ሁኔታዎችን መጠቀም*:- በተለያዩ የሰው ልጅ ገጠመኞች ላይ የተመሰረቱ ሁኔታዎችን አቅርቦ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘትን ለተማሪዎቹ ማስተዋወቅ ይቻላል። በጥቅም ላይ የሚውሉት ገጠመኞች እውነተኛ ወይም ፈጠራ ሊሆኑ ይችላሉ። ከተማሪዎቹ እውነተኛ ገጠመኝ ጋር የተያያዙ ቢሆኑ ግን አውዱ ለተማሪዎቹ ስሜት ቀስቃሽና ግልጽ ሊሆንላቸው ይችላል ።

ሐ. *ማብራሪያ*:- የተለያዩ ነገሮችን ወደመማሪያ ክፍል ውስጥ አምጥቶ ማብራሪያ እየሰጡ ሰዋስውን በአውድ ማስተዋወቅ ይቻላል። ለዚህ ተግባር ስዕሎች፣ ፎቶግራፎች ፣ ቁሣቁሶች በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ነገሮች ወዘተ በጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ። ለምሣሌ ቁጥርን ለማስተማር የተማሪዎችን ብዕሮች ፣ መጽሀፎች ፣ ደብተሮች ወዘተ መጠቀም ይቻላል።

መ. *መሸጋገሪያ*:- መሸጋገሪያ በተማሪዎቹ የቀደመ እውቀት ላይ ተረማምዶ አዲሱ ሰዋስዋዊ ይዘት በአውድ የሚቀርብበት መንገድ ሲሆን አውዱ በመምህሩ አማካኝነት ሊዘጋጅ ይችላል። በዚህ አካሄድ ትምህርቱ የሚጀምረው በክለሳ ነው። ለምሣሌ ተማሪዎቹ ቀደም ሲል አምንታዊ ዐረፍተ ነገሮችን ተምረው ቢሆን ከአምንታዊ ዐረፍተ ነገር ተነስቶ ወደ

አሉታዊ ዐረፍተ ነገር መሸጋገር ይቻላል። ከዚያም ፍቺውን ግልጽ አድርጉ በማሳየት ወደሚቀጥለው ሂደት ይሸጋገራል።

2.ማውጣጣት፡- ተማሪዎቹ በአውድ የቀረበውን ሰዋስዋዊ ቅርጽ ተጠቅመው እንዲናገሩ የሚገፋፉበት ነው። ይህም አፍልቀው እንዲናገሩ የሚያደርጉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ይከናወናል። መምህሩ ተማሪዎቹ ባላቸው አዲሱን ቅርጽ ተጠቅሞ የማፍለቅ ችሎታ ላይ ተመስርቶ ወደየትኛው ደረጃ መሸጋገር እዳለበት ይወስናል። ይኸውም እንደሚከተለው ይከናወናል ።

- ተማሪዎቹ አዲሱን ይዘት ተጠቅመው ማፍለቅ ከተሣናቸው፣ ወደ ማብራራት ይሸጋገራል።
- የተወሰኑ ስህተቶችን እየፈፀሙ ማፍለቅ ከቻሉም ስህተቶቹን ማረም እንዲቻል ወደ አፍጽም ማፍለቅ ይሸጋገራል።
- ይዘቱን የሚያውቁት ሆኖ መጠነኛ ልምምድ የሚያስፈልጋቸው ከሆነ ፣ ወደፍልቀ ራስ ይሸጋገራል።

3.ገለፃ፡- ገለፃ መምህሩ አዲሱ የቋንቋ ይዘት እንዴት በጥቅም ላይ እንደዋለ የሚያስረዳበት ነው። በዚህ ደረጃ ላይ ቋንቋው ሁለተኛ ቋንቋ ከሆነ በተማሪዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ማብራሪያ መስጠት ይቻላል። በጥቁር ሰሌዳ ላይ የሰዋስዋዊ ቅርፁን ትንታኔ ሊሰጥ ይችላል። በጥቅሉ ተማሪዎቹ አዲሱ ቅርጽ የሚዋቀርበትን ሁኔታ እንዲረዱ ይደረጋል።

4. **ኣፍጽሞ ማፍለቅ**፡- አፍፅሞ ማፍለቅ ተማሪዎቹ አዲስ በቀረበው የሰዋስው ማስተማሪያ ይዘት ላይ የተገደበ ልምምድ የሚያደርጉበት ደረጃ ነው። ልምምዱ የቀረቡትን ምሳሌዎች ደጋግሞ በማለት ይከናወናል። ከአጠቃቀምና ከፍቺ ይልቅ ከስህተት የጠራ ፍፁማዊነት ላይ ያተኩራል። ስለዚህም መምህሩ ተማሪዎቹ አዲሱን የሰዋስው ትምህርት ይዘት በትክክል ማዋቀር መቻላቸውን ይከታተላል። ይህም በሚከተሉት ሶስት ደረጃዎች ይከናወናል።

ሀ. የወል ድግግሞሽ ፡- የወል ድግግሞሽ በሞዴልነት የቀረበውን ምሣሌ ተማሪዎቹ በጋራ ደጋግመው እንዲሉ የሚደረግበት የማለማመጃ ስልት ነው። ይህ ስልት ለሁሉም ተማሪዎች ቅርጽን እኩል የመለማመድ እድል ይሰጣል። በራስ መተማመንን እንዲያዳብሩም ይረዳል። ለመምህሩም በቀረበው ትምህርት ላይ ግንዛቤ ማግኘት አለማግኘታቸውን ይጠቁማል።

ለ. የግል ድግግሞሽ ፡- የግል ድግግሞሽ ከወል ድግግሞሽ ቀጥሎ የሚከናወን ነው። ቀደም ሲል በቀረበው ሞዴል መሠረት ተማሪዎቹ በግል ደጋግሞ በማለት እንዲለማመዱ ይደረግበታል።

ክንውኑም በሚከተለው መልክ በቅደም ተከተል ይተገበራል ።

- መምህሩ አንድ ተማሪ ጠርቶ ይጠይቃል፣
- ተማሪው ለጥያቄው መልስ ይሰጣል፣

- *መምህሩ ምጋቤ ምላሽ ይሰጣል ፡፡*

የመምህሩ ምጋቤ ምላሽ የሚሰጠው የተማሪው መልስ ትክክለኛ መሆን አለመሆኑን ለመግለጽ ነው፡፡ ይኸውም በአንደበት ወይም በምልክት ሊከናወን ይችላል፡፡ አስፈላጊነቱ ተማሪዎቹ ልክ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን እንዲያውቁ ነው፡፡

ሐ. *ባለፍንጭ ምልልስ፦* ባለፍንጭ ምልልስ ተማሪዎቹ ከመምህሩ የሚሰጥን ትንሽ ሃሣብ በፍንጭነት በመጠቀም እርስ በርስ እየተጠያየቁ አዲሱን ሰዋስዋዊ ቅርጽ የሚለማመዱበት ነው፡፡ አፈፃፀሙም በቅደም ተከተል ቀጥሎ ቀርቧል ፡፡


- *መምህሩ መመሪያ ያቀርባል፣*
- *ሞዴሉን ከአንድ ተማሪ ጋር በተማሪዎች ፊት ሰርቶ ያሣያቸዋል፣*
- *መረዳታቸውን ካረጋገጠ በኋላ በጥንድ ይከፋፍላቸዋል፣*
- *የቀረበውን ሞዴል በመጠቀም ተማሪዎቹ አንዱ ፍንጭ ሰጪ ሌላው መላሽ በመሆን ይለማመዳሉ፡፡*

ስልቱ ብዙ ተማሪዎችን ያሳትፋል፡፡ ከፍ ሲል ከተገለፁት የአፍጽሞ ማፍለቂያ መንገዶች ይልቅ የተሻለ የራስን ሃሳብ የመጠቀም እድልም ይሰጣል፡፡ ተማሪዎቹ መምህሩ ያቀረበውን ፍንጭ መጠቀም እንዳለባቸው ግን መዘንጋት የለበትም፡፡ በአጠቃላይ አፍጽሞ ማፍለቅ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተማሪዎቹ ሊሰለቹት ይችላሉ፡፡ የስልቱ እርዝመት የሚወሰነው በትምህርቱ ክብደትና በተማሪዎቹ ብዛት ቢሆንም ከንውኑ ከ10 ደቂቃ መርዘም እንደሌለበት ምሁራን ይመክራሉ ፡፡

አፍጽሞ ማፍለቅ ከተከናወነ በኋላ የሚቀጥለው ፍለቀ ራስ ነው፡፡ ወደዚያ ከመግባቱ በፊት ግን ተማሪዎቹ ሰዋስዋዊ ቅርጹን በትክክል ማዋቀር መቻላቸው መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ተማሪዎቹ የወል እና የግል ድግግሞሽን ሰርተው ባለፍንጭ ምልልስ ላይ የሚቸገሩ ከሆነ ወደኋላ ተመልሶ ማብራሪያ ውስጥ መግባት ያስፈልጋል፡፡ ከዚያም እንደገና ቀጥሎ ያሉትን ሂደቶች በሙሉ በቅደም ተከተል ማከናወን ተገቢ ነው፡፡

*5.ፍልቀ ራስ፦* ፍልቀ ራስ የሰዋስው ትምህርት ሂደት የመጨረሻው ደረጃ ነው፡፡ ትምህርቱ ወደፍልቀ ራስ የሚሸጋገረው መምህሩ ተማሪዎቹ አዲስ የቀረበውን ሰዋስዋዊ ቅርጽ በትክክል ማዋቀራቸውን ሲያረጋግጥ ብቻ ነው፡፡ ይህ ደረጃ ተማሪዎቹ የተማሩትን ሰዋስዋዊ ቅርጽ ተጠቅመው የራሣቸውን ዐረፍተ ነገር የሚመሰርቱበት እና ሃሳባቸውን የሚገልጹበት ነው፡፡ ሲመሰርቱም የሰዋስዋዊ ቅርጹን አጠቃቀም፣ አወቃቀርና ፍቺ መረዳት አለመረዳታቸው ይረጋገጣል፡፡ ተማሪዎቹ ትክክለኛ አረፍተ ነገር ማፍለቅ ከቻሉ አላማው ግቡን መትቷል ማለት ነው፡፡ አለበለዚያ ወደኋላ ተመልሶ የተለያዩ ግይድ/Controlled/ መልመጃዎችን እየሰጡ ማለማመድ ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ በላይ በዝርዝር የቀረቡትን ሃሳቦች መሰረት በማድረግ የሰዋስው ማስተማሪያ ደረጃዎች በሚከተለው መልኩ አጠቃሎ ማቅረብ ይቻላል።




*ሰንጠረዥ 2፡- የሰዋስው ትምህርትን በተግባቦታዊ አቀራረብ የማስተማር ሂደት*

ቀደም ሲል እንደታየውም ሆነ በነጠብጣቡ እንደተመለከተው እንደየተማሪዎቹ ችሎታ ደረጃዎቹን አልፎ መሄድ ወይም ወደ ኋላ ተመልሶ ማከናወን ይቻላል ። ይህ አሰራር ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አንፃር ሲታይ ታልፎ የሚኬደውም ሆነ ወደኋላ የሚመለሰው ሊያጋጥም ይችላል። አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች የቋንቋ ችሎታቸው ይለያያል ። ስለዚህ እንደየችሎታቸው ሂደቱን በሥራ ላይ ማዋል ያስፈልጋል።

## 2.15 ለናሙና የቀረበ እለታዊ የሰዋስው ትምህርት

የትምህርቱ ርእስ ፡- ስማዊ ሀረግ

የትምህርቱ ዓላማ ፡- ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ከዐረፍተ ነገር ውስጥ ስማዊ ሀረግን ለይተው ያወጣሉ፤ በስማዊ ሀረግ ውስጥ የሚገኙ ተዋቃሪዎች ያላቸውን ተግባር ይናገራሉ፤ የራሣቸውን ስማዊ ሀረግ ይመሰርታሉ ።

1. ማቅረቢያ/መግቢያ/

መምህር፡- ባለፈው ክፍለ ጊዜ ስለ ስም ተነጋግረናል። እስቲ የተወሰኑ ስሞችን ንገሩኝ

ተማሪ፡- 1. ጠረጴዛ

2. ድመት

3. ዘር

መምህር ፡- ጠረጴዛ የምን መጠሪያ ነው?

ተማሪ፡- የእቃ

መምህር፡- ድመት የምን መመጠሪያ ነው?

ተማሪ፡- የእንስሳ

መምህር፡- ዘር የምን መጠሪያ ነው ?

ተማሪ፡- የእጽዋት

መምህር፡- እሺ ባለፈው እንደተነጋገርነው "ስም" የምንለው የተለያዩ ነገሮች እና ሁኔታዎች መጠሪያ ነው። እስኪ አሁን ደግሞ ከላይ ያየናቸውን ስሞች ተጠቅማችሁ የየራሣችሁን ዐረፍተ ነገሮች መስርቱ።

2. ማውጣጣት

መምህር፡- የዛሬው ትምህርታችን "ስማዊ ሀረግ" የሚል ነው። ወደ ትምህርቱ በቀጥታ ከመግባታችን በፊት እስኪ የመሠረታችኋቸውን ዓረፍተ ነገሮች እጅ እያወጣችሁ ተናገሩ። ተማሪዎች ከመሠረቷቸው ዓረፍተ ነገሮች የተወሰኑት ፡-

1. ትልቁ ጠረጴዛ ተሰበረ።
2. ጥቁር ድመት አልወድም።
3. መቶ ኩንታል ምርጥ ዘር ለገበሬዎች ተከፋፈለ።

መምህር፡- እስኪ ከእነዚህ ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ስማዊ ሀረግ ናቸው የምትሏቸውን እጅ እያወጣችሁ ተናገሩ

ተማሪዎች ፡- መልሶችን ይሞክራሉ።

3. ገለፃ

መምህሩ ተማሪዎቹ በስማዊ ሀረግ ላይ ያላቸውን ግንዛቤ ከተረዳ በኋላ ገለፃ ይሰጣል።

መምህር፡- በመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ውስጥ ስሙ የትኛው ነው?

ተማሪ፡- ጠረጴዛ

መምህር፡- ምን አይነቱ ጠረጴዛ?

ተማሪ፡- ትልቁ ጠረጴዛ

መምህር፡- "ትልቁ ጠረጴዛ" ብሎ ይፅፋል። ሌሎቹንም ጥያቄዎች በዚሁ መሠረት ይሰራል ።

መምህር፡- የተሰመረባቸውን ስሞች እንመልከት

1. ትልቁ <u>ጠረጴዛ</u> እዚህ ላይ ጠረጴዛ የሚለውን "ትልቁ" የሚለው ቃል ይገልፀዋል። ማለትም የጠረጴዛውን መጠን ይናገራል።

2. ጥቁር <u>ድመት</u> እዚህኛው ላይ "ጥቁር" የሚለው ቃል "ድመት" የሚለውን ይገልፀዋል። ማለትም ምን ዓይነት ድመት እንደሆነ ይነግረናል ።

3. መቶ ኩንታል ምርጥ <u>ዘር</u> እዚህ ላይ ደግሞ "መቶ ኩንታል" የሚለው የዘሩን መጠን እና ምርጥ የሚለው የዘሩን አይነት ይነግሩናል ።

መምህር፡- ተማሪዎች! በዚህ አይነት ሁኔታ "ስም" የሆነ ቃል በመዋቅር ውስጥ መዋቅሩን እየመራ እና ከሚገልፁት ቃላት ወይም ሀረጉች ጋር አብሮ ሲመጣ "ስማዊ ሀረግ" ተብሎ ይጠራል። ከስሙ በፊት መጥተው ስሙን የሚገልጹት ነገሮች "የስም ገላጭ" ተብለው

ይጠራሉ። የበለጠ ግልጽ እንዲሆንልን ከላይ ያቀረብናቸውን ስማዊ ሀረጐች ነጣጥለን እንያቸው።

| የስም ገላጭ | ስም | ስማዊ ሀረግ |
|---|---|---|
| 1. ትልቁ | ጠረጴዛ | ትልቁ ጠረጴዛ |
| 2. ጥቁር | ድመት | ጥቁር ድመት |
| 3. መቶ ኩንታል ምርጥ | ዘር | መቶ ኩንታል ምርጥ ዘር |

4. አፍጽሞ ማፍለቅ

እስካሁን የተማራችሁት ግልጽ እንደሆነላችሁ ለማወቅ በቡድን ሁኑና ከዚህ ቀጥሎ በቀረቡት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ስማዊ ሀረጐች በመለየት ስም እና የስም ገላጭ በማለት አስቀምጡ። ስም፣ የስም ገላጭና ስማዊ ሀረግ ናቸው ያላችሁባቸውን ምክንያቶችም በደብተራችሁ ላይ ፃፉ።

በመምህሩ የቀረቡ ዐረፍተ ነገሮች ፡-

1. የትናንትናው ልጅ ዛሬ አልመጣም።
2. ልጅቷ አለቀሰች።
3. የእግር ኳስ ጨዋታ መመልከት ደስ ይለኛል።
4. የከባድ መኪናው ሾፌር ተቀጣ።

መምህሩ በዚህ ደረጃ የተማሪዎቹን ሙከራ ያያሉ። በጥያቄዎቹ አሰራር ላይ ተማሪዎቹ ግልጽ ያልሆነላቸው ነገር ካለ ያብራራሉ። ግብረ መልስም ይሰጣሉ።

5. ፍልቀራስ

መምህር፡- አሁን ደግሞ የየራሳችሁን አምስት አምስት ስማዊ ሀረጐች በግላችሁ መስርቱና ስማዊ ሀረጉን ፣ የስም ገላጩን እና ስሙን ለይታችሁ አውጡ

| ስማዊ ሀረግ | የስም ገላጭ | ስም |
|---|---|---|
| 1. ____________ | ____________ | ____________ |
| 2. ____________ | ____________ | ____________ |
| 3. ____________ | ____________ | ____________ |
| 4. ____________ | ____________ | ____________ |
| 5. ____________ | ____________ | ____________ |

በዚህ ደረጃ መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ስራ ያያል፡፡ ተማሪዎቹ በእለቱ ትምህርት ላይ የደረሱበትን የግንዛቤ ደረጃ በማየትም ወደ ቀጣዩ ትምህርት ለመሸጋገር ወይም ወደ ኋላ ለመመለስ ይወስናል፡፡

## 2.16 ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ቀደምት ስራዎች

አጥኚው ይዞት ከተነሳው ርዕሰ ጉዳይ ጋር የሚያያዙ ጥናቶችን ለማግኘት ፍለጋ ባደረገበት ወቅት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ ያላቸውን አቀራረብ የሚመለከቱ በርካታ ስራዎች ቢያጋጥሙትም ከአንድ ስራ በስተቀር በቀጥታ "የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ ማስተማር" ከሚለው ጉዳይ ጋር የተያያዙ ጥናቶችን ማግኘት አልቻለም፡፡ ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር የሚያያዘው ጥናት በአበበ መብራቱ (2000 ዓ.ም) የተሰራ ሲሆን የጥናቱ ዋነኛ ዓላማ

> *በወላይታ ዞን በሚገኙ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 9ኛ ክፍል ውስጥ እየተሰጠ ያለው የሰዋሰው ትምህርት ከስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው የሰዋስው ትምህርት አተገባበር አኳያ ምን ያህል ተግባቢነት እንዳለው መፈተሽና በትምህርቱ አተገባበር ላይ የሚታዩትን ጠንካራና ደካማ ጎኖች በመለየት የታዩት ደካማ ጎኖች የሚወገዱበትን የመፍትሄ ሀሳብ መጠቆም*

የሚል ነው፡፡ የጥናቱ ግኝትም፡

> *ጥናቱ በተካሄደበት ዞን ውስጥ እየተሰጠ ያለው የሰዋስው ትምህርት የስነ ትምህርታዊ ሰዋስውን የትምህርት አተገባበር መርህ ያልተከተለ መሆኑና በአገሪቱ የትምህርት ፖሊሲ ውስጥ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ብዙ ትኩረት ባለመስጠቱ የስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው ትምህርት አተገባበር መርህን ተከትሎ ትምህርቱን ማቅረብ አስቸጋሪ መሆኑን ጥናቱ ጠቁሟል/ አበበ 2000፡ ii /ይላል፡፡*

የአበበ ጥናት ትኩረቱን የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ የማስተማር ሁኔታ ምን እንደሚመስል በማሳየት ላይ በማሳረፉ ከእኔ ጥናት ጋር ይመሳሰላል፡፡ ከዚህውጭ ግን ሁለቱ ጥናቶች የሚለያዩባቸው ነጥቦች አሉ፡፡

የመጀመሪያው የአበበ ጥናት ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ ለማስተማር የሚያስችሉ ደረጃዎችን በግልፅ ያላስቀመጠ ሲሆን በእነዚህ ደረጃዎች ላይ በመመስረትም የመምህራኑን የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ አልገመገመም፡፡ የእኔ ጥናት ግን በበርካታ የስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው ምሁራን ተቀባይነት ያገኙትን ደረጃዎች በግልፅ ከማስቀመጡም በላይ በእያንዳንዱ ደረጃ ሰዋስውን ለማስተማር የሚያስችሉ ስልቶችን ዝርዝርም አስቀምጧል፡፡ እነዚህን ደረጃዎች እና ስልቶች መሰረት በማድረግም የመምህራኑን የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ገምግሟል፡፡

ሁለተኛው ልዩነት ደግሞ ሁለቱ ጥናቶች የተካሄዱባቸው የክፍል ደረጃዎች መለያየት ነው፡፡ የአበበ ጥናት የተካሄደው በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ወላይታ ዞን በሚገኙ ወረዳዎች ስር ባሉ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 9ኛ ክፍል ውስጥ ሲሆን የእኔ ጥናት የተካሄደው ግን በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ወሎ ዞን በሚገኙ የከፍተኛ ትምህረት መሰናዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 11ኛ ክፍል ውስጥ ነው፡፡ ጥናቶቹ የተካሄዱባቸው ዘመናት መለያየትም ሌላው ልዩነት ነው፡፡ የአበበ ጥናት በ2000 ዓ.ም የተካሄደ ሲሆን የእኔ ጥናት ግን በ2003 ዓ.ም የተካሄደ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሦስት፡- የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት ከምርምር ዓይነቶች አንዱ የሆነውን ገላጭ የምርምር ዓይነት (Descriptive Study) የተከተለ ነው። ጥናቱ የተካሄደው በሰሜን ወሎ ዞን ስር በሚገኙት የወልድያ መሰናዶ እና የቆቦ አጠቃላይና መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች በ2003 ዓ.ም በ11ኛ ክፍል ውስጥ በሚሰጠው የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ትምህርት ላይ ሲሆን÷ የተጠኝዎች ናሙና አወሳሰድ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪዎች መረጣ እና የመረጃዎች አደረጃጀትና ትንተና በሚከተለው መልኩ ተከናውኗል።

## 3.1 የትምህርት ቤቶች፣ የመምህራን እና የመማሪያ ክፍሎች ናሙና አወሳሰድ

በሰሜን ወሎ ዞን ስር አሥር የከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ ሁለቱ (20%ቱ) ለአጥኝው ካላቸው አመችነት አኳያ ታይተው ተመርጠዋል። እነዚህም የወልድያ መሰናዶ እና የቆቦ አጠቃላይና መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ናቸው። በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎችን የሚያስተምሩ በወልድያ ሦስት እና በቆቦ ሦስት በድምሩ ስድስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚገኙ ሲሆን ከእነዚህ መካከል ከእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ሁለት በድምሩ አራት መምህራን በእጣ ናሙና አወሳሰድ ዘዴ ተመርጠዋል። የመማሪያ ክፍሎችን በተመለከተም እነዚህ በናሙናነት የተመረጡ መምህራን ከሚያስተምሩባቸው የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ በእጣ የናሙና አወሳሰድ ዘዴ አንድ አንድ በመውሰድ በድምሩ አራት የመማሪያ ክፍሎች ተመርጠዋል። ከእነዚህ አራት የመማሪያ ክፍሎች በእያንዳንዱ ክፍል ሁለት ጊዜ በድምሩ ስምንት ጊዜ በተደረገ የክፍል ውስጥ ምልከታ እና ከሁሉም በናሙናት ከተመረጡት መምህራን ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ አማካይነት መረጃዎች ተሰብስበው ጥናቱ ተካሂዷል።

## 3.2 የመረጃ መሰብቢያ መሳሪያዎች እና ዘዴዎች

ለዚህ ጥናት በዋነኛነት አገልግሎት ላይ የዋለው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ምልከታ ሲሆን ቃለ መጠይቅና የሰነድ ፍተሻ በደጋፊነት አገልግለዋል። በእነዚህ መሳሪዎች አማካይነትም መረጃዎቹ በሚከተለው መልኩ ተሰብስበዋል።

### 3.2.1 ምልከታ

ምልከታ የዚህ ጥናት ዋነኛው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሲሆን በናሙናነት በተመረጡት አራት የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ የሰዋስው ትምህርት በሚሰጥባቸው ክፍለ ጊዜያት በእያንዳንዳቸው ሁለት ጊዜ በድምሩ ስምንት ጊዜ በመገኘት ምልከታ ተካሂዷል። የጥናቱን ዓላማዎች እና በምዕራፍ ሁለት የቀረበውን የሰዋስው ትምህርት ትንታኔ መሰረት አድርጎ የተዘጋጀውን ቅጽ

(cheek list) በመገልገልም በመምህሩ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ላይ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

### 3.2.2 ቃለ መጠይቅ

የመምህራኑን ሰዋስውን በተግባቦታዊ መንገድ በማስተማር ላይ ያላቸውን ግንዛቤ እና የክፍል ውስጥ አተገባበራቸውን ለማወቅ የሚያስችሉ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት በናሙናነት ከተመረጡት መምህራን ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

### 3.2.3 የሰነድ ፍተሻ

በ2003 ዓ.ም የ11ኛ ክፍል ተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ለማስተማር በስራ ላይ ያሉ ሰነዶችን ማለትም መርሃ ትምህርቱን፣ የተማሪው መማሪያ መጽሀፍን እና የመምህሩ መመሪያን በመሰብሰብ በተለይ የሰዋስው ትምህርትን ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር በማቀናጀት እና ተግባቦታዊ በሆነ አቀራረብ ለማስተማር በሚያስችል መልኩ መዘጋጀታቸው ተፈትሿል፡፡

## 3.3 የመረጃ አደረጃጀትና ትንተና

ከዚህ በላይ በቀረቡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችና ዘዴዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች የተገኙበትን ምንጭ መሰረት በማድረግ ማለትም በምልከታ የተገኙ፣ በቃለ መጠይቅ የተገኙ እና በሰነድ ፍተሻ የተገኙ ተብለው በየፈርጃቸው ከተቀመጡ በኋላ በእያንዳንዱ ፈርጅ ስር በተቀመጡ ዝርዝር የመገምገሚያ ነጥቦች አማካኝነት የጥናቱን ዝርዝር ዓላማዎች እና በምዕራፍ ሁለት የቀረቡትን ንድፈ ሀሳባዊ መረጃዎች መሰረት በማድረግ በጥልቀት ተተንትነዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንተና እና የጥናቱ ውጤት

በዚህ የጥናቱ ክፍል በወልድያ መሰናዶ እና በቆቦ አጠቃላይና መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 11ኛ ክፍል ውስጥ ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ የማስተማር ሁኔታን አስመልክቶ የተሰበሰቡ መረጃዎች ይተነተናሉ። መረጃዎቹ የተሰበሰቡት በሦስት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ሲሆን እነዚህም የክፍል ውስጥ ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ እና የሰነድ ፍተሻ ናቸው። በምልከታ ፥ ለጥናቱ በተመረጡት የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ በመገኘት በመምህራን የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ላይ፣ በቃለ መጠይቅ ፥ ከመምህራኑ ጋር በተደረገ ውይይት እና በሰነድ ፍተሻ ፥ ለክፍል ደረጃው ከተዘጋጁት የመማሪያና የማስተማሪያ መሳሪያዎች ማለትም ከመርሃ ትምህርቱ፣ ከተማሪው መጽሐፍ እና ከመምህሩ መመሪያ መረጃዎች ተሰብስበዋል። በእነዚህ ዘዴዎች አማካኝነት የተሰበሰቡት መረጃዎች ትንተና ከዚህ ቀጥሎ ይቀርባል።

## 4.1 በምልከታ በመምህራን የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ላይ የተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና

ለዚህ ጥናት አገልግሎት ላይ ከዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መካከል አንዱና ዋነኛው ምልከታ ነው። ይህን ዘዴ በመጠቀም በናሙናነት የተመረጡት አራት መምህራን በሚያስተምሩባቸው አራት የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ በመገኘት በእያንዳንዱ መምህር እና የመማሪያ ክፍል ሁለት ጊዜ በድምሩ ስምንት ጊዜ ምልከታ በማካሄድ በመምህራኑ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ላይ እና መምህራኑ ባዘጋጇቸው ዕለታዊ የትምህርት ዕቅዶች ላይ መረጃ ተሰብስቧል። መረጃውን ለመሰብሰብ፣ ምልከታው ከመካሄዱ ቀደም ብሎ የተዘጋጀ ቅጽ በመሳሪያነት አገልግሏል። ይህ ቅጽ የተዘጋጀው በምዕራፍ ሁለት ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ ማስተማርን እና የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ቅደም ተከተሎችን አስመልክቶ የቀረቡትን ንድፈ ሀሳባዊ እሳቤዎች መሠረት አድርጎ ነው። ቅጹ በጠቅላላው በአራት ዋና ዋና ርዕሰ ጉዳዩች ስር የተካተቱ ሃያ ሁለት ነጥቦችን የያዘ ሲሆን እነዚህ ነጥቦች ለትንተና እንዲያመቹ በማሰብ በሚከተለው መልኩ ተጠቃለዋል። እነዚህም

1. መምህሩ በእለታዊ የትምህርት እቅዱ ውስጥ የሰዋስው ትምህርቱን አላማ በተገቢው ሁኔታ መግለጹ፣
2. መምህሩ ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ ለማስተማር የሚያስችሉ ደረጃዎችን ማለትም
    - ማቅረቢያ
    - ማውጣጣት
    - ገለፃ
    - አፍዕሞ ማፍለቅ እና
    - ፍልቀራስ የሚሉትን ጠብቆ የማስተማሩ ሁኔታ፣

3. የሰዋስው ትምህርቱ ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅቶ የመቅረቡ ሁኔታ፣

4. መምህሩ የሰዋስው ይዘቶችን በትክክል የማስተማሩ ሁኔታ፣

5. የሰዋስው ትምህርት ሂደቱ አብዛኛውን ተማሪ የማሳተፉ ሁኔታ እና

6. የሰዋስው ትምህርት ክፍሉ ድባብ ምን ይመስላል? የሚሉ ናቸው።

እነዚህን የመገምገሚያ ነጥቦች መሰረት በማድረግም መምህራኑ ሰዋስውን በሚያስተምሩበት ወቅት የተሰበሰቡት መረጃዎች ከእያንዳንዱ መምህር አኳያ በጥልቀት ተተንትነዋል።

### 4.1.1 መምህር አንድ

*የመምህሩ ዳራ እና በምልከታው ወቅት የተከተሏቸው የማስተማር ሂደቶች*

መምህር አንድ በወልድያ የከፍተኛ ትምህርት መሠናዶ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 11ኛ ክፍል ውስጥ አማርኛን ከሚያስተምሩ ሦስት መምህራን መካከል ለዚህ ጥናት የተመረጡ አንደኛው መምህር ናቸው። መምህሩ በቋንቋው የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ሲሆን በዚሁ ሞያቸው የሰባት ዓመታት የማስተማር ልምድ አላቸው። ከዚህ ውስጥ ለአራት ዓመታት ያክል በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያስተማሩ ሲሆን ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ ከላይ በተገለጸው ትምህርት ቤት 11ኛና 12ኛ ክፍሎች ውስጥ አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ላይ ይገኛሉ።

መምህሩ ከሚያስተምሩባቸው የ11ኛ ክፍል ሴክሽኖች መካከል 11ኛ A ተመርጦ በዚሁ የመማሪያ ክፍል ውስጥ ሁለት ጊዜ በመገኘትና ለምልከታ የተዘጋጀውን ቅጽ በመጠቀም በመምህሩ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ላይ መረጃ ተሰብስቧል። በምልከታዎቹ ወቅት ማየት እንደተቻለው መምህሩ የየዕለቶቹን የሰዋስው ትምህርቶች በሚከተለው መልኩ አቅርበዋቸዋል።

#### ምልከታ ሀ

በመምህር አንድ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ላይ የመጀመሪያው ምልከታ የተካሄደው በ13/03/2003 ዓ.ም ከጠዋቱ 2፡50 ሰዓት ጀምሮ ነው። መምህሩ በሰዓቱ ክፍል ውስጥ ተገኝተዋል። የዕለቱን የትምህርት ዕቅድ አዘጋጅተው አምጥተዋል። አጥኚውም የትምህርት እቅዱን ተቀብሏል።

#### ትምህርቱ ተጀመረ

መምህሩ ለተማሪዎቹ ሰላምታ ከሰጡ በኋላ ያለፈው ክፍለ ጊዜ ትምህርት ስለ "የአንቀጽ ማስፋፊያ ዘዴዎች" እንደነበር አስታውሰው ተማሪዎቹ ስለ ማስፋፊያ ዘዴዎች የሚያስታውሱትን እንዲናገሩ እድል ሰጡ። ሁለት ተማሪዎች መልስ ሰጡ። መምህሩም የተማሪዎቹ መልሶች ትክክል መሆናቸውን ተናገሩ። ከዚያም የዕለቱ የትምህርት ርዕስ "ምዕላድ" የሚል መሆኑን ገልፀው በጥቁር ሰሌዳው ላይ ከፃፉ በኋላ ተማሪዎቹ በርዕስ ጉዳዩ

ላይ የሚያውቁት ነገር ካለ ሀሳባቸውን እንዲገልጹ ጠየቁ። ሁለት ተማሪዎች መልስ ሰጡ። መምህሩም በምዕላድ ምንነት ላይ ለ10 ደቂቃዎች ያክል በምሳሌ የተደገፈ ማብራሪያ ሰጡ። ማብራሪያውን ሲጨርሱም፣ ያልገባቸውን እንዲጠይቁ ለተማሪዎቹ እድል ሰጡ። ነገር ግን የጠየቀ ተማሪ የለም። በመቀጠልም ስለ ነፃ እና ጥገኛ ምዕላዶች እንዲሁም ስለ የእርባታ እና የምስረታ ምዕላዶች ለ11 ደቂቃዎች ያክል በምሳሌ የተደገፈ ማብራሪያ ሰጡ። ማብራሪያውን ሲጨርሱም ያልገባቸውን እንዲጠይቁ ለተማሪዎቹ እድል ሰጡ። ሦስት ተማሪዎች ጠየቁ። መምህሩም መልስ ሰጡ።

በገለፃውና በማብራሪያው ወቅት መምህሩ በጥቁር ሰሌዳው ላይ እየፃፉ የተጠቀሙባቸው እና ተማሪዎቹ በደብተራቸው የገለበጧቸው ምሳሌዎች የሚከተሉት ናቸው።

ምዕላድ

ትርጉም አዘል የሆነ ነገር ግን ወደ ሌላ ትርጉም አዘል አካል ሊከፈል የማይችል የቋንቋ አንድ ቅንጣት (አሀድ) ነው።

ምሳሌ፡- ሴቶች ……. ሴት-ኦች

ምዕላድን ስንጠራ - ነፃ ምዕላድ

- እስር (ጥገኛ) ምዕላድ ብለን እንጠራለን።

*ነፃ ምዕላድ*፡- ራሱን ችሎ የሚቆምና ቃል መሆን የሚችል ነው።

*ጥገኛ ምዕላድ*፡- ራሱን ችሎ መቆም የማይችልና ወደ ነፃ ምዕላድ መጠጋት የሚፈልግ ነው።

የምዕላድ አመዳደብ

ምዕላድን በሁለት ከፍለን እንመድባለን።

1. የእርባታ ምዕላድ፡- የምንላቸው የቃል ክፍሉን አይለውጡም። ቁጥርን፣ ፆታን፣ መደብንና ዕምርነትን የሚያመለክቱ ምዕላዶች ናቸው።

   *ምሳሌ፡- ለቁጥር* *ቤቶች….. ቤት- ኦች*

   *- ለፆታ* *ልጂት…… ልጅ- ኢት*

   *- ለመደብ* *እናቴ…. እናት- ኤ*

   *- ለዕምርነት* *ቤቱ……. ቤት- ኡ*

2. የምስረታ ምዕላድ፡- የቃል ክፍሉን የሚለውጡ ምዕላዶች ናቸው። ቃል ለዋጭ ምዕላድም ይባላሉ።

   *ምሳሌ፡- - ክፉ( ቅፅል) + ኛ …….. ክፉኛ( ተውሳከ ግስ)*

   *- ተራራ (ቅጽል) +ማ ……. ተራራማ ( ቅፅል)*

በማስከተልም መምህሩ የተወሰኑ ቃላትን በጥቁር ሰሌዳው ላይ ከፃፉ በኋላ ተማሪዎቹ በደብተራቸው ላይ ገልብጠው በግላቸው በቃላቱ ውስጥ ያሉትን ምዕላዶች እየነጣጠሉ ነፃ እና ጥገኛ የሆኑትን እንዲያመለክቱ አዘዙ፡፡

እንዲተነተኑ የቀረቡ ቃላት፡- ልጅነት ኢትዮጵያዊ ተሜዎቻች ልብስ

ጎጃሜ ውሃማ አዝመራ በሬዎች

ተማሪዎቹ ለ 7 ደቂቃዎች ያክል በግላቸው በቃላቱ ውስጥ ያሉትን ምዕላዶች እየነጣጠሉ አስቀመጡ፡፡ ከዚያም ከመምህሩ ጋር እየተወያዩ ለ6 ደቂቃዎች ያክል ቃላቱን አንድ ባንድ ሰሩ፡፡ በዚህም የዕለቱ ትምህርት ተጠናቀቀ፡፡ የዕለቱን ትምህርት ለማቅረብ ባጠቃላይ 39 ደቂቃዎችን የወሰደ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 21 ደቂቃው በመምህሩ ገለፃ የተሸፈነ ነው፡፡

## ምልከታ ለ

በመምህር አንድ ላይ ሁለተኛው ምልከታ የተካሄደው በ15/03/2003 ዓ.ም ከሰዓት በኋላ ከ6፡45 ሰዓት ጀምሮ ነው፡፡ መምህሩ በሰዓቱ ክፍል ውስጥ ተገኝተዋል፡፡ የዕለቱን የትምህርት ዕቅድ አዘጋጅተው አምጥተዋል፡፡ አጥኚውም የትምህርት እቅዱን ተቀብሏል፡፡

## ትምህርቱ ተጀመረ

መምህሩ ለተማሪዎቹ ሰላምታ ከሰጡ በኋላ ስለ "የአማርኛ ቋንቋ የቃላት ክፍሎች" የሚያውቁትን እንዲመልሱ ተማሪዎቹን ጠየቁ፡፡ አንድ ተማሪ እጁን አውጥቶ እድል ስለተሰጠው መልስ ሰጠ፡፡ ከዚያም መምህሩ የዕለቱ ትምህርት ርዕስ "ሀረግ" የሚል መሆኑን ገልፀው በጥቁር ሰሌዳው ላይ ከፃፉ በኋላ ስለ "ሀረግ ምንነት እና አመሰራረት" ማብራሪያ ሰጡ፡፡ በመቀጠልም አምስቱን የሀረግ ዓይነቶች አንድ በአንድ እየዘረዘሩ ለ30 ደቂቃዎች ያክል በምሳሌ የተደገፈ ገለፃ አደረጉ፡፡ መምህሩ በገለፃቸው ወቅት ሰሌዳው ላይ እየፃፉ የተጠቀሙባቸው እና ተማሪዎቹ በደብተራቸው የገለበጧቸው ምሳሌዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

<u>የአማርኛ ቋንቋ የሀረግ ዓይነቶች</u>

1. *ስማዊ ሀረግ*
2. *ቅጽላዊ ሀረግ*
3. *ግሳዊ ሀረግ*
4. *ተውሳከ ግሳዊ ሀረግ*
5. *መስተዋድዳዊ ሀረግ*

ሀረግ ከአንድ በላይ ተዋቃሪ አካላት ይዞ ይመሰረታል፡፡

- ስም ከስም ጋር ሊዋቀር ይችላል
- ስም ከግስ ጋር ሊዋቀር ይችላል

- ስም ከቅጽል ጋር ሊዋቀር ይችላል
- ቅጽል ከቅጽል ጋር ሊዋቀር ይችላል

የሚዋቀሩት አካላት፡- 1. መሪ

2. መሙያ እና

3. አጃቢ ናቸው፡፡

ሀረግ፡- ቃላት ተቀናጅተው የሚመሰርቱት ሠፊ መዋቅር ነው፡፡

## በሀረግ ውስጥ መሪን እንዴት መለየት ይቻላል?

ከመስተዋድዳዊ ሀረግ ውጭ ያሉት አራቱ የሀረግ ዓይነቶች መሪያቸው በሙሉ በቀኝ በኩል ይገኛል፡፡ ነገር ግን የመስተዋድዳዊ ሀረግ መሪ በቀኝም ሆነ በግራም ይገኛል፡፡

1. ስማዊ ሀረግ፡- መሪው ስም የሆነ

ምሳሌ፡- - ቀዩ ልጅ

- የወንድሜ ልጅ

የተሰመረባቸው ቃላት የስማዊ ሀረግ መሪ ናቸው፡፡

2. ቅጽላዊ ሀረግ፡- መሪው ቅጽል የሆነ

ምሳሌ፡ የልጅ አዋቂ

አስቴር በጣም ጎበዝ ተማሪ ነች

ትርሲት በጣም ቆንጆ ነች

3. መስተዋድዳዊ ሀረግ

ከጓደኛው

ከዛፍ ላይ

ወደ ቤቱ

4. ተውሳከ ግሳዊ ሀረግ

| ነባር | ውልድ |
|---|---|
| - ቶሎ | - ክፉኛ |
| - ገና | - ጅልኛ |
| | - ምንኛ |

ምሳሌ፡- - ተማሪዎቹ ክፉኛ ተጎዱ፡፡

- ሰዓቱ ገና ነው፡፡

I. ከዚህ በታች የቀረቡት የተሰመረባቸው ቃላት የሚመሰርቱትን የሀረግ አይነት አመልክቱ፡፡

1. ልብሱን ለብሶ ሄደ = ግሳዊ ሀረግ
2. ከኤድስ ቫይረስ ጋር = መስተዋድዳዊ ሀረግ

3. የስነ-ፅሁፍ <u>መምህር</u> = ስማዊ ሀረግ

4. ተማሪዎቹ <u>ከፉኛ</u> = ተውሳከ ግሳዊ ሀረግ

5. በጣም <u>የዋህ</u> = ቅጽላዊ ሀረግ

II. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች ስማዊና ግሳዊ ሀረግ ለይታችሁ አውጡ።

1. <u>ዳምጠው የገዛው በግ</u> / <u>ትላንት ተሰረቀ</u>።

   ስማዊ ሀረግ ግሳዊ ሀረግ

2. <u>እኔ የገዛሁት መኪና</u> / <u>ጠፋ</u>

   ስማዊ ሀረግ ግሳዊ ሀረግ

3. <u>አየለ</u> / <u>አበበ እንደታመመ ሰማ</u>።

   ስማዊ ሀረግ ግሳዊ ሀረግ

መምህሩ ገለፃቸውን ሲጨርሱም ለክፍሉ ተማሪዎች በጋራ አንድ ጥያቄ ጠየቁ። ጥያቄውም "በሀረግ ውስጥ መሪውን እንዴት መለየት ይቻላል?" የሚል ነው። እጃቸውን ካወጡት መካከል ሦስት ተማሪዎች ዕድል ስለተሰጣቸው መልስ ሰጡ። መምህሩም በተማሪዎቹ መልሶች ላይ አስተያየት ከሰጡ በኋላ ተማሪዎቹ በየዴስካቸው በቡድን ተደራጅተው በመማሪያ መጽሀፉ ከገጽ 56-57 ያሉትን ጥያቄዎች እንዲሰሩ አዘዙ። ተማሪዎቹም በታዘዙት መሰረት ለ5 ደቂቃዎች ያክል እንደሰሩ የክፍለ ጊዜውን መጠናቀቅ የሚያበስረው ደወል ተሰማ። መምህሩም ጥያቄዎቹን በቤት ስራ እንዲሰሯቸው ለተማሪዎቹ ነግረው የዕለቱ ትምህርት ተጠናቀቀ። የዕለቱን ትምህርት ለማቅረብ በአጠቃላይ 38 ደቂቃዎችን የወሰደ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 30 ደቂቃው የተሸፈነው በመምህሩ ገለፃ ነው።

## ትንተና

*1. መምህሩ በትምህርት እቅዱ ውስጥ የሰዋስው ትምህርቱን ዓላማ በተገቢ ሁኔታ መግለፁ፡-* መምህር አንድ ምልከታ በተካሄደባቸው ሁለት ክፍለ ጊዜያት ባዘጋጁቸው ዕለታዊ የትምህርት እቅዶች ውስጥ በእያንዳንዳቸው ሦስት ሦስት ዓላማዎችን ገልፀዋል። በመጀመሪያው ዕቅድ ውስጥ ያሉት ዓላማዎች "ተማሪዎቹ ከዚህ ትምህርት በኋላ የምዕላድን ምንነት ይገልፃሉ"፣ "ምዕላድን ከእርባታና ከምስረታ አንፃር ይመድባሉ" እና "ምእላዶችን ከአገልግሎት አንፃር ይተነትናሉ" የሚሉ ሲሆኑ በሁለተኛው እቅድ ውስጥ ያሉት ደግሞ "የአማርኛ ቋንቋ የሀረግ ዓይነቶችን ይለያሉ"፣ "ከሀረግ ውስጥ መሪና ተዋቃሪ አካላትን ለይተው ያወጣሉ" እና "ከዓረፍተ ነገር ውስጥ የስማዊ እና የግሳዊ ክፍልን ይዘረዝራሉ" የሚሉ ናቸው።

በእነዚህ የዓላማ ገለፃዎች ውስጥ "ይገልፃሉ"፣ "ይመደባሉ"፣ "ይተነትናሉ"፣ "ይለያሉ"፣ "ለይተው ያወጣሉ" እና "ይዘረዝራሉ" የሚሉ ቃላት ይገኛሉ። እነዚህ ቃላት ተማሪዎቹ

ለትምህርት የቀረበውን ሰዋስዋዊ ይዘት ከተማሩ በኋላ የሚያከናውኗቸውን ተግባራት የሚገልፁ ሲሆኑ ተማሪዎቹ የተማሩትን መረዳት አለመረዳታቸውን ለማወቅም ያስችላሉ። ቃላቱ የየዕለቶቹን የሰዋስው ትምህርት ዓላማዎች ዝርዝር እና ተጨባጭ በሆነ መልኩ ይገልፃሉ። ከእነዚህ ቃላት ጋር በየዓላማ ገለፃዎቹ ውስጥ የገቡት ሌሎች ቃላትና ሀረጋትም ተገቢነት ያላቸው ሲሆኑ በሰዋስው ትምህርት ክፍለ ጊዜያቱ በዋነኛነት ምን ምን ተግባራትን ለማከናወን እንደታሰበ ያሳያሉ። ነገር ግን እነዚህ የአላማ ገለፃዎች የሚጠቁሙት ተማሪዎቹ በግልፅ ከሚቀርብ የሰዋስው ትምህርት በኋላ የሚያዳብሩትን ሰዋስዋዊ እውቀት ብቻ ነው። በክለሳ ድርሳኑ ክፍል እንደተነጋገርነው አላማዎቹ መጠቆም ያለባቸው ይህን ብቻ ሳይሆን ሰዋስው ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅቶ ሲቀርብ ተማሪዎቹ ሊያዳብሩት የሚችሉትን ተግባቦታዊ ችሎታም መሆን አለበት። ስለዚህም መምህር አንድ ለሁለቱም ክፍለ ጊዜያት ባዘጋጇቸው የትምህርት እቅዶች ውስጥ ያቀረቧቸው የሰዋስው ትምህርት ዓላማዎች ከፊል ተገቢነት አላቸው ማለት ይቻላል።

*2. መምህሩ ሰዋስውን በተግባቦታዊ መንገድ ለማስተማር የሚያስችሉ ደረጃዎችን ጠብቆ የማስተማሩ ሁኔታ፡-* ቀደም ሲል በክለሳ ድርሳኑ ክፍል በዝርዝር እንዳየነው ሰዋስውን በተግባቦታዊ መንገድ ለማስተማር የሚያስችሉ አምስት ደረጃዎች አሉ። ስለዚህም የመምህሩን የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ከእነዚህ ደረጃዎች አኳያ አንድ በአንድ ማየት ያስፈልጋል።

*ማቅረቢያ፡-* መምህር አንድ በሁለቱም ክፍለ ጊዜያት ትምህርቱን የጀመሩት ተማሪዎቹ በቀደሙት ክፍለ ጊዜያት ስለተማሩአቸው ርዕሰ ጉዳዮች አስታውሰው እንዲመልሱ (በመጀመሪያው ክፍለ ጊዜ ስለ አንቀጽ ማስፋፊያ ዘዴዎች እና በሁለተኛው ክፍለ ጊዜ ስለአማርኛ የቃላት ክፍሎች) በመጠየቅ ነው። ወደየዕለቶቹ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የተሸጋገሩትም ይዘቶቹን በቀጥታ በማስተዋወቅ ነው።

ነገር ግን ቀደም ሲል እንደተገለፀው በዚህ ደረጃ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች መቅረብ ያለባቸው በቀጥታ ራሳቸውን ችለው ሳይሆን በአውድ ውስጥ ተካተው ነው። በሰዋስዋዊ ይዘቶቹ ላይ ለተማሪዎቹ የሚሰጠው ማብራሪያም አውዱን መሰረት ያደረገ ሆኖ ይዘቶቹ የሚሸከሙትን ፍች እና አጠቃቀማቸውን የሚያስረዳ መሆን አለበት። እነዚህ ሁኔታዎች ግን ምልከታ በተካሄደባቸው ሁለት ክፍለ ጊዜያት በመምህር አንድ ሲተገበሩ አልታዩም። ስለዚህም መምህር አንድ ተግባቦትን ታሳቢ በማድረግና የሰዋስው ይዘቱን በአውድ ውስጥ በማካተት ትምህርቱን በአግባቡ አለመጀመራቸውን መረዳት ይቻላል።

*ማውጣጣት፡-* ይህ ደረጃ ተማሪዎቹ ለትምህርት በቀረበው ሰዋስዋዊ ይዘት ላይ ያላቸውን የቀደመ እውቀት ለማወቅ ጥረት የሚደረግበት ነው። ለዚህም የተለያዩ ስልቶችን መጠቀም

ይቻላል፡፡ ተማሪዎቹ አዲሱን ሰዋስዋዊ ይዘት ተጠቅመው ከራሳቸው በሚያፈልቋቸው ዓረፍተ ነገሮች ሀሳባቸውን እንዲገልፁ ማድረግ እና በአውድ ውስጥ የቀረበውን ሰዋስዋዊ ይዘት ነጥለው እንዲያሳዩ ማድረግ በዚህ ደረጃ የሚተገበሩ ዋነኛ ስልቶች ናቸው፡፡

ከእነዚህ ስልቶች አኳያ የመምህር አንድን የሰዋስው ትምህርት አተገባበር ስንገመግም በትክክል አለመፈፀሙን መረዳት እንችላለን፡፡ መምህሩ በመጀመሪያው ምልከታ ወቅት ስለ "ምዕላድ ምንነት" ተማሪዎቹን የጠየቁ ቢሆንም መጀመሪያውኑ ይዘቱ በአውድ ውስጥ ተካቶ ባለመቅረቡ አጠያየቁ ተግባቦትን ታሳቢ ያደረገ ሳይሆን ፅንሰ ሀሳባዊ ግንዛቤን የሚጠይቅ ነው፡፡ የተማሪዎቹ አመላለስም ሰዋስዋዊ ይዘቱ በተግባቦት ሂደት ውስጥ እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል የሚያሳይ ሳይሆን እንደ አጠያየቁ ሁሉ በይዘቱ ላይ ያላቸውን ፅንሰ ሀሳባዊ የግንዛቤ ደረጃ የሚያሳይ ነው፡፡ በሁለተኛው ምልከታ ወቅት ግን ከነጭራሹ መምህሩ በእለቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘት (ሀረግ) ላይ ጥያቄ አልሰነዘሩም፡፡ ተማሪዎቹ ባለፈው ክፍለ ጊዜ የተማሩትን እንዲያስታውሱ ካደረጉ በኋላ በቀጥታ በሀረግ ምንነት እና አመሰራረት ላይ ማብራሪያ በመስጠት ትምህርቱን ቀጥለዋል፡፡ ከእነዚህ ሁኔታዎች በመነሳት መምህር አንድ የማውጣጣት ደረጃን በአግባቡ አልተገበሩትም ማለት ይቻላል፡፡

ገለፃ፡- በሁለቱም ምልከታዎች ወቅት ማየት እንደተቻለው መምህሩ በየዕለቶቹ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ላይ በምሳሌ የተደገፉ ሰፋፊ ገለፃዎችን በማድረግ አስተምረዋል፡፡ መምህሩ የተከተሉት ውጤት ተኮር የሆነውን ሰዋስውን የማስተማሪያ ዘዴ በመሆኑ በሁለቱም ክፍለ ጊዜያት ትምህርቱ የቀረበው በገለፃ ነው፡፡ እንዲህም ሆኖ ደረጃው ሙሉ በሙሉ ተተግብሯ ማለት አይቻልም፡፡ ለዚህም ምክንያቶች አሉ፡፡ የመጀመሪያው መምህሩ ገለፃዎቹን ያካሄዱት የማውጣጣት ደረጃን ተጠቅመው የተማሪዎቹን የግንዛቤ ደረጃ በማወቅና በዚያ ላይ በመመስረት አይደለም፡፡ ሁለተኛም የየዕለቶቹ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አውድ ተፈጥሯቸው ስላልቀረቡ መምህሩ ገለፃዎቹን ያካሄዱት አውድን በመጠቀምና ተግባቦትን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ሳይሆን ውጤት ተኮር የማስተማር ዘዴን በመከተል ነው፡፡ ስለዚህም ይህ ደረጃ በመምህሩ በከፊል ተተግብሯል ማለት ይቻላል፡፡

አፍፅሞ ማፍለቅ፡- ይህ ደረጃ ተማሪዎቹ በተማሩት ሰዋስዋዊ ይዘት ላይ በጋራ፣ በግል እና በጥንድ ልምምድ የሚያደርጉበት ሲሆን የሰዋስው ትምህርቱ በተማሪቹ እንዲሰርጽ እና ተጨባጭ እንዲሆን ያስችላል፡፡ የመምህር አንድን አቀራረብ ከዚህ ደረጃ አኳያ ስናይ በመጀመሪያው ምልከታ ወቅት በምዕላድ ምንነትና ክፍሎች ላይ ገለፃ ካደረጉ በኋላ የተወሰኑ ቃላትን በመስጠት ተማሪዎቹ በግላቸው ነፃ እና ጥገኛ ምዕላዶችን እየለዩ እንዲያስቀምጡ አድርገዋል፡፡ ተማሪዎቹ ሰርተው ሲጨርሱም በጋራ እያወያዩ ጥያቄዎቹን ሰርተውላቸዋል፡፡

በሁለተኛው ምልከታ ወቅት ግን በሀረግ ላይ ገለፃ ካቀረቡ በኋላ ተማሪዎቹ በቡድን ሆነው በጥያቄዎች ላይ እንዲወያዩ ትዕዛዝ ቢሰጡም ተማሪዎቹ ስራቸውን ሳይጨርሱ እና ከመምህሩ ጋርም በጋራ ሳይወያዩ የዕለቱ ክፍለ ጊዜ ተጠናቋል። ከእነዚህ ሁኔታዎች በመነሳት መምህር አንድ ይህን ደረጃ በከፊል ተግብረውታል ማለት ይቻላል።

ፍልቀራስ፡- ይህ ደረጃ የሰዋስው ትምህርት ሂደት የመጨረሻ ደረጃ ሲሆን ተማሪዎቹ የቀረበላቸውን የሰዋስው ትምህርት መረዳት አለመረዳታቸው የሚረጋገጥበት ነው። መረዳት አለመረዳታቸው የሚታወቀው የተማሩትን ሰዋስዋዊ ይዘት ተጠቅመው ከራሳቸው አፍልቀው ሀሳባቸውን እንዲገልፁ የሚያስችሉ ተግባራትን በመስጠት ነው። ትክክለኛ አወቃቀር፣ አጠቃቀምና ፍች የያዙ መዋቅሮችን መመስረት ሲችሉ የሰዋስው ትምህርቱን መረዳታቸው ይረጋገጣል። ደረጃው በሰዋስው ትምህርት ሂደት ውስጥ ወሳኝ ሚና ያለው ቢሆንም በሁለቱም ምልከታዎች ማየት እንደተቻለው በመምህሩ አልተተገበረም።

*3. የሰዋስው ትምህርቱ ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅቶ የመቅረቡ ሁኔታ፡-*

በክለሳ ድርሳኑ ክፍል እንደተገለፀው የሰዋስው ትምህርት ሂደት ተግባቦታዊ ነው የሚባለው ሰዋስዋዊ ይዘቱ አውድ ተፈጥሮለት እና ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅቶ ሲቀርብ ነው። ከዚህ አኳያ የመምህር አንድን አቀራረብ ስንቃኘው ችግር ይታይበታል። ይኸውም በሁለቱም ክፍለ ጊዜያት ማየት እንደተቻለው ሰዋስዋዊ ይዘቶቹን በአውድ ውስጥ አካተው አላቀረቡም፤ ሰዋስዋዊ ይዘቶቹን ለተማሪዎቹ ያስተማሩትም ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር እያቀናጁ ሳይሆን የውጤት ተኮር ዘዴን በመከተል ቀጥተኛ የሆነ ገለፃና ማብራሪያ በመስጠት ነው።

**4.መምህሩ የሰዋስው ይዘቶችን በትክክል የማስተማሩ ሁኔታ፡-** ቀደም ሲል እንደተገለፀው መምህር አንድ በሁለቱም ክፍለ ጊዜያት የሰዋስው ትምህርቱን በገለፃ አቅርበዋል። ትምህርቱን በገለፃ ሲያቀርቡም ተገቢነት የሌላቸውን ሃሳቦች ለተማሪዎቹ አስተላልፈዋል። እነዚህም የሚከተሉት ናቸው።

በመጀመሪያው ምልከታ ያሉትን ስናይ "ጥገኛ ምዕላድ" የሚለውን ሲያብራሩ "ወደ ነፃ ምዕላድ መጠጋት የሚፈልግ ነው" የሚል ማብራሪያ ሰጥተዋል። ነገር ግን ጥገኛ ምዕላድ መጠጋት የሚፈልገው ወደ ነፃ ምዕላድ ብቻ አይደለም። ወደ ቃላትም ሊጠጋ ይችላል። ቃላት ደግ ቀደም ሲል እንደተገለፀው ነፃ ምዕላድ ሊሆኑም ላይሆኑም ይችላሉ። አንዳንዶቹ በውስጣቸው ከአንድ በላይ ምዕላዶችን ሊይዙ ይችላሉ። ጥገኛ ምዕላዶችን ሊያስጠጉም ይችላሉ።

ምሳሌ፡- ልጆች - ኡ

"የእርባታ ምዕላድ" በሚለው ርዕስ ስርም መደብ አመልካች ምዕላድን ለማስረዳት

እናቴ ... እናት -ኤ የሚል ምሳሌ አቅርበው "ኤ" መደብ አመልካች ምዕላድ ነው ብለዋል፡፡ ምንም እንኳን "የእኔ እናት" የሚለው ቃል "እኔ" በሚለው ተውላጠ ስም እማካኝነት መደቡ ይታወቃል ለማለት ቢቻልም "ኤ" የሚለው ምዕላድ በቀጥታ የሚያመለክተው ግን ባለንብረትነትን ነው፡፡ ስለዚህም ዘርፍ ነው፡፡ ይህንን ግን መምህሩ አልገለፁም፡፡

የምስረታ ምዕላድን ለማስረዳትም ተራራ+ማ=ተራራማ የሚል ምሳሌ በማቅረብ "ማ" ቅዕል መስራች ምዕላድ ነው ብለዋል፡፡ ነገር ግን ቅዕል መስራች ምዕላድ መሆን ያለበት "-ኣማ" እንጂ "ማ" አይደለም፡፡

በሁለተኛው ምልከታም እንዲሁ ተገቢነት የሌላቸው ገለፃዎች በመምህሩ ቀርበዋል፡፡ የሀረግ ምንነትን ለማስረዳት "ሀረግ ከአንድ በላይ ተዋቀሪ አካላት ይዞ ይመሰረታል" የሚል ገለፃ ተጠቅመዋል፡፡ ነገር ግን ቀደም ሲል በክለሳ ድርሰት ክፍል እንደተገለፀው አንድ ቃል ብቻውን ሃረግ የመሆን አቅም አለው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ መምህሩ ስለ ሃረግ ከሰጡት ገለፃ ጋር የሚቃረኑ ምሳሌዎችን ለተማሪዎቹ አቅርበዋል፡፡ እነዚህም፡-

እኔ የገዛሁት መኪና ጠፋ፡፡ እና

አየለ አበበ እንደታመመ ሰማ፡፡ የሚሉት ናቸው፡፡

በእነዚህ አረፍተ ነገሮች ውስጥ በመጀመሪያው ግሳዊ ሃረጉ እና በሁለተኛው ስማዊ ሃረጉ ከአንድ ቃል የተመሰረቱ ናቸው፡፡ ይህ ሁኔታም መምህሩ "ሀረግ ከአንድ በላይ ተዋቃሪ አካላት ይዞ ይመሰረታል" ብለው ከሰጡት ገለፃ ጋር ይቃረናል፡፡

መምህሩ በዚሁ ምልከታ ስር ያቀረቡት የመጀመሪያው መመሪያም ተገቢነት የሌለው ነው፡፡ ይኸውም "ከዚህ በታች የቀረቡት የተሰመረባቸው ቃላት የመሰረቱትን የሃረግ አይነት አመልክቱ" ማለት ሲገባው የሚመሰርቱትን ተብሎ ቀርቧል፡፡

ከላይ የቀረቡትን ክፍተቶች በማየትም መምህር አንድ የሰዋሰው ትምህርቱን በትክክል አለማቅረባቸውን መረዳት ይቻላል፡፡

5. **የሰዋስው ትምህርት ሂደቱ አብዛኛውን ተማሪ የማሳተፉ ሁኔታ፡-** በመጀመሪያው ምልከታ ወቅት በክፍል ውስጥ ከነበሩት 43 ተማሪዎች መካከል ሰባት ተማሪዎች በመምህሩ ለተጠየቋቸው ጥያቄዎች በግል መልስ በመስጠት ተሳትፈዋል፡፡ ከዚህ ውጭ ግን በጥንድና በቡድን ተደራጅተው እንዲወያዩ አልተደረገም፡፡ በሁለተኛው ምልከታ ወቅት ደግሞ በክፍል ውስጥ ከነበሩት 45 ተማሪዎች መካከል አራት ተማሪዎች በመምህሩ ለተጠየቋቸው ጥያቄዎች በግል መልስ በመስጠት ተሳትፈዋል፡፡ ሁሉም የክፍሉ ተማሪዎች ደግሞ አንድ ጊዜ ብቻ

በቡድን ተደራጅተው እንዲወያዩ ተደርጓል። ከእነዚህ ሁኔታዎች በመነሳት የሰዋስው ትምህርቱ ሂደት አብዛኛውን ተማሪ ያሳተፈ እንዳልነበር መረዳት ይቻላል። አብዛኛውን ተማሪ አለማሳተፉም የሰዋስው ትምህርቱ በተግባቦታዊ መንገድ አለመቅረቡን የሚሳይ ተጨማሪ ማስረጃ ነው።

**6.የሰዋስው ትምህርት ክፍሉ ድባብ ምን ይመስላል፡-** በሁለቱም ምልከታዎች ወቅት የሰዋስው ትምህርቱን ክፍል የሚረብሹ ሁኔታዎች አልተፈጠሩም። ክፍሉ ስነ-ስርዓት የሰፈነበት ነበር። መምህሩም በአግባቡ ተቆጣጥሮታል።

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ በዝርዝር እንዳየነው መምህር አንድ የሰዋስው ትምህርቱን ተግባቦታዊ ቢሆን አቀራረብ እና ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅተው አላቀረቡም። ትምህርቱን ያቀረቡት ውጤት ተኮር የማስተማሪያ ዘዴን በመከተል በሰዋስዋዊ ይዘቶቹ ላይ በቀጥታ ገለፃና ማብራሪያ በመስጠት ነው። ያቀረቧቸው ገለፃዎችና ማብራሪያዎችም ቢሆን ከላይ በተራ ቁጥር 4 ስር እንደተገለፀው በርካታ ክፍተቶች የሚታዩባቸው ናቸው።

### 4.1.2 መምህር ሁለት

**የመምህሩ ዳራ እና በምልከታው ወቅት የተከተሏቸው የማስተማሪያ ሂደቶች**

መምህር ሁለት በወልድያ መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 11ኛ ክፍል ውስጥ አማርኛን ከሚያስተምሩ መምህራን መካከል ለዚህ ጥናት የተመረጡ ሁለኛው መምህር ናቸው። መምህሩ በቋንቋው የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ሲሆን በዚህ ሙያቸውም የአምስት ዓመታት የማተማር ልምድ አላቸው።

መምህሩ ከሚያስተምሩባቸው ሴክሽኖች መካከል 11ኛH ክፍል ተመርጦ በዚሁ የመማሪያ ክፍል ውስጥ ሁለት ጊዜ በመገኘት በመምህሩ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ላይ መረጃ ተሰብስቧል። በምልከታዎቹ ወቅት ማየት እንደተቻለው መምህሩ የየዕለቶቹን የሰዋስው ይዘቶች በሚከተለው መልኩ አቅርበዋቸዋል።

**ምልከታ ሀ**

በመምህር ሁለት የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ ላይ የመጀመሪያው ምልከታ የተካሔደው በ14/03/2003 ዓ.ም ከሰዓት በኋላ ከ6፡40 ሰዓት ጀምሮ ነው። መምህሩ በሰአቱ ክፍል ውስጥ ተገኝተዋል። የዕለቱን የትምህርት ዕቅድ አዘጋጅተው አምጥተዋል። አጥኚውም እቅዱን ተቀብሏል።

## ትምህርቱ ተጀመረ

መምህሩ የዕለቱ ትምህርት "ምዕላድ" የሚል መሆኑን ገልፀው በጥቁር ሰሌዳው ላይ ከፃፉ በኋላ ተማሪዎቹ በየዴስካቸው በቡድን ሆነው በ "ምዕላድ ምንነት" እና "ዓይነቶች" ላይ እንዲወያዩ አዘዙ፡፡ ተማሪዎቹም በታዘዙት መሰረት ለአራት ደቂቃዎች ያክል ውይይት አደረጉ፡፡ ከዚያም መምህሩ ውይይቱ በቂ መሆኑን ተናግረው ተማሪዎቹ የተወያዩባቸውን ጥያቄዎች መልሶች በግል እጃቸውን እያወጡ እንዲመልሱ እድል ሰጡ፡፡ በዚህ ወቅት በርከት ያሉ ተማሪዎች እጃቸውን ያወጡ ሲሆን ከእነዚህ መካከል አራት ተማሪዎች እድል ስለተሰጣቸው በ "ምዕላድ ምንነት እና አይቶች" ላይ የየግላቸውን መልሶች ሰነዘሩ፡፡ መምህሩም የተማሪዎቹን መልሶች ካዳመጡ በኋላ በእለቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘት ላይ ገለፃ መስጠት ጀመሩ፡፡ በመጀመሪያ በምዕላድ ምንነት ላይ ለአምስት ደቂቃዎች ያህል በምሳሌ የተደገፈ ገለፃ አደረጉ፡፡ በመቀጠልም ስለ ምእላድ ክፍሎች ማለትም ስለ ነጻ እና ጥገኛ ምእላዶች ለአስራሁለት ደቂቃዎች ያክል፣ እንዲሁም ስለ ምድብ ተውላጠ ስሞች ለሰባት ደቂቃዎች ያክል እና ስለጥገኛ ምእላዶች ሞያ ለአምስት ደቂቃዎች ያክል በምሳሌ የተደገፈ ገለጻ አደረጉ፡፡

መምህሩ በገለፃቸው ወቅት የተጠቀሙባቸው እና ተማሪዎቹ በደብተራቸው ላይ የገለበጧቸው ምሳሌዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

**ምዕላድ**

ምዕላድ ምንድን ነው? ፡-

- ትርጉም አዘል የሆነ
- ሰዋሰዋዊ ተግባር ያለው
- ወደ ሌላ አነስተኛ ክፍል የማይከፈል የቋንቋ አሀድ ነው

ምሳሌ፡- ባህላዊነት  ባህል → ትርጉም አዘል  -አዊ -ነት → ሰዋሰዋዊተግባር

**የምዕላድ አይነቶች**

ምዕላዶች ራሳቸውን ችለው ከመቆምና ካለመቆም አንፃር ሲታዩ በሁለት ይከፈላሉ

1. **ነፃ ምዕላድ፡-** - በተለምዶ ስርዎ ቃል ዋና ቃል እየተባለ የሚጠራ
   - ትርጉም አዘል የሆነ
   - ብቻቸውን ሲነገሩ መልዕክት የሚያስተላልፉ
   - ራሳቸውን ችለው የሚቆሙ፣ መጠጊያ የማይፈልጉ

ምሳሌ፡- ወንበር

2. ጥገኛ/ እስር/ምዕላድ፡- - መጠጊያ አካል የሚፈልጉ ናቸው
   - ራሳቸውን ችለው የማይቆሙ
   - ብቻቸውን ሲነገሩ መልዕክት የማያስተላልፉ ናቸው፡፡
   ምሳሌ፡- ወንበሮች= ወንበር - ኦች ⟶ ጥገኛ ምዕላድ
   - በብዛት በስሞችና ግሶች ላይ የሚቀጠሉ ናቸው፡፡

ጥገኛ ምዕላዶች በስሞች ላይ ሲቀጠሉ

1. ቁጥር አመልካች ምሳሌ፡- መምህር - ኣን = መምህራን
2. ፆታ አመልካች ምሳሌ፡- ልጅ - ኢት = ልጂት
3. አይነትን አመልካች ምሳሌ፡- እሾህ - ኣማ = እሾሃማ
4. ወገን አመልካች ምሳሌ፡- ኢትዮጵያ - ኣዊ = ኢትዮጵያዊ
5. ባለንብረትን አመልካች ምሳሌ፡- ደብተር - ህ = ደብተርህ

ጥገኛ ምዕላዶች በግሶች ላይ ሲቀጠሉ

- የባለቤት
- የመደብ
- የቁጥር
- ፆታ

(አመልካች ይሆናሉ)

ምሳሌ፡- ገደል -ኧች -ው

ምድብ ተውላጠ ስሞች

| ምድብ ተውላጠ ስሞች | የባለቤት አመልካች | የተሳቢ አመልካች |
|---|---|---|
| 1ኛ መደብ - እኔ | - ሁ/-ኩ | - ኝ |
| - እኛ | - ን | - ን |
| 2ኛ መደብ - አንተ | - ህ/-ክ | - ህ |
| - አንቺ | - ሽ | - ሽ |
| - እናንተ | - ኣችሁ | - ኣችሁ |
| 3ኛ መደብ - እሱ | - ኧ | - ው/-ት |
| - እሷ | - ኧች | - ኣት |
| - እነሱ | - ኡ | - ኣቸው |

ጥገኛ ምዕላዶች ካላቸው ሙያ አንፃር

ሀ. የርባታ/ዘርዛሪ/ ምዕላድ፡- በቃል ላይ ሲቀጠሉ የቃል ክፍሉን ወደ ሌላ የቃል ክፍል የማይለውጡ ናቸው፡፡

⇒ቁጥርን፣መደብን፣ፆታን፣እምርነትን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

ምሳሌ፡- ወንበሮች= ወንበር + -ኦች

ወንበሬ= ወንበር+ -ኤ

ወንበራችን =ወንበር+ -ኣችን

ለ. <u>የምስረታ/ቃል ለዋጭ/ ምዕላድ፡-</u> በቃል ላይ ሲቀጠሉ የቃል ክፍሉን ወደ ሌላ የቃል ክፍል የሚቀይሩ ምሳሌ፡- 1. ብልህ( ቅፅል) + ነት = <u>ብልህነት</u> ( ስም)

2. ቁምነገር (ስም) + እኛ = <u>ቁምነገረኛ</u> (ቅፅል)

መምህሩ ገለፃቸውን ሲጨርሱ ለተማሪዎቹ በመማሪያ መፅሀፉ ከገፅ 54-56 ያሉትን ጥያቄዎች በቤት ስራ እንዲሰሩ ነግረው የዕለቱ ትምህርት ተጠናቀቀ፡፡ የዕለቱን ሰዋስዋዊ ይዘት ለማስተማር በአጠቃላይ 36 ደቂቃዎች የወሰደ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 29 ደቂቃው የተሸፈነው በመምህሩ ገለፃ ነው፡፡

## ምልከታ ለ

በመምህር ሁለት የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ ላይ ሁለተኛው ምልከታ የተካሄደው በ16/03/2003 ዓ.ም ከሰዓት በኋላ ከ7፡28 ሰዓት ጀምሮ ነው፡፡ መምህሩ በሰዓቱ ክፍል ውስጥ ተገኝተዋል፡፡ የዕለቱን የትምህርት እቅድ አዘጋጅተው አምጥተዋል፡፡ አጥኚውም የትምህርት እቅዱን ተቀብሏል፡፡

## ትምህርቱ ተጀመረ

መምህሩ የባለፈው ክፍለ ጊዜ ትምህርት ስለ "ምዕላድ" እንደነበር አስታውሰው ተማሪዎቹ ከተማሩት ውስጥ የሚያስታውሱትን እንዲመልሱ ጠየቁ፡፡ ሁለት ተማሪዎች እድል ስለተሰጣቸው መልሶቻቸውን ተናገሩ፡፡ መምህሩም በምዕላድ ምንነትና ክፍሎች ላይ ጠቅለል ያለ ማብራሪያ ከሰጡ በኋላ የዕለቱ ትምህርት ርዕስ "ሐረግ" የሚል መሆኑን ገልፀው ይህንኑ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ፃፉ፡፡ በመቀጠልም ተማሪዎቹ በየዴስካቸው በቡድን ተደራጅተው የሃረግ ምንነት፣ የሃረግ ዓይነቶች፣ የሃረግ አይነቶች ተመሳሳይነት እና ልዩነት በሚሉት ጉዳዮች ላይ እንዲወያዩ አዘዙ፡፡ ተማሪዎቹም በታዘዙት መሰረት ለአራት ደቂቃዎች ያክል ተወያዩ፡፡ በመቀጠልም በተወያዩት መሰረት እጃቸውን እያወጡ እንዲመልሱ መምህሩ ስለነገሯቸው በዚሁ መሰረት እድል የተሰጣቸው አምስት ተማሪዎች መልሶቻቸውን ተናገሩ፡፡

መምህሩም የተማሪዎቹን መልሶች ካዳመጡ በኋላ በእለቱ የትምህርት ርእስ ላይ ገለጻቸውን ጀመሩ። በእያንዳንዱ የሃረግ አይነት (ስማዊ፣ ግሳዊ፣ ቅፅላዊ፣ ተውሳከግሳዊ እና መስተዋድዳዊ) ላይ ለ31 ደቂቃዎች ያክል በምሳሌ የተደገፈ ሰፊ ማብራሪያና ገለፃ አደረጉ። በገለፃው ወቅት መምህሩ የተጠቀሙባቸው እና ተማሪዎች በደብተራቸው ላይ የገለበጧቸው ምሳሌዎች የሚከተሉት ናቸው።


## የሐረግ ዓይነቶች

1. ስማዊ ሃረግ

⇒ መሪው ስም የሆነ የሀረግ ዓይነት

⇒ መሪው ሁልጊዜ በስተቀኝ በኩል ሊገኝ የሚችል


ከመስተኣምር እና አጎላማሽ ቅንጅት ሊፈጠር የሚችል




መስተዓምሮች በ3 ይከፈላሉ፡-

1. ጠቋሚ መስተዓምር
2. መጣኝ መስተኣምር
   - ኢ-ውሱን
   - ውሱን
3. አገናዛቢ መስተዓምር

በዕፀ መዋቅር ማሳየት ይቻላል



2 ግሳዊ ሃረግ፡-

⇒ መሪው ግስ የሆነ የሃረግ ዓይነት

⇒ መሪው ሁልጊዜ በስተቀኝ በኩል ሊገኝ የሚችል

⇒ ከመሙያ፣ አጎላማሽ፣ መስተአምር ቅንጅት ሊፈጠር ይችላል።

ግሳዊ ሀረግ → የመሆን፡- - ሆነ፣

- ነው

- ይመስላል ምሳሌ፡- ካሳ ወታደር → ሆነ የመሆን ግስ

- አለ አስቴር ብርጭቆ ሰበረች → የድርጊት ግስ

→ የድርጊት፡- - ሰበረ

- ገደለ

- ሄደ

የድርጊት ግስ በሁለት ሊከፈል ይችላል 1. ተሻጋሪ፡- ስህን በመሙያነት ሊወስድ የሚችል

2 ኢ-ተሻጋሪ፡- ስህን በመሙያነት ሊወስድ የማይችል

ምሳሌ፡- ካሳ <u>ወደ ቤቱ ገባ</u> -ኢ-ተሻጋሪ ግስ

አስቴር <u>ብርጭቆ ሰበረች</u> -ተሻጋሪ ግስ

ጥያቄ፡- ስማዊ ሀረጉን እና ግሳዊ ሃረጉን ለዩ።

ካሳ ሁለት ጊዜ በባንክ ለአስቴር ገንዘብ ልኮላታል።

ሁለት ጊዜ ↓ መስተአምር; በባንክ ↓ አጎላማሽ; ለአስቴር ↓ መሙያ; ገንዘብ ↓ መሙያ; ልኮላታል ↓ መሪ።

ስህ = ካሳ

ግህ = ሁለት ጊዜ በባንክ ለአስቴር ገንዘብ ልኮላታል።

- አረፍተነገሩ በዕፀ መዋቅር ሊታይ ይችላል።

3 ቅፅላዊ ሀረግ

⇒ መሪው ቅፅል የሆነ የሀረግ ዓይነት

⇒ ሁልጊዜ ቀኝ መሪ የሆነ

⇒ እንደ ሌሎች ሀረጎች ሁሉ ከመሙያ፣ ከአጎላማሽ እና ከመስተአምር ጋር ሊቀናጅ የሚችል

አንድ ቃል ቅፅል መሆኑን ለማወቅ |በጣም + ቅፅል + ስም | በሚለው ቀመር ውስጥ ማየት አለብን።

ምሳሌ፡- በጣም እንደ እህቱ ሰው ፈሪ ነው።

↓ ↓ ↓ ↓

መስተአምር አጎላማሽ መሙያ መሪ

4 መስተዋድዳዊ ሀረግ

⇒ መሪው መስተዋድድ የሆነ የሀረግ ዓይነት ነው

⇒ መሪው በቀኝም ሆነ በግራ በኩል ሊገኝ ይችላል

⇒ ሁልጊዜ የመሪና የመሙያ ቅንጅት ነው

ምሳሌ፡- እንደ ጅብ

ምሳሌ፡- እንደ ጅብ

↓ ↓

መሪ መሙያ

5 ተውሳከ ግሳዊ ሀረግ

⇒ መሪው ተውሳከ ግስ የሆነ የሀረግ ዓይነት

⇒ ቀኝ መሪ የሆነ

⇒ መሙያ የማይፈልግ

⇒ በአጎላማሽ እና በመስተዓምር ቅንጅት የሚመሰረት

ምሌ፡- በጣም እንደ እህቱ ክፉኛ ታመመ

↓ ↓ ↓

መስተኣምር አጎላማሽ መሪ

⇒ በጣም ውስን ቃላት አሉት

መምህሩ ገለፃና ማብራሪያቸውን ሲጨርሱ ተማሪዎቹ በመማሪያ መፅሀፋቸው ከገፅ 55-56 ያሉትን ጥያቄዎች በቤት ስራ እንዲሰሩ ነግረው የዕለቱ ትምህርት ተጠናቀቀ። የዕለቱን የሰዋስው ትምህርት "ለማቅረብ በአጠቃላይ 39 ደቂቃዎችን የወሰደ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 31 ደቂቃው የተሸፈነው በመምህሩ ገለፃ ነው።

## ትንተና

**1.መምህሩ የሰዋስው ትምህርቱን ዓላማ በግልፅ የማስቀመጡ ሁኔታ፡-** መምህር ሁለት ምልከታ በተካሄደባቸው ክፍለ ጊዜያት በመጀመሪያው አንድ እና በሁለተኛው ሁለት የዓላማ ገለፃዎችን አስቀምጠዋል፡፡ እነዚህም በቅደም ተከተል "ተማሪዎቹ ከትምህርቱ በኋላ የምዕላድ ምንነት እና ዓይነቶችን ይተነትናሉ" ፣ "የሀረግ ዓይነቶችን ይተነትናሉ" እና "የሀረግ ዓነቶችን በልዩ ልዩ ምሳሌዎች ያብራራሉ" የሚሉ ናቸው፡፡ በእነዚህ የዓላማ ገለጻዎች ውስጥ "ይተነትናሉ" እና "ያብራራሉ" የሚሉ ቃላት የሚገኙ ሲሆን እነዚህ ቃላትም ተማሪዎቹ ከሰዋስው ትምህርቱ በኋላ የሚያከናውኗቸውን ተግባራትና በዚያውም የሚያዳብሩትን ሰዋስዋዊ ችሎታ በግልጽ ያሳያሉ፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎቹ ለዕለቱ የቀረበውን የሰዋስው ትምህርት መረዳት አለመረዳታቸውን ለማወቅ የሚያስችሉ ተግባራትን የሚጠቁሙ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ቃላት በተጨማሪ በዓላማ ገለፃዎቹ ውስጥ ያሉት ቃላትና ሀረጋትም ተገቢነት ያላቸው ሲሆኑ የሰዋሰው ትምህርቱን ዓለማዎች ግልፅ እና ውሱን /Specific/ በሆነ መልኩ ይገልፃሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ አላማዎች የሚገልፁት የሰዋስው ትምህርት እራሱን ችሎ ሲቀርብ ተማሪዎቹ የሚያዳብሩትን ሰዋስዋዊ ችሎታ ብቻ ነው፡፡ የሰዋስው ትምህርት ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅቶ ሲቀርብ ተማሪዎቹ የሚያዳብሩትን ተግባቦታዊ ችሎታ አይጠቁሙም፡፡ ስለዚህም መምህር አንድ የሰዋስው ትምህርቱን ኣላማ በከፊል ተገቢነት ባለው መልኩ አስቀምጠዋል፡፡

**2.መምህሩ ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ ለማስተማር የሚያስችሉ ደረጃዎችን ጠብቆ የማስተማሩ ሁኔታ፡-** ከዚህ የመገምገሚያ ነጥብ አኳያ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ቀደም ሲል እንዳደረግነው የመምህሩን የትምህርት አቀራረብ ከአምስቱ ደረጃዎች ጋር አያይዞ አንድ በአንድ ማየት ያስፈልጋል፡፡

ሀ. ማቅረቢያ፡ መምህር ሁለት በሁለቱም ክፍለ ጊዜያት ትምህርቱን የጀመሩት ተማሪዎቹ ባለፉት ክፍለ ጊዜያት የተማሯቸውን ጉዳዮች እንዲያስታውሱ በመጠየቅ ሲሆን የየእለቶቹን ይዘቶች ለተማሪዎቹ ያስተዋወቁትም በቀጥታ ገለፃ በማድረግ ነው፡፡ ይህ ግን ተገቢነት ያለው አጀማመር አይደለም፡፡ ይህን ለማለት ያስቻለን ምክንያትም መጀመሪያውኑ የየዕለቶቹ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በአውድ ውስጥ ሆነው አለመቅረባቸው ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለፀው በዚህ ደረጃ የሚከናወን ማንኛውም ተግባር (ጥያቄ መጠየቅ ጭምር) መከናወን ያለበት አውዱን መሰረት አድርጎ መሆን አለበት፡፡ ለዕለቱ የቀረበው ሰዋስዋዊ ይዘት ለተማሪዎቹ የሚተዋወቀውም ራሱን ችሎ በቀጥታ ሳይሆን አውዱን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህ ተግባራት ግን በመምህሩ አልተከናወኑም፡፡ ስለዚህም መምህር ሁለት የማቅረቢያ ደረጃን በአግባቡ አልተገበሩትም ማለት ይቻላል፡፡

ለ. **ማውጣጣት፡-** በሁለቱም ክፍለ ጊዜያት ማየት እንደተቻለው መምህሩ ለየዕለቶቹ ባቀረቧቸው ሰዋሰዋዊ ይዘቶች ላይ ተማሪዎቹን ጥያቄ ጠይቀዋል፡፡ ምንም እንኳን ጥያቄ መጠየቅ በዚህ ደረጃ ሊከናወን የሚችል ተግባር ቢሆንም ከላይ እንደተገለፀው የየእለቶቹ ሰዋስዋዊ ይዘቶች በአውድ ውስጥ ባለመቅረባቸው የመምህሩ ጥያቄዎች ተግባቦትን ታሳቢ ያደረጉ አለመሆናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡ በተጨማሪም መምህሩ በእነዚህ ጥያቄዎች የተወሰኑ ተማሪዎች ከማሳተፍ ባለፈ እያንዳንዱ ተማሪ በእለቱ በቀረበው የሰዋስው ይዘት ላይ ያለውን የግንዛቤ ደረጃ ለማወቅ አልተጠቀሙበትም፡፡ ነገር ግን በዚህ ደረጃ ጥያቄ የመጠየቅ ዋነኛ ዓላማ ቀደም ሲል እንደተገለፀው ለትምህርት በቀረበው ሰዋስዋዊ ይዘት ላይ ተማሪዎቹ ያላቸውን የግናዛቤ ደረጃ ለማወቅ እና ከተማሪዎቹ የግንዛቤ ደረጃ በመነሳት ገለፃና ማብራሪያ ለመስጠት ነው፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ግን በመምህሩ አልተተገበሩም፡፡ ስለዚህም መምህር ሁለት የማውጣጣት ደረጃን አልተገበሩትም ማለት ይቻላል፡፡

ሐ. **ገለፃ ፡-** መምህር ሁለት የማውጣጣት ደረጃን ተጠቅመው ተማሪዎቹ ለየዕለቶቹ በቀረቡት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ላይ ያላቸውን የግንዛቤ ደረጃ ለማወቅ ባይሞክሩም በሁለቱም ክፍለ ጊዜያት በሰዋስዋዊ ይዘቶቹ ላይ በምሳሌ የተደገፉ ሰፋፊ ገለፃዎችን አካሄደዋል፡፡ ይህ ግን ደረጃውን በአግባቡ ተግብረውታል አያስብልም፡፡ ለዚህም ምክንያቶቹ በመጀመሪያ መምህሩ ገለፃውን ያካሄዱት የተማሪዎቹን የግንዛቤ ደረጃ በማወቅ እና በዚያ ላይም በመመስረት አለመሆኑ ነው፡፡ ሁለተኛም ገለፃና ማብራሪያ ያደረጉት በአውድ ላይ በመመስረት ሳይሆን ውጤት ተኮር ዘዴን በመከተል ሰዋስዋዊ ይዘቶቹን በቀጥታ በማቅረብ ነው፡፡ ከእነዚህ ሁኔታዎች በመነሳት መምህር ሁለት የገለፃ ደረጃን በከፊል ተግብረውታል ማለት ይቻላል፡፡

መ. **አፍፅም ማፍለቅ፡-** በሁለቱም ክፍለ ጊዜያት ማየት እንደተቻለው ተማሪዎቹ የመምህሩን ገለፃ ከተከታተሉ በኋላ በተማሯቸው ሰዋስዋዊ መዋቅሮች ላይ እንዲለማመዱ አልተደረገም፡፡ መምህሩ በሁለቱም ክፍለ ጊዜያት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉትን ጥያቄዎች ተማሪዎች በቤት ስራ እንዲሰሩ ቢያዙም ይህ ግን የደረጃውን ተግባራዊነት አያሳይም፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎቹ የአፍፅም ማፍለቅ ልምምድ ማድረግ ያለባቸው የመምህሩን ገለፃ እንደተከታተሉ ወዲያው መሆን አለበትና ነው፡፡ ስለዚህም ይህ ደረጃ በመምህሩ አልተተገበረም፡፡

ሠ. **ፍልቀራስ፡-** በሁለቱም ክፍለጊዜያት ማየት እንደተቻለው ተማሪዎቹ ምዕላድንም ሆነ ሀረግን ተጠቅመው ከራሳቸው በማፍለቅ ሀሳባቸውን እንዲገልፁ አልተደረጉም፡፡ ስለዚህም ደረጃው በመምህሩ አልተተገበረም፡፡

3. **የሰዋስው ትምህርቱ ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅቶ የመቅረቡ ሁኔታ፡-** የሰዋስው ትምህርት ሂደትን ተግባቦታዊ ለማድረግ ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅቶ ማቅረብ የግድ ያስፈልጋል፡፡ የመምህር ሁለትን የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ከዚህ አኳያ ስንገመግም ችግር

ይታይበታል፡፡ በሁለቱም ምልከታዎች ወቅት ማየት እንደተቻለው የሰዋስዋዊ ይዘቶቹን ያስተማሩት ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር እያቀናጁ ሳይሆን የውጤት ተኮር ዘዴን በመከተል ቀጥተኛ የሆነ ገለፃና ማብራሪያ በመስጠት ነው፡፡

4. **መምህሩ የሰዋስው ይዘቶችን በትክክል የማስተማሩ ሁኔታ፡-** መምህር ሁለት በሁለቱም ክፍለ ጊዜያት ባቀረቧቸው የሰዋሰው ትምህርቶች ተገቢነት የሌላቸው ገለፃዎችን አድርገዋል፡፡ እነዚህንም ከዚህ ቀጥሎ አንድ በአንድ እናያቸዋለን፡፡

በመጀመሪያው ክፍለ ጊዜ ስለ "ነፃ ምዕላድ ምንነት" ሲያስረዱ "በተለምዶ ስርወ ቃል፣ ዋና ቃል እየተባለ የሚጠራ" የሚል ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡ ነገር ግን ነፃ ምዕላድ እና ስርወ ቃል ትርጉም አዘል በመሆናቸው የሚያመሳስላቸው ነገር ቢኖርም ፍፁም አንድ አይነት የሆኑ ፅንሰ ሃሳቦች አይደሉም፡፡ ስርወ ቃል (ስር) በግስ ውስጥ መሰረታዊውን ትርጉም ይዘው የሚገኙ ተናባቢዎች ቅንጅት ነው፡፡ በተናባቢዎቹ ውስጥ የተለያዩ አናባቢዎችን በመጨመር ወይም ስሮቹን ከአናባቢዎች ጋር በማቀናጀት ስሞችን፣ ቅፅሎችን እና የተለያየ ቅርፅ ያላቸውን ግሶች መመስረት ይቻላል፡፡ ነፃ ምዕላድ ግን እነዚህን ሁኔታዎች አያሟላም፡፡ በተጨማሪም ነፃ ምዕላድ ራሱን ችሎ መቆም የሚችል ሲሆን ስርወ ቃል (ስር) ግን በውስጡ አናባቢዎችን ካላስገባ በስተቀር ራሱን ችሎ መቆም አይችልም፡፡

ስለ "ጥገኛ/እስር/ ምዕላድ" ሲያስረዱም "ብቻቸውን ሲነገሩ መልዕክት የማያስተላልፉ ናቸው" የሚል ገለፃ አድርገዋል፡፡ ነገር ግን ጥገኛ ምዕላዶች ራሳቸውን ችለው መነገር ስለማይችሉ ገለፃው ተገቢነት የለውም፡፡ በተጨማሪም "ጥገኛ ምላዶች በግሶች ላይ ሲቀጠሉ ፆታን ሊያመለክቱ ይችላሉ" የሚል ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡ ነገር ግን በግስ ላይ የሚቀጠሉ ምዕላዶች ሰዋሰዋዊ ተግባር ባለቤትን፣ ተሳቢን፣ አኀላማሽን መጠቆም እንጂ ፆታን ማመልከት አይደለም፡፡ ምድብ ተውላጠ ስሞችን በዘረዘሩበት ሰንጠረዥ ውስጥም የባለቤት አመልካች ምዕላድ ብለው -ሁ/-ኩ፣ -ን፣ -ህ/-እ፣ -ሽ ወዘተ የሚሉ ምዕላዶችን ዘርዝረዋል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ምዕላዶች ባለቤትን የሚያመለክቱት በማንኛውም ጊዜ ሳይሆን በየዋህ ኃላፊ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ለምሳሌ አረፍተ ነገሩ በትንቢት ጊዜ ቢነገር ምዕላዶቹ ባቤትን አያመለክቱም፡፡

በሁለተኛው ክፍለ ጊዜ ስለሃረግ ያቀረቡት ትምህርት ደግሞ ለክፍል ደረጃው ላሉ ተማሪዎች የሚያስቸግር ነው፡፡ መምህሩ ውስብስብ ሃረጎችን በማቅረብ ማብራሪያ እየሰጡ እና በዕፀ መዋቅር እየተነተኑ ለማስተማር ሞክረዋል፡፡ ነገር ግን ትምህርቱ በዚህ አይነት የጥልቀት መጠን እንዲቀርብ በመርሃ ትምህርቱ፣ በተማሪው መፅሃፍም ሆነ በመምህሩ መመሪያ አልተጠቆመም፡፡ ከዚህም ባሻገር የቀረበው ትምህርት ችግሮች ይስተዋሉበታል፡፡ ስለ ስማዊ ሃረግ አፈጣጠር ሲያስረዱ "ከመስተአምርና አኀላማሽ ቅንጅት ሊፈጠር የሚችል" የሚል ገለፃ

ስጥተዋል፡፡ ይህ ገለፃ ስማዊ ሃረግ ያለ መሪ ሊመሰረት ይችላል የሚል መልዕክትን ስለሚያስተላልፍ ተገቢነት ይጎድለዋል፡፡ በስማዊ ሃረግ ውስጥ ሊገቡ የሚችሉ መስተአምሮችን ሲያስቀምጡም ጠቋሚ መስተአምር፣ መጣኝ መስተአምርና አገናዛቢ መስተአምር በሚል ቅደም ተከተል ዘርዝረዋቸዋል፡፡ ነገር ግን ትክክለኛው ቅደም ተከተል ጠቋሚ መስተአምር፣ አገናዛቢ መስተአምር እና መጣኝ መስተአምር ነው፡፡ በሌላም በኩል ለስማዊ ሃረግ ያቀረቡትን ምሳሌ በዕፀ መዋቅር አሳይተው ለሌሎቹ ሃረጎች ያቀረቧቸውን ምሳዎችን ግን አላሳዩም፡፡

በአጠቃላይ መምህር ሁለት በሁለቱ ክፍለ ጊዜያት ስለ ምዕላድና ሃረግ ያቀረቧቸው የሰዋስው ትምህርች ተገቢነት የጎደላቸው ሆነው ተገኝተዋል፡፡

5. **የሰዋስው ትምህርት ሂደቱ አብዛኛውን ተማሪ የማሳተፉ ሁኔታ፡-** በመጀመሪያው ምልከታ ወቅት በክፍሉ ውስጥ ከነበሩት 42 ተማሪዎች መካከል አራት ተማሪዎች በመምህሩ ለተጠየቋቸው ጥያቄዎች መልስ በመስጠት ሲሳተፉ፣ ሁሉም የክፍሉ ተማሪዎች ለአንድ ጊዜ ብቻ በቡድን እንዲወያዩ ተደርጓል፡፡ በሁለተኛው ምልከታ ወቅት ደግሞ በክፍሉ ውስጥ ከነበሩት 42 ተማሪዎች መካከል ስምንት ተማሪዎች በመምህሩ ለተጠየቋቸው ጥያቄዎች መልስ በመስጠት ሲሳተፉ ሁሉም የክፍሉ ተማሪዎች ለአንድ ጊዜ ብቻ በቡድን እንዲወያዩ ተደርገዋል፡፡ ከእነዚህ ሁኔታዎች በመነሳት የሰዋስው ትምህርት ሂደቱ አብዛኛውን ተማሪ ያሳተፈ እንዳልነበር መረዳት ይቻላል፡፡

6. **የሰዋስው ትምህርት ክፍሉ ድባብ ምን ይመስላል?፡-** በሁለቱም ክፍለጊዜያት ማየት እንደተቻለው የሰዋስው ትምህርቱን የሚረብሹ ሁኔታዎች አልተፈጠሩም፡፡ ክፍሉ ስነ-ስርዓት የሰፈነበት ነበር፡፡ መምህሩም በአግባቡ ተቆጣጥረውታል፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ በዝርዝር እንዳየነው መምህር ሁለት የሰዋስው ትምህርቱን ተግባቦትን ለመፍጠር የሚያስችሉ ደረጃዎችን ተጠቅመው እና ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅተው አላቀረቡም፡፡ ትምህርቱን ያቀረቡት ውጤት ተኮር የማስተማሪያ ዘዴን በመከተል በሰዋስዋዊ ይዘቶቹ ላይ በቀጥታ ገለፃና ማብራሪያ በመስጠት ነው፡፡ በሰዋስዋዊ ይዘቶቹ ላይ ያደረጓቸው ገለፃዎችና ማብራሪያዎችም ትክክለኛ ያለመሆን ችግር ተስተውሎባቸዋል፡፡

### 4.1.3 መምህር ሶስት

**የመምህሩ ዳራ እና በምልከታው ወቅት የተከተሏቸው የማስተማር ሂደቶች፡-**

መምህር ሶስት በቀቦ አጠቃላይና መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 11ኛ ክፍል ውስጥ አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ላይ ከሚገኙ ሶስት መምህራን መካከል አንዱ ናቸው፡፡ መምህሩ በአማርኛ ቋንቋ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ሲሆን በዚሁ ሞያቸው ለአምስት ዓመታት ያክል

አስተምረዋል፡፡ መምህሩ ከሚያስተምሩባቸው ክፍሎች መካከል 11ኛ ዘ ተመርጦ በዚሁ የመማሪያ ክፍል ውስጥ ሁለት ጊዜ ምልከታ ተካሂዷል፡፡ በምልከታዎቹ ወቅት ማየት እንደተቻለው መምህሩ የየዕለቶቹን የሰዋስው ትምህርቶች በሚከተለው መልኩ አቅርበዋል፡፡

ምልከታ ሀ

በመምህር ሦስት የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ላይ የመጀመሪያው ምልከታ የተካሄደው በ20/03/2003 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡44 ሰዓት ጀምሮ ነው፡፡ መምህሩ በሰዓቱ ክፍል ውስጥ ተገኝተዋል፡፡ የዕለቱን የትምህርት ዕድ አዘጋጅተው አምጥተዋል፡፡ አጥኚውም የትምህርት እቅዱን ተቀብሏል፡፡

ትምህርቱ ተጀመረ

መምህሩ ለተማሪዎቹ ሰላምታ ከሰጡ በኋላ የዕለቱን የትምህርት ርዕስ "ምዕላድ" በማት በጥቁር ሰሌዳው ላይ ጽፈው "ምዕላድ ማለት ምን ማለት ነው?" በማለት ለተማሪዎቹ ጥያቄ አቀረቡ፡፡ አንድ ተማሪ እጁን አውጥቶ እድል ስለተሰጠው ስለ ምዕላድ ምንነት የራሱን መልስ ሰጠ፡፡ ከዚያም መምህሩ ስለ ምዕላድ ምንነት ገለፃ አደረጉ፡፡ ገለፃቸውን ሲጨርሱም ተማሪዎቹ ስለ ምዕላድ ክፍሎች የሚያውቁትን እንዲናገሩ ጠየቁ፡፡ ሦስት ተማሪዎች መልስ ሰጡ፡፡ መምህሩም በምዕላድ ክፍሎች ላይ ማብራሪያ ሰጡ፡፡ በትምህርቱ ሂደት መምህሩ በጥቁር ሰሌዳው ላይ እየፃፉ የተጠቀሙባቸው እና ተማሪዎቹ በደብተራቸው የገለበጧቸው ምሳሌዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

<u>ምዕላድ</u>

ትርጉም አዘል የሆነና ወደ ሌላ ሊከፈል የማይችል የቋንቋ ንኡስ አሀድ ነው፡፡ በሌላ አባባል አነስተኛ ወደ ሆኑ ትርጉም አዘል ክፍሎች ሊከፋፈል የማይችል የቋንቋ ቅንጣት ነው፡፡

ምሳሌ፡- ቤት

ምዕላድ በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል፡፡

- ነፃ ምዕላድ፡- ራሳቸውን ችለው በመዝገበ ቃላት ውስጥ ሊመዘገቡ የሚችሉና ራሳቸውን ችለው ትርጉም የሚሰጡ ናቸው፡፡
- እስር/ጥገኛ/ ምዕላድ፡- ራሳቸውን ችለው ትርጉም የማይሰጡ ማለትም ወደ ነፃ ምዕላድ ካልተጠጉ በስተቀር ትርጉም የማይሰጡ ናቸው፡፡ ቅጥያዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ምሳሌ፡- ቤቶች = ቤት-ኦች

ምዕላዶችን ከአካባቢው አንፃር በሶስት እንከፍላቸዋለን፡፡

ሀ. መነሻ (ቅድመ ግንድ)

ለ. ዋና ቃል

ሐ. መድረሻ (ድህረ ግንድ)

ምሳሌ፡- አስገደለው አስ-ገደለ-ው

ምዕላድን የእርባታና የምስረታ ምዕላድ በማለት መመደብ ይቻላል።

1) የእርባታ/ዘርዛሪ/ ምዕላድ፡- የሚባሉት የቃል ክፍሎችን አይቀይሩም። የተለያየ ፆታን፣ መደብን፣ ቁጥርን፣ ባለቤትን፣ ተሣቢን የሚያመለክቱ ናቸው።

- ቁጥር፡- መጠንን (ስንትነትን) የሚገልጽ ነው። የነገሮችን ብዙነት በሁለት መንገድ መግለጽ

  ይቻላል።

  1. -ዎችና -ኦች በመጨመር፡- ምሳሌ ተማሪዎች፣ ወንበሮች
  2. ስሙን በመደጋገም፡- ቅጠል -አ- ቅጠል = ቅጠላቅጠል

- ፆታ፡- ተፈጥሮአዊ ፆታ በሁለት ይከፈላል። ተባእታይ እና አንስታይ ፆታ
- መደብ፡- በአማርኛ ቋንቋ 3 መደቦች አሉ

| | | |
|---|---|---|
| 1ኛ | መደብ | ነጠላ ቁጥር/እኔ/፣ ብዙ ቁጥር/እኛ/ |
| 2ኛ | መደብ | ነጠላ ቁጥር/አንቺ/አንተ/፣ ብዙ ቁጥር/እናንተ/ |
| 3ኛ | መደብ | ነጠላ ቁጥር/እሱ/እሷ/፣ ብዙ ቁጥር/እነሱ/ |

2) የምስረታ ምዕላድ፡- የሚባሉት ደግሞ የቃል ክፍል የሚለውጡ ምዕላዶች ናቸው። በአማርኛ የቃላት ምስረታ ውስጥ ቅጽል መስራች ከሆኑት ምዕላዶች መካከል -ኛ፣ -አዊ፣ -ኣማ ይገኛሉ።

ምሳሌ፡- ድንጋይ-ድንጋያማ

- ኢትዮጵያ-ኢትዮጵያዊ

መምህሩ ገለፃና ማብራሪያውን ሲጨርሱ ተማሪዎቹ ያልገባቸው ነገር ካለ እንዲጠይቁ እድል ሰጡ። ሁለት ተማሪዎች ያልገባቸውን ጠየቁ፤ መምህሩም መልስ ሰጡ። ከዚያም በተማሪው መጽሀፍ ገጽ 56 ላይ ያሉትን ጥያቄዎች ተማሪዎቹ በቤት ስራ እንዲሰሩ አዘው የዕለቱ ትምህርት ተጠናቀቀ። የዕለቱን ትምህርት ለማቅረብ በአጠቃላይ 33 ደቂቃዎችን የወሰደ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 26 ደቂቃው በመምህሩ ገለፃ የተሸፈነ ነው።

## ምልከታ ለ

ሁለተኛው ምልከታ የተካሄደው በ23/03/2003 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡30 ሰዓት ጀምሮ ነው። መምህሩ በሰዓቱ ክፍል ውስጥ ተገኝተዋል። የዕለቱን የትምህርት ዕቅድ አዘጋጅተው አምጥተዋል። አጥኚውም የትምህርት ዕቅዱን ተቀብሏል።

## ትምህርቱ ተጀመረ

መምህሩ ለተማሪዎቹ ሰላምታ ከሰጡ በኋላ ባለፈው ክፍለ ጊዜ ስለ ምዕላድ እንዳስተማሩ በማስታወስ ስለ ምዕላድ ምንነትና ክፍሎች ጥያቄ አቀረቡ። ሁለት ተማሪዎች መልስ ሰጡ። መምህሩም የዕለቱ የትምህርት ርዕስ "ሀረግ" የሚል መሆኑን ገልፀው ተማሪዎቹ ስለ ሀረግ ምንነት የሚያውቁትን እንዲመልሱ እድል ሰጡ። ሦስት ተማሪዎች እጃቸውን እያወጡ መልስ ሰጡ። ከዚያም መምህሩ ስለ ሀረግ ምንነት ገለፃ አቀረቡ። በመቀጠልም ስለ ሀረግ ዓይነቶች ማብራሪያ ሰጡ። በእያንዳንዱ የሀረግ ዓይነት ላይም ገለፃ አደረጉ። በገለፃው ወቅት መምህሩ በጥቁር ሰሌዳው ላይ እየፃፉ የተጠቀሙባቸው እና ተማሪዎቹ በደብተራቸው ላይ የገለበጧቸው ምሳሌዎች የሚከተሉት ናቸው።

ሀረግ

አንድ ቃል ከሌላ ቃል ጋር ሲቀናጅ የሚፈጠረው ሠፊ መዋቅር ሀረግ ይባላል። በመሆኑም የሀረግ መሠረቶች ቃላት ናቸው። ሁሉም የሀረግ ክፍሎች መሪ አላቸው። አጃቢዎች አሏው። በአንድ ሀረግ ውስጥ የሚኖረው አንድ መሪ ብቻ ሲሆን ከአንድ በላይ አጃቢዎች ሊኖራቸው ይችላል።

የሀረግ ክፍሎች

በአማርኛ ቋንቋ አምስት የሀረግ ክፍሎች አሉ።

ስማዊ ሀረግ፡- መሪው ስም የሆነ የሀረግ ዓይነት ነው። በአገባብ በአረፍተ ነገር መጀመሪያ ላይ ይመጣል።

ምሳሌ፡- - ታላቅ ወንድሜ

- ትንንሽ ልጆች

ግሣዊ ሀረግ፡- መሪው ግስ የሆነ የሀረግ ዓይነት ነው። በአገባብ በአረፍተ ነገር መጨረሻ ላይ ይመጣል።

ምሳሌ፡- ታላቅ ወንድሜ በሚቀጥለው ሳምንት ይመጣል።

ግሶችን የሁኔታና የድርጊት ግሶች በማለት መመደብ ይቻላል። የሁኔታ ግሶች የምንላቸው ሁኔታን የሚያመለክቱ ሲሆኑ ዋለ፣ አደረ፣ ቆየ የምንላቸው ናቸው። የድርጊት ግሶች የምንላቸው ሠበረ፣ ገደለ።

ቅጽላዊ ሀረግ፡- መሪው ቅጽል የሆነ የሀረግ ዓይነት ነው። ቅጽሎች ከስም በፊትና ከስም በኋላ ይመጣሉ። በአማርኛ ቋንቋ ቅጽሎች በጣም ጥቂት ናቸው። እነሱም የዋህ፣ ደግ፣ ሞኝ፣ ጅል ወዘተ ናቸው።

ተውሳከ ግሳዊ ሀረግ፡- ተውሳከ ግስ ማለት የግስ ተጨማሪ ማለት ነው። ተውሳከ ግስ የምንለው ክፉኛ፣ ጅልኛ፣ ግምኛ፣ ገና፣ ቶሎ ወዘተ

መስተዋድድ፡- ከስሙ መረዳት እንደሚቻለው መስተዋድድ ማለት የሚያዋድድ፣ የሚጣምር፣ የሚያያይዝ ማለት ነው። በአማርኛ ቋንቋ መስተዋድዳዊ ቃላት የምንላቸው ከ፣ በ፣ ለ፣ ወደ፣ እንደ፣ እስከ፣ ስለ ናቸው። የእነዚህ መስተዋድድ አገልግሎት እንደሚከተለው ነው።

ከ የመነሻ መስተዋድድ ነው። ምሳሌ፡- ከደሴ መጣ።

ለ የዓላማ(የግብ) መስተዋድድ ነው። ምሳሌ፡- ለትምህርት ቆቦ ሄደዋል።

በ የመሳሪያ መስተዋድድ ነው። ምሳሌ፡- ትላንት ማታ በቲቪ መስኮት አየሁሽ።

ወደ የአቅጣጫ መስተዋድድ ነው። ምሳሌ፡- የኢትዮጵያ ወንዞች ወደ ሰሜን ይፈሳሉ።

እንደ የማወዳደሪ መስተዋድድ ነው። ምሳሌ፡- ንፋሱ እንደ ዋሽንት ያፏጫል።

እስከ የወሰን መስተዋድድ ነው። ምሳሌ፡- ከቆቦ እስከ አዲስ አበባ 10 ሰዓት ያስጉዛል።

ስለ የርዕስ መስተዋድድ ነው። ምሳሌ፡- ብዙ ዘፋኞች ስለ ወሎ ዘፍነዋል።

መምህሩ ገለፃቸውን እንደጨረሱ በተማሪው መጽሀፍ ከገጽ 56-57 ያሉትን ጥያቄዎች ለተማሪዎች በቤት ስራ እንዲሰሩ ነግረው የዕለቱ ትምህርት ተጠናቀቀ። የዕለቱን ትምህርት ለማቅረብ በአጠቃላይ 29 ደቂቃዎች የወሰደ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 25 ደቂቃው የተሸፈነው በመምህሩ ገለፃ ነው።

## ትንተና

*1. መምህሩ በትምህርት እቅዱ ውስጥ የሰዋስው ትምህርቱን ዓላማ በተገቢ ሁኔታ መግለፁ፡-*

መምህር ሦስት ምልከታ በተካሄደባቸው ሁለት ክፍለ ጊዜያት ባዘጋጇቸው ዕለታዊ የትምህርት እቅዶች ውስጥ የተገለጹት ዓላማዎች "ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ስለ ምዕላድ ምንነትና የምዕላድ ክፍሎችን ለይተው ያውቃሉ" እና "ስለሀረግ ምንነትና የሀረግ ክፍሎች ለይተው ያውቃሉ" የሚሉ ናቸው። በሁለቱም የዓላማ ገለፃዎች ውስጥ "ያውቃሉ" የሚል አጠቃላይ የሆነ ቃል በመቀመጡ የሰዋስው ትምህርቶቹ ዓላማዎች ግልጽና ዝርዝር በሆነ መልኩ አለመገለፃቸውን መረዳት ይቻላል። በተጨማሪም አላማዎቹ ሰዋስው ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅቶ ሲቀርብ ተማሪዎቹ የሚያዳብሩትን ተግባቦታዊ ችሎታ አይጠቁሙም። ስለዚህም መምህር ሶስት የሰዋስው ትምህርቱን አላማ በተገቢ ሁኔታ አልገለፁም ማለት ይቻላል።

*2. ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ ለማስተማር የሚያስችሉ ደረጃዎችን ጠብቆ የማስተማሩ ሁኔታ፡-* የመምህር ሦስትን የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ከዚህ የመገምገሚያ ነጥብ አኳያ ለመመዘን መምህሩ በትምህርቱ ሂደት አምስቱን ደረጃዎች ምን ያክል እንደተገበሯቸው አንድ በአንድ ማየት ያስፈልጋል።

*ማቅረቢያ፦* በሁለቱም ምልከታዎች ወቅት እንደታየው መምህር ሦስት ትምህርቱን የጀመሩት የየዕለቶቹን የሰዋስው ይዘቶች በቀጥታ ለተማሪዎቹ በማስተዋወቅ ነው፡፡ ቀደም ሲል በክለሳድርሳኑ ክፍል እንደተገለጸው በዚህ ደረጃ የሰዋስው ትምህርቱ ይዘት መቅረብ ያለበት በአውድ ሲሆን ሰዋስዋዊ ቅርጹ የሚሸከመው ፍች እና አጠቃቀሙ ለተማሪዎቹ የሚገለጸውም በአውዱ አማካኝነት ነው፡፡ ነገር ግን መምህር ሦስት በዚህ መንገድ ትምህርቱን አልጀመሩም፡፡

*ማውጣጣት፦* በዚህ ደረጃ መምህሩ ተማሪዎቹን ጥያቄ ጠይቀዋል፡፡ ጥያቄ መጠየቅ ለማውጣጣት የሚያገለግል አንደኛው ዘዴ ቢሆንም መጀመሪያውኑ የየዕለቶቹ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች (ምዕላድና ሀረግ) በአውድ አለመቅረባቸው እና ተማሪዎቹም ሰዋስዋዊ ይዘቶቹን ተጠቅመው እንዲናገሩ ባለመደረጋቸው ደረጃው በአግባቡ አለመተግበሩን መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ደረጃ ተማሪዎቹ ለትምህርት በቀረበው የሰዋስው ይዘት ላይ ያላቸውን የግንዛቤ ደረጃ በማሳየት መምህሩ በቀጣይነት ምን ተግባር ማከናወን እንዳለበት ማለትም ወደ የትኛው ደረጃ መሸጋገር እንዳለበት በማመላከት ረገድ ከፍ ያለ ጠቀሜታ ያለው ነው፡፡ ስለዚህም መተግበር ነበረበት፡፡

*ገለፃ፦* ይህ ደረጃ ምንም እንኳን ተግባቦትን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ባይሆንም በመምህሩ ተተግብሯል፡፡ መምህሩ በሁለቱም ክፍለ ጊዜያት የሰዋስው ትምህርቱን ያቀረቡት በውጤት ተኮር ዘዴ ስለሆነ በሰዋስዋዊ ቅርፆቹ ላይ ገለፃና ትንታኔ ሰጥተዋል፡፡ ነገር ግን መምህሩ ይህን ተግባር ያከናወኑት የማውጣጣት ደረጃን ተጠቅመው የተማሪዎቹን የግንዛቤ ደረጃ በማወቅና በዚያ ላይም በመመስረት ሳይሆን ውጤት ተኮር ዘዴን በመጠቀም ሰዋስዋዊ ይዘቶቹን ለሁሉም ተማሪዎች በተመሳሳይ መልኩ በማቅረብ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ሰዋስውን በተግባቦታዊ መንገድ ከማስተማር መርህ ጋር የሚጋጭ ነው፡፡ በክለሳ ድርሳኑ ክፍል እንደተገለፀው መምህሩ ሁሉንም የመዋቅር ጉዳዮች በቡድን በተመሳሳይ ሁኔታ ለማስተማመር ከመሞከር ይልቅ ተማሪዎቹ ከሚያውቁት ወይም ከደረሱበት የመዋቅር እውቀት መነሳት አለበት፡፡ ይህ ሁኔታ ግን በመምህሩ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ውስጥ አልተስተዋለም፡፡

**አፍፅሞ ማፍለቅ፦** ይህ ደረጃም ሌላው በመምህሩ ያልተተገበረ ሰዋስውን የማስተማሪያ ደረጃ ነው፡፡ አብዛኛው የትምህርቱ ሰዓት በመምህሩ ገለፃ በመሸፈኑ ተማሪዎቹ ለትምህርት በቀረበው ሰዋስዋዊ ይዘት ላይ በግልም ሆነ በጋራ የመለማመድ እድል አላገኙም፡፡ ይህ ደረጃ ተማሪዎቹ ከስህተት የጠራ ሰዋስዋዊ መዋቅር ማፍለቅና መጠቀም መቻላቸው የሚታይበት በመሆኑ ሊዘለል አይገባውም ነበር፡፡

**ፍልቀራስ፦** ይህኛው ደረጃም በሁለቱም ክፍለ ጊዜያት ውስጥ አልተተገበረም፡፡ ደረጃው ተማሪዎቹ የተማሩትን ሰዋስዋዊ ቅርጽ ተጠቅመው የራሳቸውን ዓረፍተ ነገር የሚመሰርቱበት

እና ሀሳባቸውን የሚገልጹበት በመሆኑ የሰዋስው ትምህርቱን ውጤታማነት ለመለካትም የሚያስችል ነው፡፡

ከላይ በዝርዝር እንዳየነው መምህር ሦስት ምልከታ በተካሄደባቸው ሁለት ክፍለ ጊዜያት ውስጥ ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ ለማስተማር የሚያስችሉ ቅደም ተከተሎችን ጠብቀው አላስተማሩም፡፡ ከዚያ ይልቅ የሰዋስው ትምህርቱን በገለፃ ብቻ አቅርበዋል፡፡

*3. የሰዋስው ትምህርቱ ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅቶ የመቅረቡ ሁኔታ፡-* ቀደም ሲል እንደተገለጸው በሁለቱም ክፍለ ጊዜያት የሰዋስው ትምህርቶች የቀረቡት በውጤት ተኮር ዘዴ በመሆኑ ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅተው እንዲቀርቡ አልተደረገም፡፡

*4. መምህሩ የሰዋስው ይዘቶችን በትክክል የማስተማራቸው ሁኔታ፡-* መምህር ሶስት በሁለቱም ክፍለ ጊዜያት ባቀረቧቸው የሰዋስው ትምህርቶች ውስጥ ክፍተቶች ታይተዋል፡፡ በመጀመሪያው ክፍለ ጊዜ ምእላዶችን ነፃ ፣ጥገኛ፣ የእርባታ፣ የምስረታ እያሉ ሲከፋፍሉ ምን መስፈርትን መሰረት በማድረግ ምእላዶቹ እንደተከፋፈሉ አልገለፁም፡፡ በሁለተኛው ክፍለ ጊዜም "ሁሉም የሀረግ ክፍሎች መሪና አጃቢዎች አሏቸው" የሚል አገላለፅ አስቀምጠዋል፡፡ ነገር ግን ሁሉም ሀረጎች የግድ የሚኖራቸው መሪ እንጂ አጃቢ አይደለም፡፡ ስለዚህም መምህሩ ለተማሪዎቹ ያስተላለፉት ሃሳብ ትክክል አይደለም፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ "የሀረግ ክፍሎች" ብለው ስማዊ ሀረግ፣ ግሳዊ ሀረግ፣ ወዘተ. የሚሉ ዝርዝሮችን አቅርበዋል፡፡ ነገር ግን የሀረግ ክፍሎች ማለት በሀረግ ውስጥ ያሉ ተዋቃሪዎችን እንጂ የሀረግ አይነቶችን አያመለክትም፡፡ ይህም መምህሩ የሰዋስው ይዘቶችን በትክክል ለተማሪዎቹ አለማስተማራቸውን የሚያሳይ ተጨማሪ ማስረጃ ነው፡፡ ከነዚህ ስተቶች ውጭ መምህሩ የሰዋስው ትምህርቱን በተገቢው ሁኔታ አስተምረዋል፡፡ ስለዚህም መምህር ሶስት የሰዋስው ይዘቶቹን ከፊል ተገቢነት ባለው ሁኔታ አስተምረዋል ማለት ይቻላል፡፡

*5. የሰዋስው ትምህርት ሂደቱ አብዛኛውን ተማሪ የማሳተፉ ሁኔታ፡-* በክፍሉ ውስጥ ካሉት 40 ተማሪዎች መካከል በመጀመሪያው ምልከታ ስድስት እና በሁለተኛው ምልከታ አምስት ተማሪዎች ሲጠየቁ መልስ በመስጠትና ያልገባቸውን በመጠየቅ ተሳትፈዋል፡፡ ከዚህ ውጭ ግን በሁለቱም ምልከታዎች ወቅት በቡድንም ሆነ በጥንድ እንዲወያዩ አልተደረገም፡፡ ይህ ሁኔታም አብዛኞቹ ተማሪዎች በትምህርት ሂደቱ ተሳታፊ እንዳልነበሩ ያሳያል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የሰዋስው ትምህርቱ በዋነኛነት በመምህሩ ገለፃ መቅረቡ ነው፡፡ ይህ ሁኔታም ትምህርቱ ተግባቦታዊ ዘዴን የተከተለ ላለመሆኑ ተጨማሪ ማስረጃ ሊሆን ይችላል፡፡

*6. የሰዋስው ትምህርት ክፍሉ ድባብ ምን ይመስላል፦* በሁለቱም ምልታዎች ወቅት ክፍሉ ስኑ ስርዓት የሰፈነበት ነበር፡፡ መምህሩም በአግባቡ ተቆጣጥሮታል፡፡

ከዚህ በላይ በዝርዝር ከቀረቡት ትንታኔዎች መረዳት እንደሚቻለው መምህር ሦስት የሰዋስው ትምህርቱን ያቀረቡት በተግባቦታዊ አቀራረብ እና ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር አዋህደው ሳይሆን የውጤት ተኮር ዘዴን በመከተል ለተማሪዎቹ ገለፃ በመስጠት ነው፡፡ ይህ ደግሞ በዘመናችን ተቀባይነትን እያገኘ ካለው የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ጋር የሚስማማ አይደለም፡፡ በተጨማሪም ያቀረቡት የሰዋሰው ትምህርት ተገቢ ያለመሆን ችግር ተስተውሎበታል፡፡

## 4.1.4 መምህር አራት

**የመምህሩ ዳራ እና በምልከታው ወቅት የተከተሏቸው የማስተማር ሂደቶች**

መምህር አራት በቆቦ አጠቃላይና መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 11ኛ ክፍል ውስጥ አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ላይ ከሚገኙ መምህራን መካከል ለዚህ ጥናት የተመረጡ ሁለተኛው መምህር ሲሆኑ በቋንቋው የመጀመሪያ ዲግሪ አላቸው፡፡ መምህሩ በአጠቃላይ የአስራ ስድስት ዓመታት የማስተማር ልምድ ያላቸው ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለአስራ አራት ዓመታት ያክል በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አስተምረዋል፡፡ ከሁለት ዓመታት በፊት ጀምሮ ደግሞ ከላይ በተጠቀሰው ትምህርት ቤት በማስተማር ላይ ይገኛሉ፡፡ መምህሩ ከሚያስተምሩባቸው ክፍሎች መካከል 11ኛ D ተመርጦ በዚሁ የመማሪያ ክፍል ውስጥ ሁለት ጊዜ ምልከታ ተካሂዷል፡፡ በዚህም መሰረት የየዕለቶቹን የሰዋስው ትምህርቶች በሚከተለው መልኩ አቅርበዋል፡፡

**ምልከታ ሀ**

በመምህር አራት የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ላይ የመጀመሪያው ምልከታ የተካሄደው በ20/03/2003 ዓ.ም ከሰዓት በኋላ ከ8፡09 ሰዓት ጀምሮ ነው፡፡ መምህሩ በሰዓቱ ክፍል ውስጥ ተገኝተዋል፡፡ የዕለቱን የትምህት እቅድ አዘጋጅተው አምጥተዋል፡፡ አጥኚውም የትምህርት እቅዱን ተቀብሏል፡፡

**ትምህርቱ ተጀመረ**

መምህሩ ለተማሪዎቹ ሰላምታ ከሰጡ በኋላ የዕለቱን የትምህርት ርዕስ "ምዕላድ" በማለት በጥቁር ሰሌዳው ላይ ፅፈው በምዕላድ ምንነትና ክፍሎች ላይ ተማሪዎቹ በቡድን እንዲወያዩ አዘዙ፡፡ በዚህ ወቅት የመማሪያ መጽሀፋቸውን ይዘው የመጡት አራት ተማሪዎች ብቻ ስለነበሩ ሌሎቹ ተማሪዎች ወደ እነሱ በመሄድ በአንድ ቡድን ውስጥ እስከ 10 የሚደርሱ ተማሪዎች አንድ ላይ በመሆን ግማሾቹ ተቀምጠው፣ የተወሰኑት ቆመው ውይይቱ ተጀመረ፡፡ ውይይቱ ለ8

ደቂቃዎች ያክል ከተካሄደ በኋላ መምህሩ ይበቃል ስላሉ መጽሀፍ ፍለጋ የሄዱት ተማሪዎች ወደየመቀመጫዎቻቸው ተመለሱ። ከዚያም በምዕላድ ምንነትና ክፍሎች ላይ ያላቸውን ግንዛቤ እንዲገልጹ በመምህሩ ስለተጠየቁ እድል የተሰጣቸው አራት ተማሪዎች መልስ ሰጡ። ይህም 5 ደቂቃዎችን ወስዷል። በመቀጠልም መምህሩ በምዕላድ ምንነት እና ክፍሎች ላይ ለ 16 ደቂቃዎች ያክል ገለፃና ማብራሪያ አደረጉ። በገለፃው ወቅት መምህሩ በጥቁር ሰሌዳው ላይ እየፃፉ የተጠቀሙባቸው እና ተማሪዎቹ በደብተራቸው የገለበጧቸው ምሳሌዎች የሚከተሉት ናቸው።

<u>ምዕላድ</u>

ምዕላድ ከድምጽ ቀጥሎ የሚገኝ ሲሆን ራሱን ችሎ ትርጉም ሊሰጥም ላይሰጥም የሚችል ነው።

ምዕላድ፡- ነፃ ምዕላድ፡- ወርቅ፣ ልጅ፣ በር

- ጥገኛ ምዕላድ፡- - ኦች፣ - ዎች፣ - ነት ወዘተ.

ነፃ ምዕላድ፡- ራሱን ችሎ ትርጉም የሚሰጥ ማለት ነው።

ምሳሌ፡- ቤቶች = ነፃ ምዕላድ - ቤት

እስር ምዕላድ- ኦች

ጥገኛ ምዕላድ፡- ማለት ራሱን ችሎ ትርጉም የማይሰጥ የቋንቋ ቅንጣት ነው።

ጥገኛ ምዕላዶች ትርጉም እንዲሰጡ ከተፈለገ ወደ ነፃ ምዕላድ (ወደ ቃል) መጠጋት አለባቸው።

**ምዕላዶች የእርባታና የምስረታ በመባልም ይከፈላሉ።**

**የእርባታ ምዕላድ፡-** - በተለያዩ ቃላት ላይ እየተቀጠሉ ቃላትን የሚያረቡ ናቸው። የቃል ክፍልን አይቀይሩም።

- በእርባታ ምዕላዶች አማካኝነት ቃላት ለቁጥር፣ ለፆታ፣ ለመደብና ለዕምርነት ሊረቡ ይችላሉ።

ምሳሌ፡-

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ለቁጥር | - ሰው | + | - ኦች | = | ሰዎች |
| ለፆታ | - ልጅ | + | -ኢት | = | ልጇት |
| ለመደብ | - ቤት | + | - ኤ | = | ቤቴ |
| ለዕምርነት | - ቤት | + | - ኡ | = | ቤቱ |

**የምስረታ ምዕላድ፡-** - በቃላት ላይ ሲቀጠሉ የተቀጠሉበትን ቃል የቃል ክፍል ይቀይራሉ።

ምሳሌ፡-

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ደግ | + -ነት | = ደግነት | = | ከቅፅል ወደ ስም |
| ኃይል | + -ኛ | = ኃይለኛ | = | ከስም ወደ ቅጽል |
| ቂም | + -ኛ | = ቂመኛ | = | ከስም ወደ ቅጽል |

መምህሩ በገለፃቸው መሀል ለተማሪዎቹ ያልገባቸው ነገር ካለ እንዲጠይቁ እድል ሰጥተዋል። ነገር ግን የጠየቀ ተማሪ የለም። በመጨረሻም የዕለቱ ክፍለ ጊዜ መጠናቀቁን የሚያበስረው ደወል በመሰማቱ የዕለቱ ትምህርት ተጠናቀቀ። የዕለቱን ትምህርት ለማቅረብ በአጠቃላይ 29 ደቂቃዎች የወሰደ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 16 ደቂቃው በመምህሩ ገለፃ የተሸፈነ ነው።

### ምልከታ ለ

በመምህር አራት ላይ ሁለተኛው ምልከታ የተካሄደው በ23/03/2003 ዓ.ም ከሰዓት በኋላ ከ6:50 ሰዓት ጀምሮ ነው። መምህሩ በሰዓቱ በክፍል ውስጥ ተገኝተዋል። የዕለቱን የትምህርት ዕቅድ አዘጋጅተው አምጥተዋል። አጥኚውም የትምህርት ዕቅዱን ተቀብሏል።

### ትምህርቱ ተጀመረ

መምህሩ ለተማሪዎቹ ሰላምታ ከሰጡ በኋላ የዕለቱ ትምህርት "ሀረግ" የሚል መሆኑን ገልፀው ይህንኑ በጥቁር ሰሌዳው ላይ ፃፉ። ቀጥሎም ተማሪዎቹ ስለ ሀረግ ምንነት የሚያውቁትን እንዲናገሩ ጠየቁ። ሦስት ተማሪዎች መልስ ሰጡ። ከዚያም መምህሩ ስለ ሀረግ ምንነት እና ዓይነቶች በቅደም ተከተል ለ18 ደቂቃዎች ያክል ገለፃ አደረጉ። መምህሩ በገለፃቸው ወቅት የተጠቀሙባቸው እና ተማሪዎቹ በደብተራቸው ላይ የገለበጧቸው ምሳሌዎች የሚከተሉት ናቸው።

<u>ሀረግ ምንድን ነው?</u>

ሀረግ በቀደምት ምሁራን ያልተሟላ ሀሳብን፣ በጅምር የቀረ መልእክትን የያዘ የቃላት ስብስብ ተደርጎ ሲበየን ቆይቷል። ይሁን እንጂ ይህ ብያኔ ያልተሟላና በጅምር የቀረ ሀሳብን መግለጽንና የቃላት ስብስብ መሆኑን የሀረግ መሰረታዊ ባህርያት አድርጎ ስለሚወስድ የተሟላ ሊሆን አይችልም። ይህ ብያኔ የተሟላ የማይሆንባቸው ምክንያቶች፡-

- ሀረግ በቃል ደረጃ ሊመሰረት መቻሉ፣
- የተሟላ ሀሳብን አለመግለፅ የሀረግ ብቻ ሳይሆን በአረፍተነገር ደረጃም የሚታይ መሆኑ

ስለዚህ ሀረግ በአንድ ቃል ብቻ ወይም አንድ ቃል ከሌሎች ቃላት ጋር በመቀናጀት የሚፈጠር መዋቅር ነው።

የሀረግ አይነቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. ስማዊ ሀረግ
2. ግሳዊ ሀረግ
3. ቅጽላዊ ሀረግ
4. ተውሳከ ግሳዊ ሀረግ
5. መስተዋድዳዊ ሀረግ

1. ስማዊ ሀረግ፦ ስምን በመሪነት የሚይዝ ሲሆን ሌላ ቃል ከመሪው ጋር በተጣማሪነት ሊኖር ይችላል። ምሳሌ፦ - የጤፍ እንጀራ

- ጥቁር በግ

- በጣም ረጅም ዛፍ

ስማዊ ሀረግ፦ አብይ እና ንዑስ ክፍሎች ሊኖሩት ይችላሉ

2. ግሳዊ ሀረግ፦ ግስን በመሪነት የሚይዝ የሀረግ ዓይነት ነው። በተጨማሪ ሌሎች ቃላት ከመሪው ጋር በተጣማሪነት ሊይዝ ይችላል።

ምሳሌ፦ - ሀይሉ በመኪና አደጋ ሞተ

- ልጁ ወደ አዲስ አበባ ሄደ

3. ቅፅላዊ ሀረግ፦ ቅፅልን በመሪነት የያዘ ሀረግ ነው

ምሳሌ፦ - በጣም ሰነፍ

- እጅግ ቸር

4. ተውሳከ ግሳዊ ሐረግ፦ ቁጥራቸው ጥቂት ነው። እነሱም ገና፣ መቼ፣ እንደገና፣ ቶሎ፣ ግምኛ፣ ምንኛ፣ ጅልኛ ናቸው። ተውሳከ ግስ ሊመሰረት የሚችለው ከነዚህ መሪ ቃላት ነው።

ምሳሌ፦ - ሄኖክ ክፉኛ ተቋጣ።

- ደመቀ እንደ አባቱ ምንኛ ያሳዝናል።

5. መስተዋድዳዊ ሀረግ፦ የመስተዋድዳዊ ሐረግ መሪ መስተዋድድ ነው። በሌሎች ሀረጐች መሪዎች በስተቀኝ የሚገኙ ሲሆን መስተዋድዳዊ ሀረግ መሪው በቀኝም በግራም ሊገኝ ይችላል።

ምሳሌ፦ - ከትምህርት ቤት

- ከእህቴ ጋር

- ቤት ውስጥ

መምህሩ ገለፃቸውን ሲያጠናቅቁ ለተማሪዎቹ ያልገባቸው ነገር ካለ እንዲጠይቁ እድል ስለሰጡ ሁለት ተማሪዎች ጠየቁ። መምህሩም ማብራሪያ ሰጡ። በመቀጠልም ተማሪዎቹን በመማሪያ መጽሀፉ ገጽ 56-57 ያሉትን ጥያቄዎች በቤት ስራ እንዲሰሩ ነግረው ወደ ሌላ የትምህት ርዕስ ተሸጋገሩ። የዕለቱን የሰዋስው ትምህርት ለማቅረብ በጠቅላላው 25 ደቂቃዎችን የወሰደ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 18 ደቂቃውን የሸፈነው የመምህሩ ገለፃ ነው።

## ትንተና

1. መምህሩ በትምህርት እቅድ ውስጥ የሰዋስው ትምህርቱን ዓላማ በተገቢ ሁኔታ መግለፁ፦ መምህር አራት ለሁለቱ ክፍለ ጊዜያት ባዘጋጇቸው ዕለታዊ የትምህርት እቅዶች ውስጥ በእያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ዓላማዎችን አስቀምጠዋል። እነዚህ ዓላማዎች የሰዋስው

ትምህርት ራሱን ችሎ ሲቀርብ ተማሪዎቹ የሚያዳብሮአቸውን ሰዋስዋዊ ችሎታዎች ይገልፃል፡፡ በመጀመሪያው እቅድ ውስጥ ያሉት "ተማሪዎች የምዕላድን ምንነት ይልፃሉ" እና "የነፃና እስር ምዕላዶችን ልዩነት ያብራራሉ" የሚሉ ሲሆኑ በሁለተኛው እቅድ ውስጥ ያሉት ደግሞ "ተማሪዎች የሀረግን ምንነት ይገልፃሉ" እና "የሀረግ ዓይነቶችን በዓይነት በመለየት ያሳያሉ" የሚሉ ናቸው፡፡ በእነዚህ የዓላማ ገለፃዎች ውስጥ መምህሩ "ይገልፃሉ"፣ "ያብራራሉ" እና "ያሳያሉ" የሚሉ ቃላትን ተጠቅመዋል፡፡ ከዚህም የሰዋስው ትምህርቱ ዓላማዎች ግልጽና ዝርዝር በሆነ መልኩ መቀመጣቸውን መረዳት ይቻላል፡፡ ነገር ግን ዓላማዎቹ የሰዋስው ትምህርቱ ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅቶ ሲቀርብ ተማሪዎቹ የሚያዳብሩትን የተግባቦት ችሎታ ስለማይገልፁ የተሟሉ ናቸው ማለት አይቻልም፡፡ ስለዚህም መምህር አራት በትምህርት እቃዳቸው ውስጥ ከፊል ተገቢነት ባለው ሁኔታ የሰዋስው ትምህርቱን ዓላማ ገልፀዋል ማለት ይቻላል፡፡

*2. ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ ለማስተማር የሚያስችሉ ደረጃዎችን ጠብቆ የማስተማሩ ሁኔታ፡-*

መምህሩ ምልከታ በተካሄደባቸው ሁለት ክፍለ ጊዜያት ውስጥ ሰዋስውን በተግባቦታዊ መንገድ ለማስተማር የሚያስችሉ ቅደም ተከተሎችን ጠብቀው የማስተማራቸው ሁኔታ ከእያንዳንዱ ደረጃ አኳያ ሲገመገም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ማቅረቢያ፡- መምህር አራት በሁለቱም ክፍለ ጊዜያት ትምህቱን የጀመሩት የየዕለቶቹን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች (ምዕላድና ሀረግ) ለተማሪዎቹ በቀጥታ በማስተዋወቅ ነው፡፡ ነገር ግን ቀደም ሲል እንደተገለፀው በዚህ ደረጃ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች መቅረብ ያለባቸው በቀጥታ ራሳቸውን ችለው ሳይሆን በአውድ ውስጥ ሆነው ነው፡፡ ለተማሪዎቹ የሚሰጠው ማብራሪያም አውዱን መሰረት ያደረገ ሆኖ የሰዋስዋዊ ቅርጾቹን አጠቃቀም እና የሚሸከሙትን ፍቾች የሚያስረዳ መሆን አለበት፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ግን በመምህሩ አልተተገበሩም፡፡ ስለዚህም የሰዋስው ትምህርቱ ተግባቦትን ታሳቢ ባደረገ መልኩ አውድ ተዘጋጅቶለት አለመጀመሩን መረዳት ይቻላል፡፡

ማውጣጣት፡- በሁለቱም ክፍለ ጊዜያት መምህሩ ለየዕለቶቹ ባቀረቧቸው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ላይ ተማሪዎቹን ጥያቄ ጠይቀዋል፡፡ ምንም እንኳን ጥያቄ መጠየቅ በዚህ ደረጃ ጥቅም ላይ ሊውሉ ከሚችሉ ዘዴዎች አንዱ ቢሆንም መምህሩ ጥያቄዎቹን ያቀረቡት በአውድ ላይ ተመስርተው አይደለም፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎቹ ሰዋስዋዊ ይዘቶቹን ተጠቅመው በጽሁፍ ወይም በንግግር ሀሳባቸውን እንዲገልጹ እና በዚህ ላይ ተመስርተውም ተማሪዎቹ ለትምህርት

በቀረበው ሰዋስዋዊ ይዘት ላይ ያላቸውን የግንዛቤ ደረጃ ለማወቅ አልሞከሩም፡፡ እነዚህን ሁኔታዎች በማየት ደረጃው በአግባቡ አለመተግበሩን መረዳት ይቻላል፡፡

**ገለፃ፡-** በሁለቱም ምልከታዎች ወቅት ማየት እንደተቻለው አብዛኛው የትምህርት ጊዜ (በመጀመሪያው ምልከታ ከ39 ደቂቃዎች ውስጥ 26ቱ እና በሁለተኛው ምልከታ ከ25 ደቂቃዎች ውስጥ 18ቱ) የተሸፈነው በመምህሩ ገለፃ ነው፡፡ መምህሩ እነዚህን ገለፃዎች ያከናወኑት ተግባቦታዊ ደረጃዎችን ተከትለው ሳይሆን ውጤት ተኮር የማስተማር ዘዴን በመጠቀም ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው በሰዋስዋዊ ይዘቶች ላይ ገለፃ ከመካሄዱ በፊት የማውጣጣት ዘዴን በመጠቀም ተማሪዎቹ ለትምህርት በቀረበው ይዘት ላይ ያላቸውን የግንዛቤ ደረጃ ማወቅ እና በዚያ ላይ መመስረት ያስፈልጋል፡፡ ይህን ስናደርግም እንደየተማሪዎቹ ችግሮች የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ልንጠቀም እና ወደ ተለያዩ ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ ለማስተማር የሚያስችሉ ደረጃዎች ልንሸጋገር እንችላለን፡፡ መምህር አራት ግን ገለፃውን ያቀረቡት እነዚህን ጉዳዮች ተከትለው ሳይሆን ለሁሉም ተማሪዎች ተመሳሳይ በሆነ መልኩ በሰዋስዋዊ ይዘቶቹ ላይ ገለፃና ትንታኔ በመስጠት ነው፡፡ ይህም ደረጃው በአግባቡ አለመተግበሩን ያሳያል፡፡

**አፍፅሞ ማፍለቅ፡-** በሁለቱም ክፍለ ጊዜያት መምህሩ ገለፃውን ከጨረሱ በኋላ ተማሪዎቹ በግላቸውም ሆነ በቡድን ተደራጅተው በተማሯቸው ሰዋስዋዊ ይዘቶች ላይ እንዲለማመዱ አላደረጉም፡፡ በዚህም ተማሪዎቹ የዕለቱን ትምህርት ምን ያክል እንደተረዱት ማወቅ አይቻልም፡፡ መምህሩም ምጋቤ ምላሽ መስጠት አልቻሉም፡፡ በጥቅሉ ደረጃው አልተተገበረም፡፡

**ፍልቀራስ፡-** ተማሪዎቹ የተማሯቸውን ሰዋስዋዊ ቅርጾች ተጠቅመው የግላቸውን ዓረፍተ ነገሮች እንዲመሰርቱ እና ሀሳባቸውን እንዲገልጹ አልተደረገም፡፡ በዚህም ደረጃው አለመተግበሩን መረዳት ይቻላል፡፡

***3. የሰዋስው ትምህርቱ ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅቶ የመቅረቡ ሁኔታ፡-***
በሁለቱም ምልከታዎች እንደታየው መምህሩ የሰዋስው ትምህርቱን ያቀረቡት በውጤት ተኮር ዘዴ ስለሆነ ሰዋስዋዊ ይዘቶቹ ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅተው አልቀረቡም፡፡

***4. መምህሩ የሰዋስው ይዘቶችን በትክክል የማስተማሩ ሁኔታ፡-*** መምህር አራት በሁለቱም ክፍለ ጊዜያት ያቀረቧቸው የሰዋስው ትምህርቶች ጥልቀት የሌላቸው ከመሆናቸውም በላይ የግልፅነት ችግርም ይታይባቸዋል፡፡ በመጀመሪያው ክፍለ ጊዜ የምዕላድ አይነቶችን ቢዘረዝሩም ምዕላዶቹ በምን መስፈርት እንደተከፋፈሉ ያሉት ነገር የለም፡፡ በሁለተኛው ክፍለ ጊዜም አምስቱን የሀረግ ዓይነቶች የዘረዘሩ ቢሆንም በእያንዳንዱ የሀረግ ዓይነት ላይ የሰጧቸው

ገለፃዎችና ያቀረቧቸው ምሳሌዎች አነስተኛ ናቸው። በዚህ ሁኔታ ደግሞ ተማሪዎቹ ተገቢውን የሰዋስው እውቀት ያገኛሉ ተብሎ አይጠበቅም። በተጨማሪም ስለስማዊ ሃረግ እና ግሳዊ ሃረግ ሲያስተምሩ የየሃረጎቹን መሪዎች እያሰመሩ ያመለክቱ ቢሆንም እቡዩ ሃረግ የሚያጠቃልላቸውን ተዋቃሪዎች ግን በግልፅ አላመለከቱም። ስለዚህም መምህር አራት የሰዋስው ይዘቶችን አስፋፍተው እና ጥልቀት ባለው መልኩ አላስተማሩም ማለት ይቻላል።

*5. የሰዋስው ትምህርቱ ሂደት አብዛኛውን ተማሪ የማሳተፉ ሁኔታ፡-*

በክፍል ውስጥ ካሉት 42 ተማሪዎች ውስጥ በመጀመሪያው ምልከታ ሁሉም ተማሪዎች ለአንድ ጊዜ በቡድን እንዲወያዩ ሲደረግ አራት ተማሪዎች ደግሞ በግላቸው ለተጠየቁት ጥያቄ መልስ በመስጠት ተሳትፈዋል። በሁለተኛው ምልከታ ወቅትም አምስት ተማሪዎች ጥያቄ በመጠየቅ እና በመምህሩ ሲጠየቁ መልስ በመስጠት ተሳትፈዋል። ከእነዚህ ሁኔታዎች በመነሳት ትምህርቱ አብዛኛውን ተማሪ ያሳተፈ አይደለም ማለት ይቻላል። ለዚህም ምክንያቱ ትምህርቱ በተግባቦታዊ መንገድ አለመቅረቡ ነው።

*6. የሰዋስው ትምህርት ክፍሉ ድባብ ምን ይመስላል፡-*

በመጀመሪያው ምልከታ ወቅት ተማሪዎቹ በቡድን እንዲወያዩ ሲታዘዙ መጽሀፍ ወደ ያዙት ተማሪዎች ሲንቀሳቀሱ የክፍሉ ፀጥታ ተረብሿል። የተመሰረቱት ቡድኖችም እስከ 10 የሚደርሱ አባላትን የያዙ በመሆናቸው ለውይይት አመቺ አልነበሩም። በሁለተኛ ምልከታ ወቅት ግን የቡድንም ሆነ የጥንድ ውይይቶች ባለመኖራቸው የክፍሉን ፀጥታ የሚረብሹ ሁኔታዎች አልነበሩም።

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ በዝርዝር እንዳየነው መምህር አራት የሰዋስው ትምህርቱን ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅተው እና ተግባቦታዊ በሆነ አቀራረብ አላቀረቡም። ትምህርቱን ያቀረቡት የውጤት ተኮር ዘዴን በመከተል በገለፃ እና በማብራሪያ ነው። ገለፃና ማብራሪያውም የተገቢነት ችግር የሚስተዋልበት ነው።

## 4.2 በቃለ መጠይቅ ከመምህራን የተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና

ለዚህ ጥናት በደጋፊነት አገልግሎት ላይ ከዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አንዱ ቃለ መጠይቅ መሆኑ ቀደም ሲል 'የጥናቱ ዘዴ' በሚለው ክፍል ተገልጿል። ይህን ዘዴ በመጠቀም ለጥናቱ ከተመረጡት እና ምልከታ ከተካሄደባቸው አራት መምህራን ጋር ቃለ መጠይቅ በማድረግ መረጃዎች ተሰብስበዋል። ቃለ መጠይቁን ማካሄድ ያስፈለገበት ዋነኛ ምክንያት መምህራኑ 'ሰዋስውን በተግባቦታዊ መንገድ ማስተማር' ከሚለው ጉዳይ ጋር በተያያዘ ያላቸውን ግንዛቤ በማወቅ በምልከታ ከተሰበሰቡት መረጃዎች ለተገኘው ውጤት በግብአትነት የሚያገለግሉ መረጃዎችን ለማግኘት ነው። ለዚህም ይረዳ ዘንድ ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር የተያያዙ አስራ ሁለት

ጥያቄዎች በቃለ መጠይቁ ውስጥ የተካተቱ ሲሆን ለትንታኔ እንዲያመቹ በማሰብ በአምስት ርዕስ ጉዳዮች እንዲጠቃለሉ ተደርገዋል፡፡

እነዚህም፡-

1. መምህራኑ የሰዋስው ትምህርት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተካቶ መቅረቡ ባለው ፋይዳ ላይ ያላቸው እይታ፣
2. በ11ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ባላቸው ተገቢነት ላይ የመምህራኑ እይታ፣
3. መምህራኑ ለሰዋስው ትኩረት ሰጥተው የማስተማራቸው ሁኔታ፣
4. መምህራኑ ሰዋስውን ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር እያቀናጁ የማስተማራቸው ሁኔታ እና
5. መምህራኑ የሰዋስው ትምህርቱን በምን ዘዴ ያቀርባሉ? የሚሉ ናቸው፡፡

እነዚህን ርዕሰ ጉዳዮች መሠረት በማድረግ ከመምህራኑ የተገኙት መረጃዎች በሚከተለው መልኩ ተተንትነዋል፡፡

*1. መምህራኑ የሰዋስው ትምህርት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተካቶ መቅረቡ ባለው ፋይዳ ላይ ያላቸው እይታ፡-*

መምህራኑ በዚህ ጉዳይ ላይ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት መልስ ተመሳሳይ ነው፡፡ ይኸውም የሰዋስው ትምህርት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተካቶ መቅረቡ አስፈላጊ ነው የሚል ነው፡፡ አስፈላጊነቱን ሲያስረዱም በቅደም ተከተል የሚከተለውን ብለዋል፡፡ መምህር አንድ "ተማሪዎቹ በተገቢው መንገድ በቋንቋው እንዲግባቡ፣ የቋንቋውን ስርዓት እንዲያውቁ እና የቃላትን፣ የሀገሪቷን እና የዓረፍተ ነገሮችን አደረጃጀት እንዲረዱ ለማድረግ ስለሚያስችል፣ በተጨማሪም የፅሁፍንም ሆነ የንግግር ክሂልን ለማዳበር ስለሚያስችል ፥ ሰዋስው በቋንቋ ትምህርት ውስጥ መካተቱ አስፈላጊ ነው" ብለዋል፡፡ መምህር ሁለትም "ከቋንቋ ትምህርት አላማዎች አንዱ በመሆኑ፣ ትክክለኛ ተግባቦትን መፍጠር የሚቻለው ሰዋስውን በማወቅ ስለሆነ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ መካተቱ አስፈላጊ ነው" ብለዋል፡፡ መምህር ሦስት ደግሞ ተማሪዎቹ የቋንቋውን ህግጋትና ስርዓት እንዲያውቁ የሚደረግበት ስለሆነ አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡ መምህር አራትም "ተማሪዎቹ የቋንቋውን ስርዓትና ደንብ እንዲያውቁ እና በቋንቋው የበሰለ እውቀት እንዲኖራቸው ስለሚያስችል በቋንቋ ትምህርቱ ውስጥ መካተቱ አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡ በዚህም መሠረት ተጠኚ መምህራኑ የሰዋስው ትምህርት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተካቶ በመቅረቡ ላይ ያላቸው እይታ "መቅረብ አለበት፣ ፋይዳም አለው" የሚል ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## 2. በ11ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ባላቸው ተገቢነት ላይ የመምህራኑ እይታ፡-

በዚህ ስር መምህራኑ የተጠየቁት የሰዋስዋዊ ይዘቶችን መጠን፣ ዓይነታቸውን እና ለክፍል ደረጃው የመክበድና የመቅለል ሁኔታቸውን ነው፡፡ መጠናቸውን በተመለከተ አራቱም መምህራን ተመሳሳይ አስተያየት ሰጥተዋል፡፡ መምህር አንድ "ከመጠን አኳያ በጣም አነስተኛ ናቸው፤ እነዚህም ቢሆኑ ተብራርተው አልቀረቡም" ሲሉ መምህር ሁለት ደግሞ መጠናቸው አነስተኛ ነው ካሉ በኋላ "በአንድ ሴሚስተር ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች ከሦስት አይበልጡም፤ እነዚህም ቢሆኑ በተብራራ መንገድ ስላልቀረቡ መምህሩ በራሱ ጥረት ካላስፋፋቸው በስተቀር ለተማሪዎቹ የሚያስሩ አይደሉም" ብለዋል፡፡ መምህር ሦስት እና መምህር አራትም በተመሳሳይ ሁኔታ "የሰዋስዋዊ ይዘቶቹ መጠን አነስተኛ ነው ብለዋል፡፡ አይነታቸውን በተመለከተ መምህር አራት "ተብራርተው አለመቀመጣቸው እንጂ ዓይነታቸው ተገቢ ነው" ብለዋል፡፡ ሦስቱ መምህራን ግን ከመምህር አራት በተለየ ሁኔታ ዓይነታቸው ተገቢ አይደለም ይላሉ፡፡ መምህር አንድ "የተካተቱት እጅግ በጣም ጥቂት ናቸው" ሲሉ መምህር ሁለት "ዓይነታቸው በጣም ውሱን ነው፡፡ በመፅሐፉ ውስጥ ያሉት ይዘቶች ከሦስት የማይበልጡ ሲሆኑ እነዚህም ስነ-ድምፅ፣ ምዕላድና ሀረግ ናቸው" ይላሉ፡፡ መምህር ሦስትም በተመሳሳይ ሁኔታ "ዓይነታቸው በቂ ነው የሚባል አይደለም" ብለዋል፡፡

ክብደት ቅለታቸውን በተመለከተ አራቱም መምህራን ተመሳሳይ በሆነ መልኩ "በክፍል ደረጃው ላሉ ተማሪዎች ይመጥናሉ" ብለዋል፡፡

ከመምህራኑ መልስ ማየት እንደተቻለው ሁሉም መምህራን በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የተካተቱት ሰዋስዋዊ ይዘቶች መጠናቸው አነስተኛ ነው፡፡ ክብደት ቅለታቸው ግን ለክፍል ደረጃው ይመጥናል የሚል አስተያየት አላቸው፡፡ አይነታቸውን በተመለከተ ግን ሦስት መምህራን "በቂ አይደለም" ሲሉ አንድ መምህር "ተብራርተው እና ዘርዝር ተደርገው አለመቅረባቸው እንጂ በቂ ነው" ብለዋል፡፡

## 3. መምህራኑ ለሰዋስው ትኩረት ሰጥተው የማስተማራቸው ሁኔታ፡-

መምህር አንድ ለዚህ ጥያቄ መልስ ሲሰጡ "ትኩረት እሰጣለሁ" ካሉ በኋላ "በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ ያሉትን ይዘቶች ለተማሪዎቹ በሚገባ መልኩ አስፋፍቼና አብራርቼ አስተምራለሁ፡፡ ከዚህ ውጭ ግን ተጨማሪ ይዘቶችን ወደ ክፍል አላመጣም" ብለዋል፡፡ ማትም መፅሃፉ ውስጥ ያለውን ማስፋፋት እንጂ አዲስ አይነት ይዘት ከውጪ እንደማያመጡ ተናግረዋል፡፡ መምህር ሁለትም በተመሳሳይ ሁኔታ "በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ ያሉትን ይዘቶች በራሴ ጥረት አስፋፍቼ አቀርባለሁ" ካሉ በኋላ "ከመፅሐፉ ውጭ ግን አላመጣም፤ ምክንያቱም ለትምህርቱ የተመደበው በሳምንት ሁለት ክፍለ ጊዜ ብቻ በመሆኑ እንኳን ሌላ ተጨምሮበት በመፅሃፉ

ውስጥ ያሉትን ይዘቶች ለመሸፈንም አይበቃም" ብለዋል፡፡ መምህር ሦስት እና መምህር አራት ደግሞ "በመፅሀፉ ውስጥ በተጠቀሱት ርዕሶች ላይ ከተለያዩ ምንጮች መረጃዎችን እያመጣን አስፋፍተን እናስተምራለን" ብለዋል፡፡

ከመምህራኑ መልሶች መረዳት እንደሚቻለው ሁሉም ትኩረት ሰጥተው የሚያስተምሩት በመማሪያ መፅሀፉ የቀረቡትን ሰዋስዋዊ ይዘቶች ነው፡፡ በመፅሀፉ ውስጥ የተጠቀሱትን ይዘቶች አስፋፍተው ያስተምራሉ፡፡ ከዚህ ውጭ ሌሎች ይዘቶችን ከውጭ አምጥተው አያስተምሩም፡፡ ነገር ግን ከላይ በተራ ቁጥር ሁለት ለቀረባላቸው ጥያቄ መምህራኑ ሲመልሱ "በመፅሀፉ ውስጥ ያሉት ሰዋስዋዊ ይዘቶች መጠን እና ዓይነት በቂ አይደለም" ብለዋል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ መምህሩ ተጨማሪ እና ተስማሚ ይዘቶችን አዘጋጅቶ ወደ ክፍል በማምጣት ማስተማር ያለበት መሆኑን በክለሳ ድርሳኑ ክፍል ተነጋግረናል፡፡ ይህን ግን መምህራኑ አልተገበሩትም፡፡ ስለዚህም የመምህራኑ ለሰዋስው ትኩረት ሰጥቶ የማስተማር ሁኔታ በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ ባሉት ይዘቶች ላይ የተገደበ ነው ማለት ይቻላል፡፡

*4. መምህራኑ ሰዋስውን ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር እያቀናጁ የማስተማራቸው ሁኔታ፡-*

'ሰዋስውን ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር እያቀናጀህ/ሽ የማስተማር ልምድ አለህ?/አለሽ?' ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ መምህራኑ ሲመልሱ ፥ መምህር አንድ "ሰዋስውን ሳስተምር ለሌሎች ክሂሎች ያለውን ፋይዳ ለተማሪዎቹ አስረዳለሁ፡፡ ከዚያ ውጭ በልዩ ትኩረት አቀናጅቼ አላስተምርም" ካሉ በኋላ ምክንያታቸውን ሲገልፁ "ምክንያቱም እያንዳንዱ ክሂል በመፅሀፉ ውስጥ ራሱን ችሎ ስለቀረበ በመፅሀፉ መሠረት ማስተማር ስላለብኝ ነው" ሲሉ ፥ መምህር ሁለት ደግሞ "ሰዋስውን ሳስተምር ተማሪዎቹ በእግረ መንገድ በሌሎቹ ክሂሎች ላይም ይለማመዳሉ፡፡ አቅጄ ግን አልሰራም" ካሉ በኋላ "ምክንያቱም እያቀናጁ ማቅረብ በትምህርት ቤታችን የተለመደ አሠራር አይደለም" ብለዋል፡፡ መምህር ሦስት በበኩላቸው "ሰዋስውን በቀጥታ አስተምራለሁ" ካሉ በኋላ "ማቀናጀቱ አሁን እየሰራንበት ካለው መፅሀፍ ጋር የሚስማማ አይሆንም፤ ምክንያቱም መፅሀፉ ክሂሎቹን ነጣጥሎ ስለሚያቀርባቸው ሁሉም መምህራን የመፅሀፉን መከተል ያለባቸው ይመስለኛል" ብለዋል፡፡ መምህር አራት ደግሞ "ሰዋስውን በቀጥታ እያብራራሁ አስተምራለሁ" ካሉ በኋላ ምክንያታቸውን ሲያስረዱ "እያቀናጀሁ ላስተምር ብል ግን ከሌሎቹ መምህራን ያፈነገጠ ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ የሚፈቀድ አይደለም፡፡ ምክንያቱም እያንዳንዱ መምህር በመሰለው መንገድ የሚያስተምር ከሆነ ለተማሪዎቹ የምናስተላልፈው እውቀት የተለያየ ስለሚሆን ነው" ብለዋል፡፡

ከመልሶቻቸው በግልፅ መረዳት እንደሚቻለው መምህራኑ የሰዋስው ትምህርቱን የሚያቀርቡት ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅተው ሳይሆን ራሱን አስችለው ነው፡፡ አቀናጅተው

የማያቀርቡበትን ምክንያት ሲጠየቁ የሰጧቸው መልሶች በተለያየ አገላለፅ ቢገለፁም ተመሳሳይነት አላቸው። ይህንንም እያንዳንዱ መምህር የሰጠውን መልስ በማየት መረዳት ይቻላል። መምህር አንድ "እያንዳንዱ ክሂል በመፅሀፉ ውስጥ ራሱን ችሎ ስለቀረበ በመፅሀፉ መሰረት ማስተማር አለብኝ" ሲሉ ፣ መምህር ሁለት "እያቀናጁ ማቅረብ በትምህርት ቤታችን የተለመደ አሠራር አይደለም" ብለዋል። መምህር ሦስት "ማቀናጀቱ አሁን እየሠራንበት ካለው መፅሀፍ ጋር የሚስማማ አይደለም። ምክንያቱም መፅሀፉ ክሂሎቹን ነጣጥሎ ስላቀረባቸው" በማለት ሲመልሱ ፣ መምህር አራት በበኩላቸው "እያቀናጀሁ ላስተምር ብል ከሌሎቹ መምህራን ያፈነገጠ ይሆናል። ይህ ደግሞ የሚፈቀድ አይደለም" ብለዋል።

መምህራኑ ሰዋስውን ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅተው ላለማቅረባቸው የሰጧቸው ምክንያቶች በሁለት ጉዳዮች ላይ ያጠነጠኑ ናቸው። እነዚህም፡-

ሀ. በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ ሰዋስውና ሌሎቹ ክሂሎች ተቀናጅተው ስላልቀረቡ እና

ለ. አቀናጅቶ ማቅረብ በትምህርት ቤታችን የተለመደ ስላልሆነ የሚሉ ናቸው።

እነዚህ ሁለት ጉዳዮች መምህራን እንደሚሉት ሰዋስውን ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅቶ ለማስተማር እንቅፋት የሚሆኑ ምክንያቶች አይደሉም። የመጀመሪያውን ብናይ ፣ መምህራኑ እንደሚሉት በመፅሀፉ ውስጥ ሰዋስውና የቋንቋ ክሂሎቹ የቀረቡት ተነጣጥለው ቢሆን እንኳን ተነጣጥለው መቅረባቸው አቀናጅቶ ለማስተማር እንቅፋት አይሆንም። ምክንያቱም በክለሳ ድርሳኑ ክፍል እንደተጠቆመው መምህሩ የግድ የመማሪያ መፅሀፉን ብቻ መከተል የለበትም። በመፅሀፉ ውስጥ በቂ ይዘቶች ካልተካተቱ ከውጭ መርጦ ወይም አዘጋጅቶ ማምጣት ይኖርበታል። የማስተማር ዘዴውን በተመለከተም የተለያዩ ሁኔታዎችን ማለትም የሰዋስው ትምህርቱን ዓላማ፣ ለትምህርት የቀረበውን የሰዋስው ይዘት፣ የተማሪዎቹን የግንዛቤ ደረጃ ወዘተ ግምት ውስጥ በማስገባት ሰዋስውን በውጤታማነት ለማስተማር ያስችለኛል ብሎ ያመነበትን ዘዴ መርጦ ሊቀጠም ይችላል። አቀናጅቶ ማስተማርም በዚሁ ስር ሊካተት የሚችል ነው።

ሁለተኛው ምክንያትም ቢሆን ተቀባይነት ያለው አይደለም። ምክንያቱም ሰዋስውን ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅቶ ማስተማር በትምህርት ቤቶች አሠራር ላይም ሆነ በተማሪዎቹ ውጤት ላይ የማይፈለግ ተፅዕኖ አያመጣምና ነው። ምሁራን እንደሚሉት አንድ መምህር ሰዋስውን ከሌሎች ክሂሎች ጋር አቀናጅቶ ቢያስተምር የተማሪዎቹ የሰዋስው እውቀት እና የክሂል ችሎታቸው ይሻሻላል። ይህ ደግሞ መምህሩን የሚያስመሰግነው እንጂ ከማስተማር ሂደቱ አፈንገጥክ የሚያስብለው አይደለም።

በአጠቃላይ ለቃለ መጠይቁ ከሰጧቸው መልሶች እና ካቀረቧቸው ምክንያቶች በመነሳት መምህራኑ ሰዋስውን ከሌሎች የቋንቋ ክህሎች ጋር አቀናጅቶ በተግባቦታዊ አቀራረብ ማስተማር በሚለው ላይ የግንዛቤ እጥረት አለባቸው ማለት ይቻላል።

5. *መምህራኑ የሰዋስው ትምህርቱን በምን ዘዴ ያቀርባሉ?፡-* አራቱ መምህራን በክፍል ውስጥ የሰዋስው ትምህርቱን በምን ቅደም ተከተል እንደሚያስተምሩ ለቀረበላቸው ጥያቄ እንደሚከተለው መልስ ሰጥተዋል።

**መምህር አንድ፡-** *በእለቱ ይዘት ላይ ያላቸውን የቀደመ ዕውቀት እጠይቃለሁ፣ ከዚያም በይዘቱ ምንነት ላይ ተማሪዎቹን በማሳተፍ ሰፊ ማብራሪያዎችንና ገለፃዎችን እሰጣለሁ፣ ከዚያም በማስረጃ የተደገፉ ተግባራትን እሰጣለሁ፣ በቡድን በጋራ እንዲሰሩ አደርጋለሁ፣ በስራዎቻቸው ላይ ምጋቤ ምላሽ እሰጣለሁ፣ ተማሪዎቹ ያልገባቸውን እንዲጠይቁ እድል እሰጣለሁ፣ ዋና ዋና ነጥቦቹን ጠቅለል አድርጐ በማቅረብ ትምህርቱን ተጨባጭ አደርጋለሁ፣ ተጨማሪ ተግባራትን በቤት ሥራ እንዲሰሩ አደርጋለሁ።*

**መምህር ሁለት፡-** *ስለ ዕለቱ ትምህርት በሚገባ አስተዋውቃለሁ፣ የተማሪዎቹን የቀደመ ዕውቀት እጠይቃለሁ፣ ለዚህም በቡድን ተወያይተው ሀሳባቸውን እንዲገልፁ አደርጋለሁ፣ ከዚያም ማብራሪያ እሰጣለሁ፣ ስጨርስም ያልገባቸውን እንዲጠይቁ እድል እሰጣለሁ፣ ለጥያቄዎቹም መልስ እሰጣለሁ፣ በመጨረሻም የቤት ሥራ በመስጠት በሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ አብረን እንሰራለን።*

**መምህር ሦስት፡-** *በመጀመሪያ ተማሪዎቹ ስለ ይዘቱ ያላቸውን ግንዛቤ ለማወቅ እሞክራለሁ፣ ቀጥሎም በይዘቱ ላይ ማብራሪያ እሰጣለሁ፣ ከዚያም መረዳታቸውን አረጋግጣለሁ፣ በመቀጠልም ያልገባቸውን እንዲጠይቁ እድል እሰጣለሁ፣ በመጨረሻም በቤት ሥራ የሚሰሩ ጥያቄዎችን እሰጣቸዋለሁ።*

**መምህር አራት፡-** *በመጀመሪያ መርጃ መሣሪያ የሚያስፈልገው ከሆነ አዘጋጃለሁ፣ በእለቱ ትምህርት ላይ ተማሪዎቹ ያላቸውን ግንዛቤ ለማወቅ እሞክራለሁ፣ ከዚያም ገለፃ በመስጠት እና በተገለፀው መሠረት ጥያቄዎችን በመጠየቅ መረዳት አለመረዳታቸውን ለማወቅ እሞክራለሁ፣ ከዚያም ምጋቤ ምላሽ እሰጣለሁ።*

ከላይ ከቀረቡት የመምህራኑ መልሶች ማየት እንደሚቻለው ሁሉም መምህራን ሰዋስውን በተግባቦታዊ መንገድ ለማስተማር የሚያስችሉ ደረጃዎችን አልጠቀሱም። ከሌሎቹ የቋንቋ ክህሎች ጋር አቀናጅተው እንደሚያስተምሩም አልተናገሩም። በመልሶቻቸው መሠረት ሰዋስውን ያስተማሩት ራሱን አስችለው በማቅረብ እና በሰዋስዋዊ ይዘቶች ላይ በቀጥታ ገለፃና ማብራሪያ በመስጠት ነው። በዚህ መንገድ ሰዋስውን ማስተማር "ውጤት ተኮር ሰዋስውን የማስተማር

ዘዴ እንደሚባል በክለሳ ድርሳኑ ክፍል ተጠቅሷል። ስለዚህም መምህራኑ የሰዋስው ትምህርቱን በተግባቦታዊ አቀራረብ አላቀረቡም ማለት እንችላለን። መምህራኑ ትምህርቱን በተግቦታዊ አቀራረብ እንደማያቀርቡ የሚያሳይ ተጨማሪ ማስረጃም አለ። ይኸውም ሁሉም መምህራን በመልሶቻቸው ውስጥ የሰዋስው ይዘቱን በአውድ ውስጥ አካተው እንደሚያቀርቡ አለመናገራቸው ነው። በክለሳ ድርሳኑ ክፍል እንደተገለፀው የሰዋስው ትምህርትን በተግቦታዊ ዘዴ ለማቅረብ በመጀመሪያ የሰዋስው ይዘቱ በአውድ ውስጥ ተካቶ መቅረብ አለበት። ተጠኚ መምህራኑ ግን ይህን እንደሚያደርጉ አልጠቀሱም። ከዚህ ሁኔታ በመነሳትም መምህራኑ የሰዋስው ትምህርቱን በተግባቦታዊ አቀራረብ እያቀረቡ አይደለም ማለት ይቻላል።

በአጠቃላይ በቃለ መጠይቅ ከተሰበሰቡት መልሶች መረዳት እንደተቻለው መምህራኑ ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ እና ከሌሎች የቋንቋ ክህሎች ጋር አቀናጅቶ በማስተማር ላይ ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ ነው ማለት ይቻላል። ይህ ሁኔታም በምልከታ ከተሰበሰቡት መረጃዎች ለተገኘው ውጤት መንስኤ መሆን ይችላል። በምልከታ እንደታየው መምህራኑ ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ አያስተምሩም። ለዚህም አንዱ ምክንያት በቃለ መጠይቅ እንደታየው መምህራኑ ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ ስለማስተማር ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆኑ ነው ማለት ይቻላል። ስለዚህም በቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ በምልከታ የተገኘውን መረጃ ደግፎታል ማለት ይቻላል።

## 4.3 በሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

የሰነድ ፍተሻ ዘዴ በዚህ ጥናት ውስጥ በደጋፊነት አገልግሎት ላይ የዋለ ሌላኛው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ነው። ይህን ዘዴ በመጠቀም ከ11ኛ ክፍል የአማርኛ ሰዋስው ትምህርት ጋር ግንኙነት ያላቸውና በመምህራኑ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ሰነዶች ተፈትሸዋል። እነዚህም መርሃ ትምህርቱ፣የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ እና የመምህሩ መመሪያ ናቸው። በፍተሻው እነዚህ የትምህርት መሣሪያዎች የሰዋስው ትምህርትን በተግባቦታዊ አቀራረብ ለማስተማር የሚያስችሉ ጥቆማዎችን፣አቀራረቦችንና ስልቶችን መያዝ አለመያዛቸው በጥልቀት የተዳሰሰ ሲሆን ፣ በእያንዳንዳቸው ላይ የተደረገው ዳሰሳና የተገኘው ውጤት ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል።

### 4.3.1 በ11ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ግምገማ

የ11ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት አስር ምዕራፎችን የያዘ ሲሆን በዘጠኙ ምዕራፎች ውስጥ የሰዋስው ይዘቶችን አካቷል። እነዚህ ይዘቶች በተግባቦታዊ አቀራረብ መቅረብ አለመቅረባቸውን ለመገምገም እንዲቻል ቀደም ሲል በክለሳ ድርሳኑ ክፍል 'ሰዋስውን

በተግባቦታዊ አቀራረብ ለማስተማር ያስችላሉ' ተብለው የተጠቀሱት ነጥቦች ከመርሃ ትምህርት አኳያ ተመቻችተው ቀርበዋል፡፡ ነጥቦቹም፡-

1. መርሃ ትምህርቱ ለሰዋስው ትምህርት ተገቢ ትኩረት መስጠቱ፣
2. መርሃ ትምህርቱ ሰዋስዋዊ ይዘቶቹን ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅቶ የማቅረቡ ሁኔታ እና
3. መርሃ ትምህርቱ በሰዋስው ትምህርቱ ሂደት ተማሪዎቹን በጥንድና በቡድን ለማወያየት የሚያስችሉ ጥቆማዎችን መስጠቱ የሚሉ ናቸው፡፡

ከነዚህ ነጥቦች አኳያ ግምገማውን ለማካሄድ፣ ከሰዋስው ትምህርት ጋር በተያያዘ በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱ ጉዳዮችን ማየት ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም እንዲረዳ የቋንቋ ማስተማሪያውን አውደ ርዕስ፣ የሰዋስው ይዘቱን፣ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ሰዋስዋዊ ብቃት፣ የመማር ማስተማር ክንውኑን ፣የመርጃ መሣሪያዎችን፣ ማጣቀሻዎችንና ግምገማውን የሚያሳይ ሰንጠረዥ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

| ምዕራፍ | የሰዋስው ይዘት | የሚጠበቀው የሰዋስው ብቃት | የመማር ማስተማር ክንውን፣ የመርጃ መሣሪያና ማጣቀሻ | ግምገማ |
|---|---|---|---|---|
| አንድ | • ድምጸ ልሳናት /አናባቢናተናባቢ/ | • ድምጸ ልሳናትን መለየት<br>• ቃላትን በድምጸ ልሳናዊና በቀለማዊ አጻጻፍ መጻፍ | • አናበቢንና ተናባቢ ድምጾችን ለይተው ቃላትን በድምጸ ልሳናዊና ቀለማዊ አጻጻፍ ስርዓት እንዲጽፉ ምሳሌ በመስጠት በመልመጃ ማስራት | አናባቢና ተናባቢ ድምጾችን መለየታቸውን፣ ቃላትን በድምጸ ልሳናዊና ቀለማዊ አጻጻፍ ስርዓት መጻፋቸውን መከታተል |
| ሁለት | • በአረፍተ ነገር ውስጥ የቃል ክፍሎች ሙያ | • ከአረፍተ ነገር ውስጥ የቃል ክፍሎችን ሙያ መለየት | • የተለያዩ ምሳሌዎችን በመስጠት በአረፍተ ነገር ውስጥ የቃል ክፍሎችን ሙያ እንዲለዩ ማበረታታት | በአረፍተ ነገር ውስጥ የቃል ክፍሎችን ሙያ መለየታቸውን ማረጋገጥ |
| ሦስት | • በቅጥያዎች ቃልን ማርባትና መመስረት | • ቅጥያ ምዕላዶችን በመጠቀም ቃላትን ማርባትና መመስረት | • ቃላትን ለማርባትና ለመመስረት የሚያገለግሉ ቅጥያ ምዕላዶችን በመጠቀም የቅጥያ ምዕላዶችን ተግባር እንዲገልጹ ማድረግ | ለቃላት እርባታና ምስረታ የሚያገለግሉ ቅጥያ ምዕላዶችን ተግባር መግለጻቸውን ማረጋገጥ |
| አራት | • በአረፍተ ነገር ውስጥ የቃል ክፍሎች ሙያ | • በአረፍተ ነገር ውስጥ የቃል ክፍሎችን ሙያ መለየት | • አረፍተ ነገሮችን በማቅረብ ቃላቱን በየቃል ክሎቻቸው እንዲመድቡ ማበረታታት | በአረፍተ ነገር ውስጥ ያሉ ቃላት በየትኛው የቃል ክፍል እንደሚመደቡ መግለጻቸውን ማጋገጥ |
| አምስት | • የድምጽ መጥበቅና መላላት መርዘምና ማጠር የሚያመጣው የትርጉም ልዩነት | • የድምጽ መጥበቅ፣ መላላት፣ መርዘምና ማጠር ባህሪ ያላቸውን ቃላት ለይቶ | • የድምጽ መጥበቅ፣ መላላት፣ መርዘምና ማጠር ባህሪ ያላቸውን ቃላት በመጠቀም | የድምጽ መጥበቅ፣ መላላት፣ መርዘምና ማጠር ባህሪ ያላቸውን ቃላት በትክክል |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | በማውጣትና ፍቺ በመስጠት ፍቺአቸውን የሚያመለክት አረፍተ ነገር መስራት | ፍቺ በመስጠት ፍቺአቸውን የሚያመለክት አረፍተ ነገር እንዲሰሩ ማበረታታት | በመለየት ፍቺ ሰጥተው ፍቺአቸውን የሚያመለክት አረፍተ ነገር መስራታቸውን መፈተሽ |
| ስድስት | • ቃላትን በድምጸ ልሳናዊ አጻጻፍ መተንተን<br>• በቃላት ውስጥ የድምጾች መጥበቅና መላላት ማጠርና መርዘም | • ቃላትን በድምጸ ልሳናዊ አጻጻፍ ተንትኖ መጻፍ<br>• በቃላት ውስጥ ድምጾች በመጥበቅና በመላላት፣ በማጠርና በመርዘም የትርጉም ልዩነት እንደሚኖራቸው በአረፍተ ነገር ማሳየት | • የተለያዩ ምሳሌዎችን በመስጠት በቀለማዊ ስርዓት የተጻፉትን ቃላት በድምጸ ልሳናት እንዲተነትኑ፣ እንዲሁም በድምጸ ልሳናዊ ስርዓት የተጻፉትን በቀለማዊ እንዲጽፉ ማለማመድ<br>• በቃላት ውስጥ ድምጾች በመጥበቅና በመላላት፣ በማጠርና በመርዘም ባህሪያቸው የፍቺ ልዩነት እንደሚያመጡ በምሳሌ በማሳየት ማለማመድ | • ቃላትን በድምጸ ልሳናት መጻፋቸውን መፈተሽ<br>• የድምጾች መጥበቅና መላላት፣ ማጠርና መርዘም የፍቺ ልዩነት እንደሚያመጣ በአረፍተ ነገር ማሳየታቸውን ማየት |
| ሰባት | • በአረፍተ ነገር ውስጥ የቃል ክፍሎች ሙያ<br>• የቃል እርባታና ምስረታ | • በአረፍተ ነገር ውስጥ የቃል ክፍሎችን ሙያ መዘርዘር<br>• በእርባታና በምስረታ ምዕላዶች መካከል ያለውን ልዩነት መግለጽ | • በተለያዩ አረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገኙ የቃል ክፍሎችን እንዲዘረዝሩ ማድረግ<br>• በእርታና ምስረታ ምዕላዶች መካከል ያለውን ልዩነት ምሳሌ በማቅረብ እንዲተነትኑት ማበረታታት | • በአረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኙ የቃል ክፍሎችን በመዘርዘር መግለጻቸውን ማረጋገጥ<br>• በእርባታና በምስረታ ምዕላዶች መካከል ያለውን ልዩነት መግለጻቸውን ማረጋገጥ |
| ስምንት | • የእርባታና የምስረታ ምዕላዶች | • በቃላት ላይ ልዩ ልዩ | • በቃላት ላይ ልዩ ልዩ | • በተሰሚቸው ቃላት ላይ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ምዕላዶችን በመጨመር ቅርጻቸውንና ባህሪያቸውን መለወጥ | ቅጥያዎችን በመጨመር ቅርጻቸውንና ባህሪያቸውን እንዲለዋውጡ ምሳሌዎች እየሰጡ ማሰራት | ቅጥያዎችን በማከል ቃላቱ በቅርጽና በባህሪ ለውጥ ማስከተላቸውን ማየት |
| አስር | • በአረፍተ ነገር ውስጥ የቃል ክፍሎች ሙያ | • በተለያዩ አረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉ የቃል ክፍሎችን ሙያ ለይቶ መዘርዘር | • ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል ከቀረቡ ልዩ ልዩ አረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገኙ የቃል ክፍሎችን ሙያ ለይተው እንዲዘረዝሩ ማድረግ | • በዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉ የቃል ክፍሎችን ሙያ መለየታቸውን ማረጋገጥ |

ሰንጠረዥ 3፡- በ11ኛ ክፍል የአማርኛ መርሃ ትምህርት ውስጥ የቀረበ የሰዋሰው ትምህርት

ከላይ በቀረቡት የመገምገሚያ ነጥቦች ላይ በመመስረት በሰንጠረዡ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ጉዳዮች በሚከተለው መልኩ ተተንትነዋል፡፡

1. *መርሃ ትምህርቱ ለሰዋስው ትምህርት ተገቢ ትኩረት መስጠቱ፡-* ከዚህ ነጥብ አኳያ መርሃ ትምህርቱን ለመገምገም፣ ዋና ዋና የሚባሉት የሰዋስው ይዘቶች መካተታቸውንና ሰዋስዋዊ ይዘቶቹ በአብዛኞቹ ወይም በሁሉም የመርሃ ትምህርቱ ምዕራፎች ውስጥ ተካተው መገኘታቸውን ማየት ያስፈልጋል፡፡ በክለሳ ድርሳኑ ክፍል በትምህርትነት የሚቀርቡ ዋና ዋና የሰዋስው ይዘቶች ያልናቸው ድምፅ፣ ምዕላድ፣ ቃል፣ ሐረግና ዓረፍተነገር ናቸው፡፡ እነዚህ ይዘቶች በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ መካተታቸውን ስንፈትሽ ሁሉም ተካተው ተገኝተዋል፡፡ እነዚህ ይዘቶች በምዕራፎቹ ውስጥ ያላቸውን ስርጭት ስናይም ድምፅ በምዕራፍ አንድ ገፅ1፣ በምዕራፍ አምስት ገፅ 5 እና በምዕራፍ ስድስት ገፅ 6፣ ምዕላድ በምዕራፍ ሦስት ገፅ 3፣ በምዕራፍ ሰባት ገፅ 7 እና በምዕራፍ ስምንት ገፅ 8፣ ሀረግ በምዕራፍ ሁለት ገፅ 2፣ በምዕራፍ አራት ገፅ 4፣ በምዕራፍ ሰባት ገፅ 7 እና በምዕራፍ አስር ገፅ 10 እንዲሁም ዓረፍተ ነገር በምዕራፍ ሁለት ገፅ 2፣ በምዕራፍ አራት ገፅ 4፣ በምዕራፍ ሰባት ገፅ 7 እና በምዕራፍ አስር ገፅ 10 ይገኛሉ፡፡

ከላይ ከቀረበው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው የ11ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ዋና ዋና የሚባሉትን የሰዋስዋዊ ይዘቶች አካቶ ይዟል፡፡ በእያንዳንዱ ምዕራፍ ውስጥም ሰዋስዋዊ ይዘቶች አቅርቧል፡፡ ስለዚህም መርሃ ትምህርቱ ለሰዋስው ትምህርት ተገቢ ትኩረት ሰጥቷል ማለት ይቻላል፡፡

2. *መርሃ ትምህርቱ ሰዋስዋዊ ይዘቶችን ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅቶ የማቅረቡ ሁኔታ፡-* ከዚህ ነጥብ አኳያ መርሃ ትምህርቱን ስንገመግመው ልዩ ትኩረት ሰጥቶ የሰዋስው ይዘቶችን ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅቶ አላቀረበም፡፡ እላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ ማየት እንደሚቻለውም በመማር ማስተማር ክንውኑም ሆነ በግምገማው ላይ ሰዋስዋዊ ይዘቶቹን ከሌሎቹ ክሂሎች ጋር ማቀናጀት እንደሚገባ የተጠቆመ ነገር የለም፡፡ ስለዚህም መርሃ ትምህርቱ የሰዋስው ይዘቶቹን ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅቶ ሳይሆን ራሳቸውን አስችሎ አቅርቧቸዋል ማለት ይቻላል፡፡ ይህ አይነት አቀራረብ ደግሞ ተግባቦታዊ አለመሆኑን ቀደም ሲል ተነጋግረናል፡፡

3. *መርሃ ትምህርቱ በሰዋስው ትምህርቱ ሂደት ተማሪዎቹን በጥንድና በቡድን ለማወያየት የሚያስችሉ ጥቆማዎችን መስጠቱ፡-* ከዚህ ነጥብ አኳያ መርሃ ትምህርቱን ስንፈትሸው በአንድ ቦታ ላይ ብቻ ተማሪዎቹን በቡድ ለማሰራት የሚያስችል ጥቋማ ሰጥቶ ይገኛል፡፡ ይህም በምዕራፍ አሥር ገጽ 10 ለቀረበው ሰዋስዋዊ ይዘት የተሰጠው የመማር ማስተማር ክንውን መግለጫ ነው፡፡ እላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ ማየት እንደሚቻለው "ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል ከቀረቡ ልዩ ልዩ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገኙ የቃል ክፍሎችን ሞያ ለይተው እንዲዘረዝሩ ማድረግ" የሚል መግለጫ ቀርቧል፡፡ ከዚህ ውጭ ግን ስለ ግምገማውም ሆነ ስለ መማር ማስተማር ክንውኑ

በተሰጡት ገለፃዎች ላይ ተማሪዎችን በጥንድም ሆነ በቡድን ለማወየያት የሚያስችሉ ጥቆማዎች አልቀረቡም። ስለዚህም መርሃ ትምህርቱ የሰዋስው ትምህርቱን በአብዛኛው ተማሪዎችን በጥንድና በቡድን ለማወያየት በሚያስችል መልኩ አላቀረበም ማለት ይቻላል። ይህ ሁኔታ ደግሞ የሰዋስው ትምህርቱ በተግባቦታዊ መንገድ ላለመቅረቡ ተጨማሪ ማስረጃ ሊሆን ይችላል።

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ በዝርዝር እንዳየነው የ11ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ከመጠን አኳያ ለሰዋስው ትምህርት ተገቢ ትኩረት ቢሰጥም አቀራረቡ ግን ተግባቦታዊ አይደለም። ተግባቦታዊ ያልሆነባቸው ምክንያቶችም ሰዋስዋዊ ይዘቶችን ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅቶ አለማቅረቡና በትምህርቱ ሂደት ተማሪዎችን በጥንድና በቡድን ለማወያየት የሚስችሉ ጥቆማዎችን አለመስጠቱ ናቸው።

### 4.3.2 በ11ኛ ክፍል የተማሪው መማሪያ መፅሃፍ ውስጥ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ግምገማ

በሰነድ ፍተሻ ዘዴ መረጃ ከተሰበሰበባቸው የትምህርት መማሪያዎች መካከል የተማሪው መማሪያ መፅሀፍም እንደሚገኝበት ቀደም ሲል ተገልጿል። በዚህ ዘዴ በመጠቀም በ11ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የተካተቱት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተመጣጥነውና ተግባቦታዊ በሆነ አቀራረብ መቅረብ አለመቅረባቸውን ለመፈተሽ ተሞክሯል። ፍተሻውን ለማካሄድ በክለሳ ድርሳኑ ክፍል ስለ ሰዋስው ትምህርት እና ሰዋስዋዊ ይዘቶች በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ ስለሚቀርቡበት መንገድ ከቀረበው ንድፈ ሀሳባዊ ትንታኔ የተውጣጡ ነጥቦች ጥቅም ላይ የዋሉ ሲሆን ትንተናው የተካሄደውም እነዚህን ነጥቦች መሠረት በማድረግ ነው። ነጥቦቹም፡-

1. የሰዋስው ይዘቶቹ ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተመጣጣኝ ሆነው የመቅረባቸው ሁኔታ፣
2. ሰዋስዋዊ መልመጃዎቹ በሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ላይም ለመለማመድ የማስቻላቸው ሁኔታ፣
3. ሰዋስዋዊ መልመጃዎቹ ተማሪዎቹ በጥንድና በቡድን እንዲወያዩ የማድረጋቸው ሁኔታ እና፣
4. ሰዋስዋዊ ይዘቶቹ የቀረቡበት መንገድ የሚሉ ናቸው።

በእነዚህ ነጥቦች ላይ በመመስረት የተካሄደው ትንተና በሚከተለው መልኩ ቀርቧል።

1. *የሰዋሰው ይዘቶቹ ከሌሎቹ የቋንቋ ትምህርት ዘርፎች ጋር ተመጣጣኝ ሆነው የመቅረባቸው ሁኔታ፡-* በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ አራቱ የቁንቋ ክሂሎች፣ እና ስነ-ፅሁፍ ያላቸው ስርጭት የሚከተለውን ይመስላል።

(✓) ምልክት በምዕራፉ ውስጥ የይዘቱን መኖር ሲያመለክት (x) ምልክት ደግሞ አለመኖርን ያመለክታል፡፡

| ምዕራፍ | የቋንቋ ትምህርት ዘርፎች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ማዳመጥ | መናገር | አንብቦ መረዳት | መፃፍ | ስነ-ፅሁፍ | ሰዋስው |
| 1 | x | ✓ | ✓ | ✓ | x | ✓ |
| 2 | ✓ | x | ✓ | ✓ | x | ✓ |
| 3 | x | ✓ | ✓ | ✓ | x | x |
| 4 | ✓ | ✓ | ✓ | x | ✓ | x |
| 5 | x | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | x |
| 6 | x | ✓ | ✓ | ✓ | x | ✓ |
| 7 | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | x | x |
| 8 | x | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | x |
| 9 | ✓ | x | ✓ | x | ✓ | ✓ |
| 10 | ✓ | x | ✓ | ✓ | ✓ | x |
| 11 | x | x | ✓ | x | ✓ | ✓ |
| 12 | ✓ | ✓ | ✓ | x | ✓ | ✓ |
| 13 | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | x |
| 14 | ✓ | ✓ | ✓ | x | ✓ | ✓ |
| የ(✓) ድምር | 8 | 10 | 14 | 9 | 9 | 7 |

*ሰንጠረዥ 4፡- በ11ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የቋንቋ ትምህርት ዘርፎች ስርጭት*

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ከሁሉም የቋንቋ ትምህርት ዘርፎች ባነሰ ሁኔታ ተካቶ ይገኛል፡፡ ይኸውም በመፅሀፉ ውስጥ ካሉት 14 ምዕራፎች ውስጥ አንብቦ መረዳት በአስራ አራቱም፣ መናገር በአስሩ፣ መፃፍ እና ስነ-ፅሑፍ በተመሳሳይ በዘጠኙ፣ ማዳመጥ በስምንቱ ውስጥ ሲገኙ፣ ሰዋስው ግን በሰባቱ ምዕራፎች ውስጥ ብቻ ማለትም በግማሽ ያህሉ ምዕራፎች ተካቶ ይገኛል፡፡ እነዚህም በምዕራፍ አንድ ገፅ 9፣ በምዕራፍ ሁለት ገፅ 18፣ በምዕራፍ ስድስት ከገፅ 25-28፣ በምዕራፍ ዘጠኝ ከገፅ 79-80፣ በምዕራፍ አስራ አንድ ከገፅ 96-97፣ በምዕራፍ አስራ ሁለት ከገፅ 101-102 እና በምዕራፍ አስራ አራት ከገፅ 125-126 የሚገኙ ናቸው፡፡ ከቀረቡት መረጃዎች መረዳት እንደሚቻለው የሰዋስው ትምህርት በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ ከሌሎቹ ዘርፎች ጋር በተመጣጠነ መልኩ አልቀረበም፡፡

*2. ሰዋስዋዊ መልመጃዎቹ በሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ላይም ለመለማመድ የማስቻላቸው ሁኔታ፡-*

ቀደም ሲል በክለሳ ድርሳኑ ክፍል እንደተገለፀው የሰዋስው ይዘት በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ በተግባቦታዊ መንገድ ቀርቧል ለማለት ከሚያስችሉ ነጥቦች አንዱ በሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ላይም ለመለማመድ የሚያስችል ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ ያሉትን የሰዋስው መልመጃዎች ስናይ በምዕራፍ ሁለት ገፅ 18 እና በምዕራፍ 11 ገፅ 96 የሚገኙት መልመጃዎች የመፃፍ ክሂልን ሊያለማምዱ የሚችሉ ሆነው ሲገኙ፣ በምዕራፍ ዘጠኝ ገፅ 80 የሚገኝ አንድ መልመጃ ደግሞ የንግግር ክሂልን የሚያዳብር ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ፅህፈትን ሊያዳብሩ የሚችሉት መልመጃዎች ተመሳሳይነት ያላቸው ሲሆኑ ተማሪዎቹ ሰዋስዋዊ ስህተት ያለባቸው ዓረፍተ ነገሮችን አስተካክለው እንዲፅፉ የሚያለማምዱ ናቸው፡፡ በሁለቱም ቦታዎች የሚገኘው ትዕዛዝ "ሰዋስዋዊ ስህተት የሚታይባቸውን አረፍተ ነገሮች ስህተታቸውን እየጠቆማችሁ እንደገና አቅንታችሁ ፃፏቸው" የሚል ሲሆን በመጀመሪያው ትዕዛዝ ስር አምስት እና በሁለተኛው ትዕዛዝ ስር ሰባት ሰዋስዋዊ ስህተት ያለባቸው አረፍተ ነገሮች ቀርበዋል፡፡ ተማሪዎቹ እነዚህ አረፍተ ነገሮች ያሉባቸውን ስህተቶች እያስተካከሉ ሲፅፉ በዚያውም በአረፍተ ነገር አካላት መካከል መኖር የሚገባውን ስምምነት እየተለማመዱ ስለሆነ በፅሁፍ ክሂል ላይም ይለማመዳሉ ማለት ይቻላል፡፡ በዚህ ወቅት የሚዳብረው የፅሁፍ ክሂልም "በፅሁፍ የተለያዩ ክፍሎች መሀከል ያለውን ግንኙነት ማሳየት መቻል" የሚባለው ንዑስ የፅሁፍ ክሂል ነው፡፡

ንግግርን ሊያዳብር የሚችለው መልመጃ ተማሪዎቹ በቡድን እንዲወያዩ የሚያዝዝ ሲሆን መመሪያውም፡- *ለታሪክ ምርምር መነሻ ሊሆኑ ከሚችሉ ጉዳዮች መካከል አንዱ የቋንቋዎች ውርርስና ዝምድና ነው፡፡ ቋንቋዎች የሚወራረሱበት አንዱ መንገድ ደግሞ የቃላት ውሰት ነው፡፡ አማርኛ ከሌሎች ቋንቋዎች ከተዋሳቸው ቃላት መካከል በተለያዩ ቡድኖች ሆናችሁ አስር አስር ቃላትን አቅርቡና ለታሪክ ጥናት በሚኖራቸው ፋይዳ ላይ ተወያዩ የሚል ነው፡፡*

በዚህ መመሪያ መሠረት ተማሪዎቹ ሲወያዩ የመናገር እድል ስለሚፈጠርላቸው የመናገር ችሎታቸውን ያዳብራሉ፡፡ በዚህ መልመጃ አማካኝነት ተማሪዎቹ የሚያዳብሩት ክሂልም "በተለያዩ ችግሮች ዙሪያ በሚደረግ ውይይት (ክርክር) ሂደት አንደበት ርቱዕ መሆንና አላማን ከግብ ማድረስ" የሚለውን ንዑስ የንግግር ክሂል ነው፡፡

ከዚህ ውጭ ግን በሌሎቹ ምዕራፎች ስር የቀረቡት መልመጃዎች የቋንቋ ክሂሎችን ለማዳበር የሚያስችሉ አይደሉም፡፡ ሁኔታውን ግልፅ ለማድረግ በሌሎቹ ምዕራፎች ውስጥ የሚገኙት መመሪያዎች ከዚህ ቀጥሎ ቀርበዋል፡፡

- የሚከተሉትን ቃላት በምሳሌዎቹ መሠረት በአናባቢና ተናባቢ እየለያችሁ በድምፀ ልሳናዊ አፃፃፍ ፅፉችሁ አሳዩ /ምዕራፍ አንድ ገፅ 9/፡፡
- በአማርኛ የቃላት ምስረታ መሠረት፣ ቅፅል መመስረቻ ከሆኑት ምዕላዶች መካከል "ኣ"፣ "አታ"፣ "ኧኛ"፣ "ኣማ" እና "ኣም" ይገኛሉ፡፡ በምሳሌዎቹ መሠረት ለእያንዳንዱ መስራች ምዕላድ አምስት አምስት ምሳሌዎች ፃፉ /ምዕራፍ ስድስት ገፅ 56/፡፡
- የእርባታ ምዕላዶችን ለማሳየት ይረዳ ዘንድ አንድ ግስ መርጣችሁ በተለያዩ ምድብ ተውላጠ ስሞች ተንትናችሁ አቅርቡ /ምዕራፍ ስድስት ገፅ 56/፡፡
- የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች በስማዊ ሀረግ እና በግሳዊ ሀረግ ለይታችሁ አመልክቱ /ምዕራፍ ስድስት ገፅ 56/፡፡
- ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሀረጋት በምሳሌዎቹ መሠረት የሀረግ ክፍላቸውን አመልክቱ /ምዕራፍ ስድስት ገፅ 56/፡፡
- ቀጥሎ ያሉትን የሰዋስው ጥያቄዎች በተሰጡት ማስታወሻዎች በመታገዝ ሥሩአቸው/ምዕራፍ ስድስት ገፅ 58/፡፡ (እዚህ ላይ ማስታወሻው ቀርቧል፣ ነገር ግን ጥያቄዎች አልቀረቡም፡፡)
- ከዚህ ቀጥሎ ከምንባቡ የተወሰዱና የግዕዙን የአበዛዝ ስልት የተከተሉ ቃላት ቀርበዋል፡፡ የቃላቱን የነጠላ ቁጥር ቅርፃቸውን ከገለፃችሁ በኋላ የአማርኛ አበዛዛቸውን ግለጹ /ምዕራፍ ዘጠኝ ገፅ 79/፡፡
- ቀጥለው ለቀረቡት ቃላት ቅርፃዊ አቻነት ያላቸው ተቃራኒዎች ፈልጉላቸው /ምዕራፍ ዘጠኝ ገፅ 80/፡፡
- በምሳሌዎቹ መሠረት ከተሰጡት ቃላት ሌሎች ቃላትን ጥንድ ሆናችሁ መስርቱ /ምዕራፍ 12 ገፅ 101/፡፡
- ከዚህ ቀጥሎ ሃያ ነፃና እስር ምዕላዶች በተራ ቁጥር ተለይተው ተዘርዝረዋል፡፡ እያንዳንዳቸውን በዚያው ዝርዝር ውስጥ ከሚገኝ ሌላ ተስማሚ ምዕላድ ወይም ቃል ጋር በማገጣጠም በምሳሌው መሠረት የቅኔ ህብረ ቃል ሊሆኑ የሚችሉ ቃላት መስርቱ /ምዕራፍ አስራ አራት ገፅ 125/፡፡

ከዚህ በላይ ለማየት እንደሞከርነው በመፅሀፉ ውስጥ ካሉት አስራ አንድ የሰዋስው መመሪያዎች ውስጥ ሦስቱ ብቻ ሌሎች ክሂሎችን በተጨማሪነት ለማዳበር የሚያስችሉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ እነዚህም ቢሆኑ አራቱንም የቋንቋ ክሂሎች የሚመለከቱ ሳይሆኑ የንባብ እና የንግግር ክሂልን ብቻ ለማዳበር የሚያስችሉ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ክሂሎች ውስጥም ከእያንዳንዳቸው አንድ ንዑስ ክሂልን ብቻ ለማዳበር የሚያስችሉ ናቸው፡፡ ስለዚህም በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የቀረቡት አብዛኞቹ

ሰዋስዋዊ መልመጃዎች በሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ላይም ለመለማመድ የሚያስችሉ አይደሉም ማለት እንችላለን። ይህም ሁኔታ ሰዋስዋዊ ይዘቶቹ በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ በተግባቦታዊ መንገድ አለመቅረባቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ነው።

3. *ሰዋስዋዊ መልመጃዎቹ ተማሪዎቹ በጥንድ እና በቡድን እንዲወያዩ የማድረጋቸው ሁኔታ፦* በመፅሀፉ ውስጥ ከሚገኙት አስራ አንድ የሰዋስው መልመጃዎች መመሪያዎች ውስጥ ሁለቱ ብቻ ተማሪዎቹ በጥንድና በቡድን እንዲወያዩ ያዛሉ። እነዚህም፦

- ለታሪክ ምርምር መነሻ ሊሆኑ ከሚችሉ ጉዳዮች መካከል አንዱ የቋንቋዎች ውርርስና ዝምድና ነው። ቋንቋዎች የሚወራረሱበት አንዱ መንገድ ደግሞ የቃላት ውሰት ነው። አማርኛ ከሌሎች ቋንቋዎች ከተዋሳቸው ቃላት መካከል በተለያዩ ቡድኖች ሆናችሁ አስር አስር ቃላትን አቅርቡና ለታሪክ ጥናት በሚኖራቸው ፋይዳ ላይ ተወያዩ /ምዕራፍ ዘጠኝ ገፅ 80/ እና
- በምሳሌዎቹ መሠረት ከተሰጡት ቃላት ሌሎች ቃላትን ጥንድ ሆናችሁ መስርቱ /ምዕራፍ አስራ ሁለት ገፅ 101/ የሚሉት ናቸው።

ከዚህ የምንረዳው መምህሩ የመማሪያ መፅሀፉን ብቻ ተከትሎ ቢያስተምር ተማሪዎቹ በአመቱ የሰዋስው ትምህርት ውስጥ ለሁለት ጊዜ ብቻ አንድ ጊዜ በቡድንና አንድ ጊዜ በጥንድ እንደሚወያዩ ነው። ይህ ሁኔታ ደግሞ የሰዋሰው ትምህርቱ በተግባቦታዊ አቀራረብ ላለመቅረቡ ተጨማሪ ማስረጃ ሊሆን ይችላል።

4. *ሰዋስዋዊ ይዘቶቹ የቀረቡበት መንገድ፦* በክለሳ ድርሳኑ ክፍል እንዳየነው የሰዋስው ይዘቶች በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ወይም ሰዋስውን እንደ ክሂል ማስተማር በሚሉት መንገዶች ሊቀርቡ ይችላሉ። ከዚህ አኳያ በ11ኛ ክፍል የመማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የቀረቡትን ይዘቶች ስናያቸው ከአንዱ በስተቀር ሁሉም ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የቀረቡ ናቸው። እያንዳንዳቸውን ስንመለከትም፣ በምዕራፍ አንድ ገፅ 9 ላይ ስለ ʽድምፀ ልሳናዊ አፃፃፍʼ የሚያስረዱ አራት ምሳሌዎች ከተሰጡ በኋላ ተማሪዎቹ በድምፀ ልሳናዊ አፃፃፍ እንዲፅፏቸው ስድስት ቃላት ቀርበዋል። በምዕራፍ ሁለት ገፅ 18 እና በምዕራፍ አራት ገፅ 96 ላይ ደግሞ ሰዋስዋዊ ስህተት ያለባቸው አረፍተ ነገሮች ተማሪዎቹ እንዲሠሯቸው ያለምንም ማብራሪያ በቀጥታ ቀርበዋል። በምዕራፍ ስድስት ገፅ 55-56 ላይ ደግሞ ስለምዕላድ ምንነት እና አይነቶች ማብራሪያና ምሳሌ ከቀረበ በኋላ ተማሪዎቹ የሚሰሯቸው መልመጃዎች ቀርበዋል። በምዕራፍ አስራ ሁለት ገፅ 101 እና በምዕራፍ አስራ አራት ገፅ 125-130ም እንዲሁ በቅደም ተከተል ስለ "ቃላት አመሠራረት" እና ስለ "ህብረ ቃል አፈጣጠር" ምሳሌ ከተሰጠ በኋላ ተማሪዎቹ የሚሠሯቸው መልመጃዎች ቀርበዋል። በእነዚህ መልመጃዎች ውስጥ ተማሪዎቹ አስቀድሞ

የሰዋሰው ህግጋቱ ተነግሯቸዋል። በተነገራቸው ሕግ መሠረትም ጥያቄዎቹን ይሰራሉ። ሰዋስዋዊ ይዘቶች በመማሪያ መፃሕፍት ውስጥ በዚህ መንገድ ሲቀርቡ፣ አቀራረቡ "ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር (ውጤት ተኮር)" እንደሚባል ቀደም ሲል በክለሳ ድርሳኑ ክፍል ተገልጿል።

ከላይ ከጠቀስናቸው የሰዋሰው ይዘቶች በተለየ መልኩ የቀረበ አንድ ሰዋስዋዊ ይዘት በመማሪያ መፅሀፉ ምዕራፍ ስድስት ገፅ 56-58 ይገኛል። ይህም የአማርኛ ቋንቋ ሀረግን የሚመለከት ሲሆን አቀራረቡ የሚከተለውን ይመስላል።

በመጀሪመሪያው መመሪያ "የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች በስማዊ እና በግሳዊ ሀረግ ለይታችሁ አመልክቱ" የሚል ትዕዛዝ ቀርቧል። ከዚያም ሦስት ዐረፍተ ነገሮች በምሳሌነት ቀርበው የስማዊ እና የግሳዊ ክፍላቸው ተጠቁሟል። በመቀጠልም በምሳሌዎቹ መሰረት ተማሪዎቹ የሚሰሯቸው ሰባት አረፍተ ነገሮች ቀርበዋል። በሁለተኛው መመሪያ ደግሞ "ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሐረጋት በምሳሌዎቹ መሠረት የሀረግ ክፍላቸውን አመልክቱ" የሚል ትዕዛዝ ከቀረበ በኋላ ሁለት አረፍተ ነገሮች በምሳሌነት ቀርበው በውስጣቸው የሚገኙ ቅፅላዊ እና ተውሳከ ግሳዊ ሀረጎች ተጠቁመዋል። ከምሳሌዎቹ በማስከተልም ተማሪዎቹ የሚሠሯቸው ሁለት አረፍተ ነገሮችና ስምንት ሀረጎች ተዘርዝረዋል። በመጨረሻም ስለ አማርኛ ቋንቋ የሀረግ አይነቶች፣ ስለ አመሰራረታቸውና በውስጣቸው ስለሚይዟቸው አካላት በምሳሌ የተደገፈ ማብራሪያ ቀርቧል።

ይህን አቀራረብ ስናይ የሰዋስው ህግጋቱ (ሀረግን የሚመለከቱት) አስቀድመው ለተማሪዎቹ አልተነገሩም ተማሪዎቹ የሚለማመዱባቸው መልመጃዎች ቀድመው ከቀረቡ በኋላ መጨረሻ ላይ እስካሁን የተለማመዱባቸውን መልመጃዎች ስርዓት ባለው መልኩ ለመረዳት የሚያስችሉ ህግጋት በማብራሪያዎቹ ቀርበዋል። ይህ አይነት አቀራረብ "ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ" እንደሚባል ቀደም ሲል ተገልጿል።

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ በዝርዝር ለማቅረብ እንደተሞከረው በ11ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የሚገኙ አብዛኞቹ የሰዋስው ይዘቶች "ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በሆነ መንገድ ቀርበዋል። ከዚህም መፅሀፉ ሰዋስውን ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅቶ እና ተግባቦታዊ በሆነ አቀራረብ አለማቅረቡን መረዳት ይቻላል። ይህ ሁኔታ ደግሞ መምህራኑ የሰዋስው ትምህርቱን በተግባቦታዊ አቀራረብ ላለማቅረባቸው ምክንያት መሆን ይችላል። ምክንያቱም በቃለ መጠይቁ ትንተና እንዳየነው መምህራኑ የመማሪያ መፅሀፉን ተከትለው ሰዋስውን እንደሚያስተምሩ ተናግረዋል። በዚህም መሠረት ከመማሪያ መፅሀፉ የተገኘው መረጃ በምልከታ የተገኘውን መረጃ አጠናክሮታል ማለት ይቻላል።

### 4.3.3 በ11ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመምህሩ መመሪያ መፅሀፍ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ግምገማ

የመምህሩ መመሪያ መፅሀፍ በተማሪው መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ በቀረቡት እና ከላይ ባየናቸው ሁሉም ሰዋስዋዊ ይዘቶች ላይ ለመምህሩ አቅጣጫ የሚሰጡ የተለያዩ ጉዳዮችን አካቷል። እነዚህም የሰዋስው ትምህርቱ ዝርዝር ዓላማዎች፣ ዝርዝር ይዘቶች፣ ማብራሪያ፣ የትምህርቱ አቀራረብ፣ መርጃ መሣሪያዎች፣ ግምገማና በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ ናቸው። ከእነዚህ ጉዳዮች ውስጥ ማብራሪያ፣ የትምህርቱ አቀራረብ፣ መርጃ መሣሪያዎችና ግምገማ የሰዋስው ትምህርቱ በተግባቦታዊ አቀራረብ መቅረብ አለመቅረቡን ለመገምገም ስለሚያስችሉ እነሱን በማየት እና ቀደም ሲል ስንነጋገርበት የቆየነውን 'በተግባቦታዊ አቀራረብ የማስተማር እሳቤ'ን ግምት ውስጥ በማስገባት የመምህሩ መመሪያ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ተገምግሟል። የመገምገሚያ ነጥቦቹም፣ የመምህሩ መመሪያ፡-

1. የሰዋስው ይዘቶች ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅተው እንዲቀርቡ የመጠቆሙ ሁኔታ፣
2. በሰዋስው ትምህርት ሂደት ተማሪዎቹ በጥንድ እና በቡድን እንዲወያዩ የመጠቆሙ ሁኔታ እና
3. የሰዋስው ትምህርቱ ተግባቦትን ሊፈጥሩ የሚያስችሉ ደረጃዎችን ጠብቆ እንዲቀርብ የመጠቆሙ ሁኔታ የሚሉ ናቸው።

በእነዚህ ነጥቦችም በመመስረትም ግምገማው በሚከተለው መልኩ ተከናውኗል።

1. *የመምህሩ መመሪያ የሰዋስው ይዘቶች ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅተው እንዲቀርቡ የመጠቆሙ ሁኔታ፡-* የሰዋስው ትምህርት ተግባቦታዊ ከሚሆንባቸው መንገዶች አንዱ ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅቶ መቅረቡ ነው። የመምህሩ መመሪያ መፅሀፍን ከዚህ አኳያ ስንገመግመው በማብራሪያውም ሆነ በትምህርቱ አቀራረብ ክፍል ስር ሰዋስዋዊ ይዘቶችን ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅቶ ስለማስተማር የጠቆመው ነገር የለም። ይህም ሁኔታ መመሪያ መፅሀፉ የሰዋስው ትምህርቱን በተግባቦታዊ መንገድ ላለማቅረቡ አንድ ማስረጃ ይሆናል።
2. *በሰዋስው ትምህርቱ ሂደት ተማሪዎቹ በጥንድና በቡድን እንዲወያዩ የመጠቆሙ ሁኔታ፡-* በመመሪያ መፅሀፉ ውስጥ በማብራሪያው፣ በትምህርቱ አቀራረብ፣ በመርጃ መሣሪያዎችም ሆነ በግምገማው ክፍል ተማሪዎችን በጥንድና በቡድን ለማወያየት የሚያስችሉ ጥቆማዎች አልቀረቡም።
3. *የሰዋስው ትምህርቱ ተግባቦትን ሊፈጥሩ የሚያስችሉ ደረጃዎችን ጠብቆ እንዲቀርብ የመጠቆሙ ሁኔታ፡-* በክለሳ ድርሳኑ ክፍል እንደተገለፀው ሰዋስውን በተግባቦታዊ መንገድ ለማስተማር የሚያስችሉ ደረጃዎች አሉ። እነዚህ ደረጃዎች ግን በመምህሩ መመሪያ መፅሀፍ ውስጥ አልተካተቱም።

በአጠቃላይ የ11ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመምህሩ መመሪያ መፅሀፍ መምህሩ የሰዋስው ይዘቶችን ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅቶ እንዲያቀርብ የሚያስችል ጥቆማ አልሰጠም፤ በሰዋስው ትምህርቱ ሂደት ተማሪዎቹን በጥንድና በቡድን ለማወያየት የሚያስችሉ አቅጣጫዎችን አልጠቆመም፤ በተጨማሪም ሰዋስውን በተግባቦታዊ መንገድ ለማስተማር የሚያስችሉ ደረጃዎችን አላመላከተም፡፡ ስለዚህም የመምህሩ መመሪያ መፅሀፍ የሰዋስው ትምህርትን በተግባቦታዊ መንገድ ለማስተማር በሚያስችል መልኩ አላቀረበም ማለት ይቻላል፡፡

ከላይ በዝርዝር እንዳየነው ለ11ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን ለማስተማር ታስበው የተዘጋጁት የማስተማሪያ መሣሪያዎች የሰዋስው ትምህርትን ከሌሎቹ የቋንቋ ክህሎች ጋር አቀናጅቶና ተግባቦታዊ በሆነ አቀራረብ ለማስተማር በሚያስችል መልኩ አላካተቱትም፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ መምህራኑ ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ ላለማስተማራቸው ምክንያት መሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም እነዚህ የማስተማሪያ መሣሪያዎች መምህሩ በሰዋስው ትምህርት ሂደት ምን ዓይነት ይዘቶችን በምን አይነት አቀራረብ ማስተማር እንዳለበት አቅጣጫ ስለሚጠቁሙ ነው፡፡ ስለዚህም ለክፍል ደረጃው የተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ማስተማሪያ መሣሪያዎች ተግባቦታዊ አይደሉም፤ መምህሩም በተግባቦታዊ አቀራረብ አላስተማረም ማለት ይቻላል፡፡ በአጠቃላይ በሰነድ ፍተሻ የተገኘው መረጃ በምልከታ የተገኘውን መረጃ የሚያጠናክር ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚህ ምዕራፍ በዝርዝር ለማየት እንደተሞከረው ለጥናቱ በተመረጡት የወልድያ መሰናዶና የቆቦ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ እና የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች 11ኛ ክፍል ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሰዋሰው ትምህርትን ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅተው እና በተግባቦታዊ አቀራረብ አያስተምሩም፤ ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ በማስተማር ላይ ያላቸው ግንዛቤም አነስተኛ ነው፡፡ ለክፍል ደረጃው የተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መሳሪያዎች ማለትም መርሃ ትምህርቱ፣ የተማሪው መፅሐፍ እና የመምህሩ መመሪያ የሰዋስው ትምህርትን ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅተው እና በተግባቦታዊ አቀራረብ አላካተቱም፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሀሳብ

የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ በሰሜን ወሎ ዞን በሚገኙ ሁለት የከፍተኛ ትምህርት መሠናዶ ትምህርት ቤቶች 11ኛ ክፍል ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ የማስተማር ሁኔታ ምን እንደሚመስል በጥልቀት በማጥናት ችግሮች የሚስተዋሉ ከሆነ ለችግሮቹ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን መጠቆም እንደሆነ በጥናቱ የመጀመሪያ ምዕራፍ ተገልጿል፡፡ በዚህም መሠረት በጥናቱ የተገኙ ውጤቶች እና በውጤቶቹ የተጠቆሙትን ችግሮች ለማስወገድ የተሰጡት የመፍትሄ ሀሳቦች በቅደም ተከተል ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡

## 5.1 ማጠቃለያ

በዚህ ጥናት በምዕራፍ አንድ የተቀመጡትን አላማዎች ከግብ ለማድረስ፣ የሰዋስው ትምህርትን አስመልክቶ በተለያዩ የመስኩ ምሁራን የተሰነዘሩ ሀሳቦች በምዕራፍ ሁለት የቀረቡ ሲሆን በእነዚህ ሀሳቦች ላይ በመመስረትም በምዕራፍ ሦስት በተገለጹት የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አማካይነት የተሰበሰቡት መረጃዎች በክፍል በክፍል ተለይተው እና ተተንትነው በምዕራፍ አራት ቀርበዋል፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለፀው መረጃዎቹ የተሰበሰቡት መምህራኑ ሰዋስውን በሚያስተምሩባቸው ክፍሎች በመገኘት በምልከታ፣ ከመምህራኑ ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና ከክፍል ደረጃው የሰዋስው ትምህርት ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሰነዶች ማለትም መርሃ ትምህርቱን፣ የተማሪው መማሪያ መፅሀፍን እና የመምህሩ መመሪያን በመፈተሽ ነው፡፡ በእነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች ሲተነተኑም የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡

### *5.1.1 በምልከታ ከተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና የተገኙ ውጤቶች*

1. በጥናቱ ውስጥ የተካተቱት ሁሉም መምህራን ምልከታ ለተካሄደባቸው ክፍል ጊዜያት ባዘጋጇቸው ዕለታዊ የትምህርት እቅዶች ውስጥ ያቀረቧቸው የዓላማ ገለፃዎች የሚጠቁሙት ተማሪዎቹ በግልፅ ከሚቀርብ የሰዋስው ትምህርት በኋላ የሚያዳብሩትን ሰዋስዋዊ እውቀት ወይም ችሎታ ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን በክለሳ ድርሳኑ ክፍል እንደተገለፀው የሰዋስው ትምህርት ዓላማ መጠቆም ያለበት ይህን ብቻ ሳይሆን ሰዋስው ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅቶ ሲቀርብ ተማሪዎቹ ሊያዳብሩት የሚችሉትን ተግባቦታዊ ችሎታም መሆን አለበት፡፡ በዚህም መሠረት በመምህራኑ ዕለታዊ የትምህርት እቅዶች ውስጥ የተቀመጡት የሰዋስው ትምህርት ዓላማዎች ከፊል ተገቢነት ያላቸው ሆነው ተገኝተዋል፡፡

2. ሁሉም መምህራን በዕለታዊ የትምህርት እቅዶቻቸው ውስጥ የጠቆሙት ሰዋስዋዊ ይዘቶችን በቀጥታ ለተማሪዎቹ የሚያቀርቡባቸውን ቅደም ተከተሎች ነው። ነገር ግን ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ ለማስተማር የሚያስችሉ ስልቶችን አልጠቆሙም። በዚህም ምክንያት የመምህራኑ ዕለታዊ የትምህርት እቅዶች ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ ለማስተማር በሚያስችል መልኩ ያልተዘጋጁ ሆነው ተገኝተዋል።
3. መምህራኑ በእለታዊ የትምህርት እቅዶቻቸው ውስጥ ያስቀመጧቸውን ቅደም ተከተሎች ተከትለው የሰዋስው ትምህርቱን አቅርበዋል። የትምህርት እቅዶቻቸው ደግሞ ከላይ እንደተገለፀው ተግባቦትን ሊፈጥሩ የሚችሉ ደረጃዎችን የሚያሳዩ አይደሉም። በዚህም መሰረት መምህራኑ ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ ለማስተማር የሚያስችሉ ደረጃዎችን ጠብቀው አላስተማሩም።
4. ምልከታ በተካሄደባቸው ሁሉም ክፍለ ጊዜያት ውስጥ መምህራኑ የሰዋስው ትምህርቱን ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅተው አላቀረቡም።
5. ምልከታ በተካሄደባቸው ሁሉም ክፍሎች እና ክፍለ ጊዜያት የሰዋስው ትምህርቱ ሂደት አብዛኛውን ተማሪ ያሳተፈ አልነበረም።
6. ምልከታ የተካሄደባቸው አብዛኞቹ ክፍለ ጊዜያት ስነ-ስርዓት የሰፈነባቸው እና ሰዋስውን ለማስተማር አመቺ ሆነው ተገኝተዋል።

### 5.1.2 በቃለ መጠይቅ ከተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና የተገኙ ውጤቶች

1. ሁሉም ተጠኚ መምህራን የሰዋስው ትምህርት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተካቶ መቅረቡ ፋይዳ እንዳለው ያምናሉ።
2. ሁሉም መምህራን በ11ኛ ክፍል የመማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የተካተቱት ሰዋስዋዊ ይዘቶች መጠን በቂ አይደለም ብለው ያምናሉ።
3. ሁሉም መምህራን የተማሪው መማሪያ መፅሀፍን ተከትለው ሰዋስውን እንደሚያስተምሩ ተናግረዋል። ስለዚህም ሰዋስውን በተግባቦታዊ መንገድ አያስተምሩም። ምክንያቱም የመማሪያ መፅሀፉ ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ ስለማያቀርብ።
4. ሁሉም መምህራን ሰዋስውን ራሱን አስችለው እንጂ ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅተው እንደማያስተምሩ ተናግረዋል። ይህም መምህራኑ ሰዋስውን በተግቦታዊ መንገድ እንደማያስተምሩ የሚያሳይ አንድ ማስረጃ ነው።
5. ሁሉም መምህራን የሰዋስው ትምህርትን ለተማሪዎች የሚያቀርቡት በቋንቋ መዋቅሮች እና በሰዋስዋዊ ህግጋት ላይ በቀጥታ ማብራሪያና ገለፃ በመስጠት መሆኑን ተናግረዋል። ይህም

መምህራኑ የሰዋስው ትምህርትን በተግባቦታዊ መንገድ እንደማያቀርቡ የሚያሳይ ተጨማሪ ማስረጃ ነው፡፡

6. መምህራኑ ሰዋስውን ሲያስተምሩ የሚከተሏቸውን ቅደም ተከተሎች ሲጠየቁ እንዳቸውም ተግባቦትን ለመፍጠር የሚያስችሉ ደረጃዎችን በትክክል አልጠቀሱም፡፡ ይህም መምህራኑ ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ ማስተማር በሚለው ሀሳብ ላይ የግንዛቤ እጥረት እንዳለባቸው ያመለክታል፡፡

### 5.1.3 በሰነድ ፍተሻ ከተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና የተገኙ ውጤቶች

1. የ11ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት የሰዋስው ይዘቶችን በተገቢ መጠን ቢያካትትም እነዚህን ይዘቶች ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅቶ እና በተግባቦታዊ አቀራረብ ለማስተማር የሚያስችሉ ጥቆማዎችን አልሰጠም፡፡
2. በ11ኛ ክፍል የተማሪው መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የሰዋስው ይዘቶች ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ አልቀረቡም፡፡
3. በ11ኛ ክፍል የተማሪው መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የሚገኙት ሰዋስዋዊ መልመጃዎች ተማሪዎቹን በሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ላይም ለማለማመድ በሚያስችል መልኩ አልቀረቡም፡፡ ይህም መማሪያ መፅሀፉ የሰዋስው ትምህርቱን በተግባቦታዊ መንገድ አለማቅረቡን የሚያሳይ ማስረጃ ነው፡፡
4. የመምህሩ መመሪያ የሰዋስው ትምህርቱ ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅቶ እንዲቀርብ አቅጣጫ አልሰጠም፡፡
5. የመምህሩ መመሪያ የሰዋስው ትምህርቱ ተግባቦትን ለመፍጠር የሚያስችሉ ደረጃዎችን ጠብቆ እንዲቀርብ አልጠቆመም፡፡

በአጠቃላይ የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው በወልድያ መሰናዶ እና በቆቦ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ እና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች 11ኛ ክፍል ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ ሰዋሰው ትምህርት ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅቶ እና በተግባቦታዊ አቀራረብ እየተተገበረ አይደለም፡፡ ለዚህም ምክንያቶቹ መምህራኑ ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ በማስተማር ላይ ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ መሆን እና ለክፍል ደረጃው የተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መሣሪያዎች የሰዋሰው ትምህርትን ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅቶ እና ተግባቦታዊ በሆነ አቀራረብ ለማስተማር በሚያስችል መልኩ አለማካተታቸው ናቸው፡፡

## 5.2 የመፍትሄ ሀሳብ

ከላይ በዝርዝር እንደቀረበው በሰሜን ወሎ ዞን በሚገኙት የወልድያ መሠናዶ እና የቆቦ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ እና መሠናዶ ትምህርት ቤቶች 11ኛ ክፍል ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስው ትምህርት በተግባቦታዊ አቀራረብ እየተሰጠ አይደለም። ስለዚህም የሚከተሉት የመፍትሄ እርምጃዎች ቢወሰዱ ችግሩ ሊቀረፍ እንደሚችል የዚህ ጥናት አቅራቢ ያምናል።

1. መምህራን ሰዋስውን በማስተማር ላይ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ቢደረግ፡- የቋንቋ መምህራንን የሚያስለጥኑ ተቋማት ለተማሪዎቻቸው ሰዋስዋዊ መዋቅሮችንና ሕግጋትን ብቻ ሳይሆን እነዚህን መዋቅሮች እና ሕግጋትን እንዴት ማስተማር እንደሚቻል በማሰልጠን ላይ ቢያተኩሩ። በተለይም በዘመናችን ተቀባይነትን እያገኘ ከመጣው ተግባቦታዊ አቀራረብ ጋር ሰልጣኞቻቸው እንዲተዋወቁ ቢያደርጉ።
2. መምህራን በሚያገኟቸው መልካም አጋጣሚዎች እራሳቸውን ከተግባቦታዊ አቀራረብ ጋር ቢያስተዋውቁ
3. ከትምህርት ቤት እስከ ዞን ያሉ የትምህርት አመራሮች ሰዋስውን በተግባቦታዊ አቀራረብ ማስተማርን አስመልክቶ ለመምህራኑ የስራ ላይ ስልጠና የሚያገኙበትን መንገድ ቢያመቻቹ
4. መርሃ ትምህርቱ ለክፍል ደረጃው ያቀረባቸው ሰዋስዋዊ ይዘቶች መጠን ተገቢ ቢሆንም፣ እንዴት ከሌሎቹ ክሂሎች ጋር ተቀናጅተው እና ተግባቦታዊ በሆነ አቀራረብ መቅረብ እንዳለባቸው የሚጠቁመው ነገር ስለሌለ እነዚህ ችግሮቹን አስወግዶ ቢሻሻል።
5. የ11ኛ ክፍል የተማሪው መማሪያ መፅሀፍ ሰዋስዋዊ ይዘቶችን በተገቢ መጠን ካለማካተቱም በላይ ያካተታቸውንም በተግባቦታዊ አቀራረብ አላቀረበም። ስለዚህም መማሪያ መፅሀፉ ሰዋስውን በመማሪያ መፅሀፍት ውስጥ እንዴት ማቅረብ እንደሚቻል በሚያውቁ ባለሞያዎች በአዲስ መልክ ቢዘጋጅ።
6. የመምህሩ መመሪያ የሰዋስው ትምህርት በቀጥታ የሚቀርብበትን ቅደም ተከተል ብቻ ሳይሆን ሰዋስው ከሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅቶ እና ተግባቦትን ሊፈጥሩ የሚችሉ ደረጃዎችን ጠብቆ የሚቀርብባቸውን ስልቶች በሚጠቁም መልኩ ቢሻሻል።

## ዋቢ ጽሁፎች


ሐዋዝ ወልደየስ። 2000። "በአዲስ አበባ ከተማና አማራ ክልል አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አደረጃጀትና አቀራረብ ንፅፅራዊ ጥናት"። ለማስተር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ፅሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሑፍ ክፍል።

መስሉ መንግስቱ። 1994። "የአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ሥነ ዘዴ"። ዲላ፣ ዲላ መምህራን ትምህርትና ጤና ሣይንስ ኮሌጅ የርቀት ትምህርት ክፍል /ያልታተመ/።

ማረው ዓለሙ። 1998። *የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ*። አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሠላም ማተሚያ ድርጅት።

ሰለሞን ተሰማ። 1987። "የብጤ እርማት ተግባራዊነትና ውጠታማነት"፣ በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ገላጭ ጥናት፣ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ፣ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሁፍ ክፍል።

ባዬ ይማም። 2000። *የአማርኛ ሰዋሰው* (የተሻሻለ እትም)። አዲስ አበባ፣ እሌኒ ማተሚያ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር

ትምህርት ሚኒስቴር። 1998 ። *የ11ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ* ። አዲስ አበባ፣ ትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት።

........................። 1997። *"የ11ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት"*። አዲስ አበባ ፣ ትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ።

........................። 1993። *የ11ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመምህሩ መመሪያ*። አዲስ አበባ፣ ትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት።

አልፋ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ። 2006። *ክሂሎችን የማስተማር ሥነ ዘዴ I* ። አዲስ አበባ፣ አልፋ ዩኒቨርሲቲ፣ የርቀት ትምህርት ክፍል።

አበበ መብራቴ። 2000። "በወላይታ ዞን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 9ኛ ክፍል ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አተገባበር ግምገማ (በሦስት ትምህርት ቤቶች ናሙናነት)"። ለማስተርስ ድግሪ ማማያ የቀረበ ጽሁፍ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሁፍ ክፍል አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

ጌታሁን አማረ። 2002። *ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ*። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት

Batston, R. 1994. "Product and Process: Grammar in the Second Lanaguage Classromm." In Bygate, M.et.al. (ed). *Grammar and the Lanaguage Teacher.* Englewood Cliffs, N.J. Prentice Hall International (UK) Ltd.

Brown, D.H. 2000. *Principle of Language Learning and Teaching* (4th edition). San Francisco state university, Longman inc.

Bygeate, M., Alan, T. & Eddie, W(eds.). 1994. *Grammar and the language Teacher.* Uk prentice Hall international.

Celce-Murcia, M. (ed.). 1991. *Teaching English as a Second or Foreign Language( 2nd ed).* Losangeles: Heinle and Heinle Publishers.

Chelker, S. 1994. "Pedagogical Grammar Principles and Problems". In Byget, M. et.al (eds). *Grammar and the Language Teacher.* Englewood Cliffs, N.J. Prentice Hall International Ltd.

Freeman, L. 1986. *Teachniques and Principles in Language Teaching.* New Yrok: Oxford University Press.

Grant, N. 1987. *Making the Best of your Textbook.* London: Longman.

Harmer, J. 1987. *Teaching and Learning Grammar.* New York. Longman.

Krashen, Ds. 1987. *Principles and Practices in Second Language Acquisitions.* UK Prentice Hall.

Leech, G. 1994. "Grammar and Grammars". In Byget et.al. (eds.). *Grammar and the Language Teacher.* Englewood cliffs, N.J: Printice Hall International (UK) Ltd.

Mitchell, R. 1994. "Grammar, Syllabuses and Teachers." In Bygate, M.et.al. (eds). *Grammar and the Language Teacher.* Englewood Cliffs, N.J. Printice Hall International (UK) Ltd.

Odlin, T. (ed). 1994 *Perspectives on Pedagogical Grammar.* Cambridge: Cambridge University Press.

Pedagogical grammar // http. www.com./

Prabhu, N.S. 1987. *Second Language Pedagogy.* Oxford. Oxford University Press.

Richards, J.C. and T.S. Rodgers .1995. *Approaches and Methods in Language Teaching.* Newyork: Cambridge University Press.

Stern, H.H. 1991. *Fundamental Concepts of Language Teaching.* Oxford. Oxford University Press.

Ur.P. 1991. *Grammar Practice Activities. A Practical Guide for Teacher.* Cambridge. Cambridge University Press.

## አባሪ አንድ፡- የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ምልከታ መከታተያ ቅፅ

ምልከታ የተካሄደበት፡-

የት/ቤቱ ስም ______ የክፍለ ጊዜ ርዝማኔ ______

ሴክሽን ______ የዕለቱ ትምህርት ርዕስ ______

መምህር ______ ቀን እና ዓ.ም. ______

ትምህርቱ፡- የተጀመረበት ሰዓት ______ የተማሪዎች ብዛት ______

የተጠናቀቀበት ሰዓት ______

| ተ.ቁ | የመከታተያ ነጥቦች | አይ | አዎ | አይ ከሆነ ሌላ ምን? | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| I | የመምህሩን ዕለታዊ የትምህርት እቅድ በተመለከተ | | | | |
| | 1.1 የሰዋስው ትምህርቱን ዓላማ በግልፅ አስቀምጧል | | | | |
| | 1.2 የሰዋስው ትምህርቱን በተግባቦታዊ መንገድ ለማስተማር የሚያስችሉ ስልቶችን አስቀምጧል | | | | |
| | 1.3 በመምህሩ መመሪያ ከተጠቀሰው በተለየ መልኩ ሰዋስውን በተግባቦታዊ መንገድ ለማስተማር የሚያስችሉ ዘዴዎች ተጠቁመዋል | | | | |
| የአጥኚው አስተያየት፡- | | | | | |
| II | የመምህሩን የትምህርት አቀራረብ በተመለከተ | | | | |
| | 2.1 አውድ በማቅረብ ትምህርቱን ጀምሯል | | | | |
| | 2.2 አውድ ካቀረበ በምን መንገድ? በምልልስ? በገጠመኝ? በማብራሪያ? በገለጻ? | | | | |
| | 2.3 ተማሪዎቹ ለትምህርት በቀረበው ሰዋስዋዊ ይዘት ላይ ያላቸውን ግንዛቤ ለማወቅ ሞክሯል | | | | |
| | 2.4 ለትምህርት በቀረበው ሰዋስዋዊ ይዘት ላይ ማብራሪያ እየሰጠ አስተምሯል | | | | |
| | 2.5 ተማሪዎቹ የቀረበላቸውን የሰዋስው ትምህርት መረዳታቸውን ለማወቅ ጥረት አድርጓል | | | | |
| | 2.6 መረዳታቸውን ለማወቅ ጥረት ካደረገ በምን መንገድ? በወል ድግግሞሽ? በግል ድግግሞሽ? በባለ ፍንጭ ምልልስ? | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | 2.7 ተማሪዎቹ የተማሩትን መሰረት አድርገው የራሳቸውን ዓረፍተ ነገር እንዲመሰርቱና ሀሳባቸውን እንዲገልጹ አድርጓል | | | | |
| | 2.8 በየእርከኑ ለተማሪዎች ምጋቤ ምላሽ ሰጥቷል | | | | |
| | 2.9 ምጋቤ ምላሹ ለአብዛኞቹ ተማሪዎች ተሰጥቷል | | | | |
| | 2.10 በትምህርቱ ሂደት ተማሪዎቹ ሰዋስዋዊ ይዘቱን ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅተው እንዲለማመዱበት አድርጓል | | | | |
| የአጥኚው አስተያየት፡- | | | | | |
| III | ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት የነበራቸውን ተሳትፎ በተመለከተ | | | | |
| | 3.1 የመማሪያ መሳሪያዎቻቸውን አሟልተው ይዘዋል | | | | |
| | 3.2 አብዛኞቹ ተማሪዎች በግላቸው ንቁ ተሳታፊ ናቸው | | | | |
| | 3.3 አብዛኞቹ ተማሪዎች በቡድናቸው ውስጥ ንቁ ተሳታፊ ናቸው | | | | |
| | 3.4 በትምህርቱ ሂደት ችግሮች አላጋጠሙአቸውም | | | | |
| የአጥኚው አስተያየት፡- | | | | | |

**IV. አጠቃላይ የትምህርት ሂደቱን የሚመለከቱ ጉዳዮች፡-**

4.1 የክፍሉ ድባብ ምን ይመስላል? ስነስርዓት ሰፍኖበታል? መምህሩ በአግባቡ ተቆጣጥሮታል? ሰዋስውን ለማስተማር አመቺ ነው?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

4.2 ትምህርቱ አሳታፊ ነበር?

4.3 የተማሪዎች ተሳትፎ ምን ይመስላል?

4.4 ያጋጠሙ ችግሮች ነበሩ? ካሉ ምንድን ናቸው? በምን መንገድ ተፈቱ?

4.5 የባከነ ሰዓት ነበር? በምን ምክንያት?

## አባሪ 2፡- ሰዋስውን በተግባቦታዊ መንገድ ማስተማርን አስመልክቶ ለመምህራን የቀረበ ቃለ መጠይቅ

### መምህር አንድ

ፆታ፡- ወንድ

የት/ደረጃ፡- የመጀመሪያ ዲግሪ

አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ያላቸው ልምድ፡- 7 ዓመት

ቃለ መጠይቁ የተካሄደበት ቀን፡- 04/05/03 ዓ.ም ሰዓት፡- 3፡20 - 4፡12

ቦታ፡- ወልድያ መሠናዶ ትምህርት ቤት ግቢ የመምህራን የሻይ ክበብ

በቅድሚያ ለዚህ ቃላ መጠይቅ ፈቃደኛ ሆነው በቀጠሮአችን መሠረት በሰዓቱ ስለተገኙ አመሰግናለሁ፡፡

ጥያቄ 1፡- የሰዋስው ትምህርት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተካቶ መቅረቡ ምን ያክል አስፈላጊ ነው ትላለህ?/ትያለሽ?

መልስ፡- እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በተለይ ተማሪዎች ተገቢ የሆነ ተግባቦትን ፈጥረው በቋንቋው ለመጠቀም የቋንቋውን ስርዓት በአግባቡ አውቀው ለመረዳት አስፈላጊ ነው፡፡ ለምሳሌ የአረፍተ ነገሮችን ፍሰት ጠብቆ ለመመስረት በንግግርም ቢሆን ለመጠቀም፣ የቃላትን፣ የሀረጋትን አደረጃጀት ለመረዳት በአጠቃላይ ለፅሑፍም ሆነ የንግግር ክሂልን ለማዳበርና ለማሳደግ አስፈላጊ ነው፡፡

ጥያቄ 2፡- በ11ኛ ክፍል የመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ምን ያክል ተገቢነት አላቸው ትላላህ?/ትያለሽ? (ብዛታቸው፣ ዓይነታቸው፣ ክብደት ቅለታቸው ምን ይመስላል?)

መልስ፡- የተካተቱት ይዘቶች እጅግ በጣም ጥቂት ናቸው፡፡ ስለድምፀ ልሳን በመፅሐፉ ቢጠቀስም የተብራራ አይደለም፡፡ ምዕላድ ጥሩ ነው፡፡ ሀረጎች ላይም ጥሩ ነው፡፡ የግስ ርባታ የሚለው የተብራራ ነገር የለውም ከመጠን አኳያ አነስተኛ ናቸው፡፡ እነዚያም ቢሆኑ የተብራሩ አይደሉም፡፡ ክብደት/ቅለታቸው ተገቢ ነው፡፡ መፅሀፉ ትኩረቱን ያደረገው በስነ-ፅሁፍ ላይ ነው፡፡ ለስነ-ልሳን የሰጠው ትኩረት አነስተኛ ነው፡፡ ያሉትም የተብራሩ አይደሉም፡፡

ጥያቄ 3፡- ሰዋስውን በማስተማር እና ሌሎች የቋንቋ ክሂሎችን በማስተማር መካከል ምን ግንኙነት ያለ ይመስልሃል?/ይመስልሻል?

መልስ፡- እጅግ ከፍተኛ ግንኙነት አለ ለተማሪዎቹ በንግግርም ሆነ በፅሁፍ ሀሳባቸውን በትክክል ለመግለፅ ይረዳል፡፡ በስነ-ፅሁፍ ችሎታም በኩል የሰዋስው እውቀት ካላቸው ጥሩ የስነ-

መፍታት ይቻላል። ለእያንዳንዱ ተማሪ እድል በመስጠትና እርስ በርሳቸው እንዲተራረሙ በማድረግ ችግሮቹን መፍታት ይቻላል።

ጥያቄ 9፡- ተማሪዎችህ/ሽ የቋንቋውን መዋቅር እንዲለማመዱ አዘውትረህ የምታለማምድባቸው/ጂባቸው ስልቶች ምንድን ናቸው?

መልስ፡- በጥንድ፣ በቡድን እንዲወያዩ በማድረግ፣ እንግሊዘኛውን ከአማርኛው ጋር በንፅፅር በማቅረብ። ምሳሌ ባለቤት፣ ተሳቢ፣ ማሰሪያ አንቀፅ በመዘርዘር እንዴት እንደሚገናኙና እንደሚለያይ በማሳየት አለማምዳለሁ።

ጥያቄ10፡- የሰዋስው ትምህርቱን በምታቀርብበት/ቢበት ወቅት የተማሪዎች ተሳትፎ ምን ይመስላል?

መልስ፡- በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል። ይዘቱ እስከሚገባቸው ደከም ያለ ነው ከተረዱት በኋላ ግን ከፍተኛ ይሆናል።

ጥያቄ 11፡- የሰዋስው ትምህርትን በውጤታማነት ለማስተማር ምን መደረግ አለበት ትላለህ?/ትያለሽ?

መልስ፡- ከእያንዳንዱ ክሂል ጋር ተመጣጣኝ በሆነ መንገድ የሰዋስው ይዘት መቅረብ አለበት። ይህም ክሂሎችን ተጨባጭ ለማድረግ እንዲረዳ ነው። መፅሀፉን ብናየው የሰዋስው ይዘቶቹ ያሉት 1ኛሴሚስተር ላይ ነው። ቢያንስ በየምዕራፉ መካተት ነበረባቸው። እንዲሁም ክሂሎቹን ጠቅለሎ ሊያስረዳ የሚችል የሰዋስው መልመጃዎች መካት አለባቸው።

አመስግናለሁ።

## መምህር ሁለት

ፆታ፡- ወንድ

የት/ደረጃ፡- የመጀመሪያ ዲግሪ

አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ያላቸው ልምድ፡- 5 ዓመት

የሚያስተምሩበት ትምህር ቤት፡- ወልድያ መሠናዶ

ቃለ መጠይቁ የተካሄደበት ቀን፡- 04/05/03 ዓ.ም ሰዓት፡- 8፡05 - 9፡00

ቦታ፡- ወልድያ መሠናዶ ትምህርት ቤት ግቢ የመምህራን የሻይ ክበብ

በቅድሚያ ለዚህ ቃለ መጠይቅ ፈቃደኛ ሆነው በቀጠሮአችን መሠረት በሰዓቱ ስለተገኙ አመሰግናለሁ።

ጥያቄ 1፡- የሰዋስው ትምህርት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተካቶ መቅረቡ ምን ያክል አስፈላጊ ነው ትላለህ?/ትያለሽ?

መልስ፡- አስፈላጊ ነው። ከቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች አንዱ ነው። ስለዚህም አስፈላጊ ነው። ትክክለኛ ተግባቦትን ለመፍጠር (በፅሁፍና በንግግር) የምንችለው ሰዋስውን ስናውቅ ነው።

ጥያቄ 2፡- በ11ኛ ክፍል የመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱን ሰዋስዋዊ ይዘቶች ምን ያክል ተገቢነት አላቸው ትላለህ?/ትያለሽ? (ብዛታቸው፣ ዓይነታቸው፣ ክብደት ቅለታቸው ምን ይመስላል?)

መልስ፡- ዓይነታቸው በጣም ውሱን ነው። እነዚህም ስነ ድምፅ፣ ምዕላድና ሀረግ የሚሉ ናቸው። በመፅሀፉ ውስጥ ያሉት ይዘቶች አነስተኛ ናቸው። በአንድ ሴሚስተር ውስጥ ከ3 የማይበልጡ ይዘቶች ናቸው። እነዚህም ቢሆኑ በተብራራ መንገድ አልቀረቡም። መምህሩ በራሱ ጥረት ካላስፋፋቸው በስተቀር ለተማሪዎቹ የሚያስሩ አይደሉም። በክፍል ደረጃው ላሉ ተማሪዎች የሚከብዱ አይደሉም። 9ኛ እና 10ኛ ክፍሎች ላይሰዋስውን ስለተማሩ በትምህርቱ ሂደት ተማሪዎቹ ሲቸገሩ አይታዩም። የሚከብዳቸው አይሆንም።

ጥያቄ 3፡- ሰዋስውን በማስተማር እና ሌሎች የቋንቋ ክሂሎችን በማስተማር መካከል ምን ግንኙነት ያለ ይመስልሃል?/ይመስልሻል?

መልስ፡- በሌሎቹ ክሂሎች መልዕክትን መረዳትና ማስተላለፍ የምንችለው ትክክለኛ ሰዋስው የሚታይበት የቋንቋ አጠቃቀም ስንገለገል ነው። ትክክለኛ ሰዋስው ብሎም ቋንቋ የሚጠቀም ሰው በሌላው ማህበራዊ ህይወቱም ተጠቃሚ ይሆናል።

ጥያቄ 4፡- ቋንቋን ስታስተምር/ሪ ለሰዋስው ትምህርት ምን ያክል ትኩረት ትሰጣለህ?/ ትሰጪያለሽ?

መልስ፡- በመፅሀፉ ውስጥ ያሉት ይዘቶች አነስተኛ ናቸው። እነዚህኑ እናስተምራለን። ነገር ግን እነዚህኑ በራስ ጥረት በሰፊው አቀርባለሁ። መፅሀፉ ለመነሻ የሚሆን ሰጥቷል፤ እኔ አስፋፋዋለሁ። ሌሎች ይዘቶችን እናምጣ ቢባል ጊዜ የለም። ለመፀሀፉ የተመደበው ሁለት ክፍለ ጊዜ በጣም ያንሳል።

ጥያቄ 5፡- ሰዋስውን ከሌሎች ክሂሎች ጋር እያቀናጀህ የማስተማር ልምድ አለህ?/አለሽ?

መልስ፡- ለምሳሌ ሰዋስዋዊ ስህተት ያለባቸውን ዓረፍተ ነገሮች ስናስተምር ተማሪዎቹ በእግረ መንገድ ንግግርንም ይለማመዳሉ። አቅጄ ግን አልሠራም።

ጥያቄ 6፡- ሰዋስውን ስታስተምር/ስታስተምሪ እንዴት አድርገህ ታቀርባለህ?/ ታቀርቢያለሽ? (ምን ምን ቅደም ተከተሎችን ታከናውናለህ/ታከናውኚአለሽ?)

መልስ፡- ስለዕለቱ ትምህርት በሚገባ አስተዋውቃለሁ። የተማሪዎቹን የቀደመ እውቀት እጠይቃለሁ። ለዚህም በቡድን እንዲወያዩ አደርግና ሀሳባቸውን እንዲገልፁ አደርጋለሁ።

ከዚያም ማብራሪያ እሰጣለሁ። ስጨርስም ያልገባቸውን እንዲጠይቁ እድል እሰጣለሁ። ለጥያቄያቸውም መልስ እሰጣለሁ። የቤት ስራ እሰጥና በሚቀጥለው ጊዜ አብረን እንሠራለን።

ጥያቄ 7፦ ሰዋስውን ስታስተምር/ሪ ምን ምን ችግሮች ያጋጥሙሃል?/ያጋጥሙሻል?

መልስ፦ የመጀመሪያው ማትሪክ ላይ ስለማይሰጥ ተማሪዎቹ ፍላጎት ያጣሉ (ግዴለሽ ይሆናሉ)። ከአሁን በፊት የተማሩትን ለማስታወስ አለመነሳሳት ይታያል። የማጠቀሻ መፃህፍት እጥረት፣ አንዳንዶቹ ምሳሌ አማርኛ ለኮሌጅ ደረጃ ራሳቸው ችግር አለባቸው። የመምህር መመሪያ፣ መርሃ ትምህርት የለም።

ጥያቄ 8፦ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ምን መደረግ አለበት ትላለህ?/ትያለሽ?

መልስ፦ ትምህርት ለፈተና ሳይሆን ለእውቀት የሚለውን በተማሪዎች ማስረፅ መቻል። ማትሪክ ላይ ባይመጣም ያለውን ጠቀሜታ ብንነግራቸው(ብናስረዳቸው)። በትምህርት ክፍሉ ስር ያሉ መምህራን መነጋገር እና ትምህርቱ በጥራት የሚሰጥበትን መንገድ ማመቻቸት አለብን። ተጨማሪ ማጠቀሻዎች ቢገኙ። የመምህራን መመሪያ የለም፣ መርሃ ትምህርት የለም። እነዚህ ቢሟሉ።

ጥያቄ 9፦ ተማሪዎችህ/ሽ የቋንቋውን መዋቅር እንዲለማመዱ አዘውትረህ የምታለማምድባው/ጂባቸው ስልቶች ምንድን ናቸው?

መልስ፦ መጀመሪያ ስለ ይዘቱ በደንብ እንዲረዱ እፈልጋለሁ። ስለዚህም ጥልቅ የሆነ ገለፃ እሰጣለሁ። መረዳታቸውንም ተግባራት በመስጠት ለማወቅ እሞክራለሁ። በጥንድ፣ በቡድን እና ከመምህሩ ጋር በጋራ እንዲወያዩ በድረግ መረዳታቸውን እከታተላለሁ።

ጥያቄ 10፦ የሰዋስው ትምህርቱን በምታቀርብበት/ቢበት ወቅት የተማሪዎች ተሳትፎ ምን ይመስላል?

መልስ፦ እድል ከተሰጣቸው በደንብ ይሳተፋሉ። ለምሳሌ መልመጃዎችን ስንሰጥ፣ ጥያቄ ስንጠይቅ አብዛኛው ተማሪ ይሳተፋል። በተለይ ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች መምህራን ጋር ስንነጋገር እንደተረዳሁት በአማርኛ ሰዋስው ክፍለ ጊዜ ይሳተፋሉ።

ጥያቄ 11፦ የሰዋስው ትምህርትን በውጤታማነት ለማስተማር ምን መደረግ አለበት ትላለህ?/ትያለሽ?

መልስ፦ መምህራን የሰዋስው እውቀት እና ሰዋስውን የማስተማር ችሎታ ሲኖራቸው ይገባል። ይህም ዋነኛው ነው። ለዚህም በየዩኒቨርሲቲዎች ትኩረት መስጠት አለበት። በት/ቤት ደረጃ መምህራኑ እየተወያዩ የጋራ ግንዛቤ እና የማስተማር ዘዴ መከተል አለባቸው። መፃህፍቱን መገምገም አለብን፤ ግምገማውንም ለማስተካከል ያመች ዘንድ ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ አለብን። ስተርቪዥንን መደራረግንም መፍትሄ ይሆናል። የልምድ

ልውውጥ በትምህርት ቤቶች መካከል ቢደረግ። መምህራት በትጋት የተማሪዎችን መሻሻል መከታተል አለባቸው።

አመሰግናለሁ።

መምህር ሦስት

ፆታ፡- ወንድ

የት/ደረጃ፡- የመጀመሪያ ዲግሪ

አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ያላቸው ልምድ፡- 5 ዓመት

የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት፡- ቆቦ አጠቃላይና መሠናዶ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት

ቃለ መጠይቁ የተካሄደበት ቀን፡- 05/05/03 ዓ.ም ሰዓት፡- 7፡55 - 8፡15

ቦታ፡- የርእሰ መምህሩ ቢሮ

በቅድሚያ ለዚህ ቃለ መጠይቅ ፈቃደኛ ሆነው በቀጠሮአችን መሠረት በሰዓቱ ስለተገኙ አመሰግናለሁ።

ጥያቄ 1፡- የሰዋስው ትምህርት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተካቶ መቅረቡ ምን ያክል አስፈላጊ ነው ትላለህ?/ትያለሽ?

መልስ፡- በጣም አስፈላጊ ነው። ተማሪዎቹ ህግጋትንና ስርዓትን እንዲያውቁ ስለሚረዳ አስፈላጊ ነው።

ጥያቄ 2፡- በ11ኛ ክፍል የመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ምን ያክል ተገቢነት አላቸው ትላለህ?/ትያለሽ? (ብዛታቸው፣ ዓይነታቸው፣ ክብደት ቅለታቸውን ምን ይመስላል?)

መልስ፡- መጠናቸው አነስተኛ ነው። አብዛኞቹ ይዘቶች ያሉት 12ኛ ክፍል ላይ ነው። ዓይነታቸውም በቂ ነው አያስብልም አነስተኛ ነው፤ ክብደት ቅለታቸው በደረጃው ላሉ ተማሪዎች ይመጥናል።

ጥያቄ 3፡- ሰዋስውን በማስተማር እና ሌሎች የቋንቋ ክሂሎችን በማስተማር መካከል ምን ግንኙነት ያለ ይመስልሃል?/ይመስልሻል?

መልስ፡- የተያያዙ ናቸው ሰዋስውን ስናስተምር ተማሪዎቹ ይፅፋሉ፣ ይናገራሉ፣ ያዳምጣሉ። በዚህም ክሂሎቹን ያዳብራሉ። ስለዚህም ተያያዥነት አላቸው።

ጥያቄ 4፡- ቋንቋን ስታስተምር/ሪ ለሰዋስው ትምህርት ምን ያክል ትኩረት ትሰጣለህ?/ትሰጪያለሽ?

መልስ፡- መፅሀፉ ነካክቶ ያልፋል፡፡ በርዕሶቹ መሰረት ከተለያዩ ምንጮች ምሳሌ ከደሴ ኮሌጅ ሞጁዩል፣ ከዶ/ር ባዬ እና ከዶ/ርጌታሁን መፃህፍት በማውጣጣት እስተምራለሁ፡፡ ከሌሎች ምንጮች አያመጣን እናስተምናለን፡፡

ጥያቄ 5፡- ሰዋስውን ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር እየቀናጀህ የማስተማር ልምድ አለህ?/አለሽ?

መልስ፡- ሰዋስውን በቀጥታ አስተምራለሁ፡፡

ጥያቄ 6፡- ሰዋስውን ስታስምር/ስታስተምሪ እንዴት አድርገህ ታቀርባለህ?/ታቀርቢያለሽ? (ምን ምን ቅደም ተከተሎችን ታከናውናለህ/ታከናውኚአለሽ?)

መልስ፡- በመጀመሪያ ተማሪዎች ስለይዘቱ ያላቸውን ግንዛቤ ለማወቅ እሞክራለሁ፡፡ ቀጥሎም በይዘቱ ላይ ማብራሪያ እሰጣለሁ፡፡ ቀጥሎም መረዳታቸውን እጠይቃለሁ፡፡ አረጋግጣለሁ፡፡ ከዚያም ያልገባቸውን እንዲጠይቁ እድል እሰጣለሁ፡፡ ቀጥሎም በቤት ስራ መልክ የሚሰሩ ጥያቄዎችን እሰጣቸዋለሁ፡፡

ጥያቄ 7፡- ሰዋስውን ስታስተምር/ሪ ምን ምን ችግሮች ያጋሙሃል?/ያጋጥሙሻል?

መልስ፡- አንደኛው ችግር የተዘጋጁ የመርጃ መሳሪያዎች አለመኖር ነው፡፡ ለምሳሌ ቻርቶች የሉም፡፡ መፅሀፉ የአቀራረብ ችግር አለበት፡፡ ይዘቱን መጠቆም እንጂ የተብራራ ነገር የለውም፡፡ ከተማሪው አቀባበል ጋር የተያያዘ ችግር የለም፡፡

ጥያቄ 8፡- እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ምን መደረግ አለበት ትላለህ?/ትያለሽ?

መልስ፡- መፅሐፉ ተሻሽሎ መታተም አለበት፡፡ ቢያንስ ቢያንስ ብያኔን አካቶ ቢቀርብ፤ መርጃ መሣሪያዎቹን በትምህርት ቤት ደረጃ ማዘጋጀት ይቻላል፡፡ ካልሆነም እንደ መፅሀፉ የመርጃ መሣሪያዎች ተዘጋጅተው ቢላኩ፡፡

ጥያቄ 9፡- ተማሪዎችህ/ሽ የቋንቋውን መዋቅር እንዲለማመዱ አዘውትረህ የምታለማምድባቸው/ጂባቸው ስልቶች ምንድን ናቸው?

መልስ፡- በእነዚህ ነገሮች ላይ ተደጋጋሚ መልመጃዎችን እሰጣለሁ፡፡ በግል በክፍል ውስጥ እየወጡ እንዲሠሩ አደርጋለሁ፡፡

ጥያቄ 10፡- የሰዋስው ትምህርቱን በምታቀርብበት/ቢበት ወቅት የተማሪዎች ተሳትፎ ምን ይመስላል?

መልስ፡- አብዛኞቹ ተማሪዎች ይሳተፋሉ፡፡

ጥያቄ 11፡- የሰዋስው ትምህርትን በውጤታማነት ለማስተማር ምን መደረግ አለበት ትላለህ?/ትያለሽ?

መልስ፡- መምህሩ የራሱን ጥረት ማድረግ አለበት፡፡ መፅሀፉ በአግባቡ ተዘጋጅቶና ለሰዋስው ትኩረት ተሰጥቶ መዘጋጀት አለበት፡፡

**አመሰግናለሁ፡፡**

## መምህር አራት

ፆታ፡- ወንድ

የት/ደረጃ፡- የመጀመሪያ ዲግሪ

አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ያላቸው ልምድ፡- 16 ዓመት

የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት፡- ቆቦ አጠቃላይና መሠናዶ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት

ቃለ መጠይቁ የተካሄደበት ቀን፡- 05/05/03 ዓ.ም ሰዓት፡- 8፡30 - 9፡00

ቦታ፡- የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ቢሮ

በቅድሚያ ለዚህ ቃለ መጠይቅ ፈቃደኛ ሆነው በቀጠሮአችን መሠረት በሰዓቱ ስለተገኙ አመሰግናለሁ፡፡

ጥያቄ 1፡- የሰዋስው ትምህርት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተካቶ መቅረቡ ምን ያክል አስፈላጊ ነው ትላለህ?/ትያለሽ?

መልስ፡- ተማሪዎች የቋንቋውን ስርዓትና ደንብ እንዲያውቁ ያስችላል፡፡ ለዚህም ያስፈልጋል፡፡ በቋንቋው ላይ የበሰለ እና የተሟላ እውቀት እንዲኖራቸው ያስችላል፡፡

ጥያቄ 2፡- በ11ኛ ክፍል የመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ምን ያክል ተገቢነት አላቸው ትላለህ?/ትያለሽ? (ብዛታቸው፣ ዓይነታቸው፣ ክብደት ቅለታቸው ምን ይመስላል?)

መልስ፡- ብዛታቸው አነስተኛ ነው፡፡ ዓይነታቸው አለ፡፡ ነገር ግን በበቂ ሁኔታ ተብራርተው አልተቀመጡም፡፡ ክብደት የላቸውም፡፡ የክፍል ደረጃውን ይመጥናሉ፡፡

ጥያቄ 3፡- ሰዋስውን በማስተማር እና ሌሎች የቋንቋ ክሂሎችን በማስተማር መካከል ምን ግንኙነት ያለ ይመስልሃል?/ይመስልሻል?

መልስ፡- አራቱን ክሂሎች ስናስተምር ሆን ብለንም ይሁን አይሁን ሰዋስዋዊ ህጎችንም እናለማምዳለን፡፡ ስለዚህም ግንኙት አለ፡፡

ጥያቄ 4፡- ቋንቋውን ስታስተምር/ሪ ለሰዋስው ትምህርት ምን ያክል ትኩረት ትሰጣለህ?/ትሰጪያለሽ?

መልስ፡- ተማሪው ራሱ ሰዋስውን የመማር ፍላጎት አለው፡፡ በተለይ ተማሪዎቹ አፋፍት ከሆኑ የመናገር የማዳመጥ ክሂልን እናውቀዋለን ብለው ያስባሉ፡፡ ከስር ጀምረው ህግን እየተማሩ በመምጣታቸው የቋንቋ ትምህርት የሰዋስው ትምህርት ነው የሚል ግንዛቤ አላቸው፡፡ መፅሀፉ በሚያዘው መሠረት በቀረበው ይዘት ላይ ከተለያዩ ምንጮች አምጥቼ አስፋፍቼ አስተምራለሁ፡፡

ጥያቄ 5፡- ሰዋስውን ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር እያቀናጀህ የማስተማር ልምድ አለህ?/አለሽ?

መልስ፡- ሰዋስውን በቀጥታ እያብራራሁ አስተምራለሁ። ምክንያቱም በመፅሀፉ ውስጥ ሁሉም ክሂሎች ራሳቸውን ችለው ስለቀረቡ።

ጥያቄ 6፡- ሰዋስውን ስታስተምር/ ስታስተምሪ እንዴት አድርገህ ታቀርባለህ?/ ታቀርቢያለሽ? (ምን ምን ቅደም ተከተሎችን ታከናውናለ?/ታከናውኚአለሽ?)

መልስ፡- በመጀመሪያ መርጃ መሣሪያ የሚያስፈልገው ከሆነ እናዘጋጃለን (አዘጋጃለሁ)። በእለቱ ትምህርት ላይ ተማሪዎቹ ያላቸውን ግንዛቤ ለማወቅ እሞክራለሁ። ከዚያም ገለፃ መስጠት። በተገለፀው መሠረት ጥያቄዎችን በመስጠት መረዳት አለመረዳታቸውን ማወቅ እና ምጋቤ ምላሽ እሰጣለሁ።

ጥያቄ 7፡- ሰዋስውን ስታስተምር/ሪ ምን ምን ችግሮች ያጋጥሙሃል?/ያጋጥሙሻል?

መልስ፡- ለምሳሌ ሀረግ ውስጥ ብናይ በተማሪዎችም ሆነ በመምህራን ብዥታን የሚፈጥሩ አሉ። ይህን ለማጥራት በቂ ማጣቀሻዎች ያስፈልጋሉ። ነገር ግን በት/ቤታችን የሉም። በተማሪዎቹ አቀባበል በኩል ችግር የለም። ፍላጎት አላቸው።

ጥያቄ 8፡- እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ምን መደረግ አለበት ትላለህ?/ትያለሽ?

መልስ፡- መፅሐፎችን በቋንቋው ባለቤት አስጠንቶ የሚፈለጉትን መፃህፍት ብቻ እንጂ ገበያ ላይ የተገኘው ሁሉ ባይገዛ።

ጥያቄ 9፡- ተማሪዎችህ/ሽ የቋንቋውን መዋቅር እንዲለማመዱ አዘውትረህ የምታለማምድባቸው/ ጂባቸው ስልቶች ምንድን ናቸው?

መልስ፡- ምሳሌዎችን አቅርቦ ሰርቶ በማሳየት እና እነሱም እንዲሞክሩ በማድረግ፣ ተደጋጋሚ ስራዎችን ሲሰሩ ይረዱታል።

ጥያቄ 10፡- የሰዋስው ትምህርቱን በምታቀርብበት/ቢበት ወቅት የተማሪዎች ተሳትፎ ምን ይመስላል?

መልስ፡- በጣም ጥሩ የሆነ የተማሪዎች ተሳትፎ አለ።

ጥያቄ 11፡- የሰዋስው ትምህርትን በውጤታማነት ለማስተማር ምን መደረግ አለበት ትላለህ?/ትያለሽ?

መልስ፡- በመፅሀፉ ውስጥ በቂ ይዘቶች ቢካተቱ፣ ይህ ካልሆነ ሁሉም መምህር ኃላፊነት ተሰምቶት አስፋፍቶ ላያስተምር ይችላል። አንዳንዱ ያሉትን ብቻ ነካክቶ ሊያልፍ ይችላል።

አመሰግናለሁ።

# ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የኔ መሆኑንና በጽሑፉ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን መረጃዎች በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ፡፡

ስም [illegible]

ፊርማ [illegible]


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ፋክልቲ

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

አዲስ አበባ